ከገባች በጣም ለመለመች" ሲል ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ አሹፎበታል። እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁመራ የትግራይ ናት ብሎ የተቀበለ የለም። ለዚህም ነው ይህን ማስረጃ እየፈለሰኩ የማቀርበው። ከትግራይ አብራክ የወጡት ኢትዮጵያውያን ሳይቀሩ መስክረዋል።

1ኛ ራስ መንገሻ ስዩም 2ኛ አቶ ግደይ ባሕር ሹም
3ኛ አቶ አቶ ታመነ (ሲንጎ) 4ኛ ገብረ መድህን አእርያ
5ኛ አቶ አብርሃም ያየህ የጎንደር መሆኑን በተለያዩ ጊዜ መስክረዋል።

ገብረ መድህን አእርያ አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 33 ገብረ መድህን አእርያ "በመሰረቱ ካርታ እኔም ሆንኩ ጥቂት ሰዎች ሆነን በዘፈቀደ የምንቀርጸው ነገር አይደለም። ካርታ በዓለም አቀፍ ሕግ ደንቦችና በአገር ደረጃ ከታሪክ በመነሳት በኤክስፐርቶች ተጠንቶ የሚቀረጽ ነገር ነው። በታሪክ የትግራይ ወሰን እስከ ሱዳን ጠረፍ ነው የሚል ነገር የለም። የትግራይ ክልል በማንኛውም ጊዜ ከሱዳን ጠረፍ ጋር የተያያዘ ነው የሚል ታሪክ ፈጽሞ የለም። ይሁን እንጂ የትግራይን ሪፓብሊክ እንመሰርታለን በሚል ከጎንደር ወልቃይትን በመቁረጥ እስከ ሱዳን ወስዶ እስከ አሰብ ድረስ አዲስ ካርታ ተነድፏል። ይህ ካርታ ፈጽሞ በታሪክ የሌለ ከመሆኑም ሌላ አሁንም ሆነ ወደፊት ከአጎራባች ክፍላተ ሀገር ጋር የሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። የወሎንም ሆነ የጎንደርን መሬት የእኔ ነው ብሎ የሚነሳ ክፍል ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ መፍጠሩ የማይቀር ነው" ሲሉ ተናግረው እንደነበር ገልጸዋል።

የኢዲዩ ወሳኝ ሰው የነበሩ አቶ ታመነ ወይም ሲንጎ በ1983 ዓም ሉስ አንጀለ ላይ ከኢዲኃቅ ጽፈት ቤት እንዲህ ሲሉ ተናግረው ነበር። "እኛ የትግራይ ልጆች እንኳን የትግራይን ታሪክ የኢትዮጵያን ታሪክ የማይጽፈውና የማያነበው ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። የትግራይ መሬትም ከዜት እስከ ዜት እንደሆነ አበጥሮ ያውቃል። ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ከጎንደርና ከወሎ ሕዝብ ጋር ሊያጣላው ብሎ መሬት ቆርሶ ሊወስድ ያሰበ መሆኑን ቀደም ጠራናፊት ሁነን ስንዋጋው ሳለ ጀምሮ መፈክሩ ነበር። ይህ በጠበንጃ የሚነጠቅ መሬት አንዳንድ ከአፍንጫቸው ላይ የሚያስቡ የወያኔ ደጋፊዎች ሊቀበሉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን የወያኔ ሥልጣን ሲገረሰስ ቅሌት እንዳይሆንባቸው ሊያስቡበት ይገባል" ሲሉ ተናግረው ነበር።

ገ/ጻድቅ አበራ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 3 ነሐሴ 1991 ዓም ገጽ 7 "ደርግ በ1967 ዓም የወረሳቸው ቤቶች በትግራይ ክልል በሙሉ ተመልሰዋል። ወልቃይት፣ጠገዴ እና ጠለምትን ከጎንደር አሳማጣና ኮረምን ከወሎ ወደ ትግራይ ከልለዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ውዱ ገበየሁ ዜጋ መጽሔት 1 ዓመት ቁ 5 የካቲት/መጋቢት 1992 ዓም ገጽ 30 "የወልቃይትና የጠለምት መሬት ወደ ትግራይ መሄድ አለመረጋጋት ያመጣል" ሲሉ ጽፈዋል።



አቶ ሐቢቡ ታከለ "በጎንደር ላይ ሰላም እንዲመጣ ከፈለጋችሁ ወልቃይት ጠገዴና ሌሎችም ወረዳዎች ወደ ቀድሞ ግዛታቸው ይመለሱ" ሲሉ ተናግረዋል።

መጽሐፈ ሲራክ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 5 ቁጥር 8 መጋቢት 7 ቀን 1992 ዓም ገጽ 7"ዋ ጎንደር ወልቃይት ጠገዴ እግር ኖሮት እሰም ለስደት ሲዳረግ ሁመራ ሌላውም ሲከተል የትውልድ መሬቴ የትም ሲነጉድ ወኔዬ ከውስጤ ገንፍሎ አሳልኩትም በሀ አትሂድ ውበትሽ ሲነጠቅ ካልተቆጨሁ መሬትሽ ሲሄድ ካልተነሳሁ እትብቴን መልሽ እናታለም እኔስ ለራሴም አልበጀሁ" ሲሉ ጽፈዋል። የጎንደር ማህበር መርኃ ግብር ዋቢ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ማሕበሩ ሲመሰረት ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ወረዳዎችን ከሌሎች የጎንደር ክፍለ ሀገር ወረዳዎች ጋር አጣምሮ የያዘ መሆኑ ሰነዱ ዋቢ ነው።

የጎንደር ክፍለ ሀገር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ማህበር ጥራዝ 1 መስከረም 1984 ዓም ገጽ 3 "ክልላዊ አስተዳደሩም በስሜን የተከዜን ወንዝ በማካለል ኤርትራንና ትግራይን፤ በምስራቅ ትግራይንና ወሎን፤በደቡብ የዓባይን ወይዝ በማካለል ጎጃምና በምዕራብ ሱዳን ነው። ክፍለ ሀገሩም 79.098 ካሬ ሜትር ስፋ ያለና በሰባት አውራጃዎች የጎንደር ከተማን ጨምሮ ወደ 3.7 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርበት ሲሆን የተረሳና በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ሲፈራረቁበት የኖረ ክልል ነው" ሲል ጽፏል።

መይሣው ጋዜጣ ጥር 15 ቀን 1992 ዓም ገጽ 2 "ከየትኛውም ክ/ዘመን ጀምሮ በየትኛውም የታሪክ ወቅት ወይም በየትኛውም ንጉሥ ዘመን ነው ወልቃይት ጠገዴና ሁመራ በትግራይ ስር የነበረው ተብሎ መሪዎች ቢጠየቁ መልስ የላቸውም። ሆኖ አያውቅም። በባሕልና በቋንቋ መመሳሰል የሚለው ከመጣ ታዲያ እምብርቱ ኢትዮጵያ መሬት ላይ ያለው አፋር መሆኑ እየታወቀ እስከ ቀይ ባሕር የዘለቀውን የአፋር ብሔረሰብ ለምን ለኤርትራ አሳልፋችሁ ሰጣችሁ ቢባሉ የሚሰጡት ምላሽ አይኖርም" ሲሉ ጽፈዋል።

ፊያሜታ ጋዜጣ ታህሳስ 15 ቀን 1990 ዓም ገጽ 5 "የህወሓት/ማሌሊት ኢሕአዴግ መሪዎች አዲስ አበባ ገብተው ቤተ መንግሥት ከተቆጣጠሩ በኋላ ወልቃይቶች በጎንደር በአዲስ አበባ እየሰበሰቡ ወልቃይት የትግራይ ክፍለ ሀገር እንደነበረ እንዲመሰክሩ ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ የሞከሩበት ጊዜም ነበር። ይሁን እንጂ ወልቃይት አገሩን አሳልፎ የሰጠ ማንም አልነበረም። ለወደፊቱም አይኖርም። አንድ ጊዜ አቶ መለስ ዜናዊ ለአንድ የወልቃይት ሰው ወልቃይት ትግራይ ነው አይደልም? ብሎ ቢጠይቅ አዩ ጌታዬ እርስዎ እንደሚሉት እኛ እንፈርም ነበር ነገር ግን የማይፈርም ሰው አለን እሱም ተከዜ ነው። ተከዜ ወንዝ ባይኖር ኖሮ ነበረ ሲል መልስ ሰጡ" ሲሉ ጽፈዋል።

ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም "ኢሕአዴግ ፊርሞና አጽድቆ ያወጣውን ቻርተር በመጣስ አማርኛን አፍ መፍቻቸው ያደረጉ ጎንደሬዎችን

መሬት ቀርሶ ለክልል 1 መስጠቱ በታሪክም በሕግም ፊት አጠያያቂ ነው። ከተከዜ ጀምሮ ደቡብ እስከ በሽሎና ጠፋን ወንዞች በተዘረጋው ምድር ላይ ያሉት ወረዳዎች ሕዝብ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው። ከትግራይ ጋር በተከዜ ወንዝ ድልድይነት ጎረቤት ስለሆኑ ወዲያና ወዲህ ማዶ ያለው የአማራና የትግራይ ሕዝብ አንዱ የሌላውን ቋንቋ ይናገራል። የአማርኛ ቃላት ደግሞ ቢያንስ 80 በመቶ ተመሳሳይ በመሆናቸው መናገሩ አዳጋች አይሆንባቸውም።"

"ይልቁንም የወልቃይት የጠገዴና የጠለምት መዘጋዎች ጥጥ ስለሚያመርቱ ብዙ የትግራይ ተወላጆች በጥጥ ለቀማ ወቅት በየዓመቱ ወደዚህ መዘጋዎች ይመጣሉ።አማሮች ከእነሱ ጋር ለመግባባት ሲሉ ትግርኛውን ይጠቀሙበታል። ከእንግዶቹም መካከል እዚያው ሚስት እያገቡ የሚቀሩት ጥቂት ስላላይደሉ ሀገሬው ትግርኛውን ለማሻሻል ሲል ከእነርሱ ጋር በትግርኛ መነጋገር በማዘውተሩ ለወልቃይትና ለጠለምት አካባቢዎች ትግርኛ እንደ 2ኛ ቋንቋ ሆኖአል ማለት ይቻላል። ወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ወይም ሁመራ በአክሱም በላስታው ዛጉዬ በሸዋ ሆነ በጎንደር ዘመነ መንግሥት አንድም ጊዜ የትግራይ ግዛት አካል ወይም ገባር የሆነበት የታሪክ ወቅት የለም" ሲሉ ጽፈዋል።

በውጩ ዓለም በተለይ በሐዋርያና በጋፋት ጋዜጣ በሌሎችም መጽሔቶች እንዲሁም በጉግሣ መጽሔት በመጽሐፍትም ብዙ መጣጥፍ ወጥቶአል። ክቡር አቶ ታየ ረታ፣ሌላው ቢቀር ከመንደርዎ ይታተም የነበረው ሞረሽ መጽሔት ያወጣውን ጹሑፍ ረሱት? መጽሔቱ ሚኒሶታ ይታተም ነበረ። ጹሁፍን ያገኘው አዲስ አበባ ይታተም የነበረ ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም የወጣውን ጹሑፍ አላነበቡም? ልጥቀስ።

<u>ሞረሽ መጽሔት</u> ቅጽ 3 ቁጥር 2 1987 ዓም ገጽ 13 "ይህ በእንዲህ እንዳለ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ከወገራና ከከምከም ጋር የታወቁ የአማርኛ ዘፈን፣ ውዝዋዜ፣ለቅሶ፣ወዮታ ፍከራ ቀረርቶ፣ሽለላ እና እንጉርጉሮ መፈለቂያ ቦታዎች ናቸው። የጎንደር ዘፈን ተብሎ በፋሲለደስ ኪነት የሚቀርበው ዘፈን እስክስታና ውዝዋዜ አብዛኛው ከነዚህ ወረዳዎች የመነጨ ነው። ይህ ሕዝብ በትግርኛ መዝፈን፣መወዛወዝ እስክታ መውረድ ወዮ ማለት መፈከር ማቅራራት ማንጎራጎር ከቶ አይችልም" ሲል የጻፈውን ቀንጭቤ አቅርቤአለሁ። ጎንደሮች እንዲም ወልቃይት ሁመራ ጠገዴና ጠለምት ወደ ትግሬ መከለሉን አንቀበልም። የወልቃይት ተወላጆች ወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት የትግራይ ነው ብለው አያምኑም።

ክቡር ቀኛቀዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል የተባሉ አንድ አባት የተናገሩትን ታሪክ ከዚህ ላይ ልጥቀስ። ወያኔዎች አንዴ ከቤታቸው ሄዱ። ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ደግሞ ከቤታቸው የቅዱስ ሚካኤል ጸበል አዘጋጅተው እንግዳ እያስተናገዱ ናቸው። ታዲያ ወያኔዎች ከግቢያቸው ገቡና "ጌታው ቀኛዝማችን ጥራልን" ብለው አንድ ሰው ላኩ። ያ የተላከው ሰውም ወደ ክቡር ቀኛዝማች ጠጋ ብሎ "ወያኔዎች ከውጭ ይጠሩዎታል" ሲያቸው ክቡር



ቀኛዝማች "ግቡ የቅዱስ ሚካኤል ፀበል ቅመሱ በላቸው" አሉ። ወያኔዎች መልዕክቱ ሲደርሳቸው ቤት ገቡና ከበሉና ከጠጡ በኋላ እርሳቸውን ሊጠይቋቸው እንደሚፈልጉ ነገሩአቸው። ለውይይቱ ከተስማሙ በኋላ ወያኔዎች "ጌታው ቀኛዝማች ታሪክ ልንጠይቅዎ ነው የመጣነው" ይሏቸዋል።
ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እኔን ታሪክ ልትጠይቁኝ" ሲሉ ወያኔዎች "አዎ" አሉ። ክቡር ቀኛዝማች ገብሩም "የኢትዮጵያን ታሪክ ከሆነ ምን ችግር አለው" ሲሉ ወያኔዎች አይደለም ልንጠይቅዎ የመጣነው። ወልቃይት የትግራይ ግዛት ነው ይህን ያውቃሉ" ሲሉአቸው ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል "በል እስክርቢቶና ወረቀት አምጣ ጻፉ። አያቴ በ88 ዓመታቸው ሞቱ፣አባቴ ደግሞ በ85 ዓመታቸው ሞቱ" እያሉ መናገር ሲጀምሩ ወያኔዎች "አይ ጌታው ቀኛዝማች እኛ እኮ የፈለግነው ወልቃይት የትግራይ ግዛት መሆኑን ይንገሩን ነው ያልን" ሲሉ ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እኮ ስማ ልትደርስበት አይደለም እንዴ እኔ ደግሞ 82 ዓመቴ ነው ይህን ደምርና ንገረኝ" አሉት።

ወያኔው "ይህማ 255 ዓመት ይሆናል" ይላቸዋል። ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እንግዲያውስ ልጆቼ በነዚህ ዓመታት ውስጥ ወልቃይት በትግራይ አለመተዳደሯን እናውቃለን። ወልቃይት ሲተዳደር የነበረው በበጌምድ ግዛት ሁኖ ነው። ሰው እሺ ቢል እምቢል የሚለው ተከዜ ወንዝ ደንበራችን ሁኖ በጉርብትና በመረዳዳት በግቢና በመተዛዘን አብረን መኖራችን ልክ ነው ይህ የታሪካችን አንዱ ገጽታ መሆኑን እናገራለሁ" ብለው እንቅጩን ሲነግሩአቸው ወያኔዎች ደህና እደሩ ሳይሉ ከቤታቸው ወጥተው ሐደዋል።



ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል

ስሜን አውራጃ ውስጥ ደግሞ አንድ አባት የተናገሩት ታሪክ ይህ ነው:: ፊታውራሪ ያይኔ ------ የተባሉትን አባት ወያኔ ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር:: የጥያቄው ፍሬ ነገር ከዚህ የሚከተለው ነው "ፊታውራሪ እንኳን የጠለምትን ታሪክ ቀርቶ የኢትዮጵያን ታሪክ ያውቃሉ:: ባለቤትዎ የትግራይ ተወላጅ ናቸው:: ስለዚህ ጠለምትና ጠገዴ ሰቲት ሁመራ የትግሬ መሆኑን ያውቃሉ አይደል?" ብለው ሲጠይቋቸው ፊታውራሪ ያይኔ "የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ መሆኑን ልክ ነው አውቃለሁ:: አማራና ትግሬም ተጋብቶ መኖር የጀመረው ቀድሞ እንጂ በእኛ ጊዜ የተጀመረ አይደለም:: እኛ ወልቃይት ጠለምትና ጠገዴም የትግራይ ነው እንበል ነገር ግን የማይስማማ አንድ አለ" ሲሉአቸው ወያኔዎች "እርሱ ማነው የማይቀበል ብለው ሰውየውን ለማወቅ ሲቋምጡ ፊታሪራሪ ያይኔ፣ ከበጌምድር ግማሹ የትግራይ ግዛት ነበር ብሎ የማይቀበለውማ ተክዜ ነው:: ስለዚህ እኛ የምናውቀው እነዚህ ቦታዎች የበጌምድር ግዛት እንጅ የትግራይ ግዛት ሁነው አያውቁም" ብለው ነግረዋቸዋል:: እኒህ አዛውንት ባይገደሉም ሌሎች በዚህ ዓይነት ታሪክ እየተናገሩ የተገደሉና የታሰሩ ቁጥር ብዙ ሺህዎች ናቸው:: ከወያኔ ያመለጡ የነዚህ ወረዳዎች ተወላጆች ብዙ ጠቃሚ ምክር ጥለውልን አልፈዋል:: ከሱዳን ወደ አሜሪካ እንዲሰደዱ ያደረጉአቸው መላከ ሰላም ሲሰይ አየለም እንዲሁ ታሪክ ትተውል አልፈዋል::





መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 12" መቸም ኢትዮጵያ ከቀናች ጀምሮ ጎንደርና ትግራይ ተከዜ ወንዝ ነው ደንበራቸው:: አሁን ግን ወልቃይት የልማት አገር በመሆኑ ወልቃይትን ጠገዴን ጠለምትን የትግራይ ነው ብለው አወጁበት:: ከጥንት ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ወልቃይት ሆነ ጠገዴ ወይም ጠለምት የትግራይ ሆኖ አያውቅም:: በኃይላቸውና በጦራቸው ብዛት የሚታወቁት አጤ ዮሐንስ እንኳን የትግራይ ነው ብለው አልወሰዱትም እስከ ትናንት ድረስ ጎንደርና ትግራይ ተከዜ ወንዝ ነበር ደንበራቸው:: እኛ በምናውቀው የወልቃይት ሰው ውል ሲዋዋል ሲጻጻፍ ማንኛውንም ነገር በአማርኛ ቋንቋ ነው ሀዘን ደስታውን በአማርኛ ነው የሚገልጸው:: እርግጥ ኩታ ገጠም በመሆኑ ከጊዜ ብዛት ትግርኛ ይናገር ይሆናል:: አሁን ሱዳን ውስጥ ተሰዶ ያለ የአማራና የትግሬ ሰው ሱዳንኛ ይናገራሉ:: ቋንቋቸውን ስለተናገሩ ሱዳናዊ ሆኑ ማለት ግን አይደለም" ይሉና " ሕዝቡ በጣም አዘነ ከዚያም ከፋኝ የሚል ወገን ሲዋጋ ቆይቶ የሞተው ሞቶ ሁለት ሽህ የሚሆን ሰው ታሰረ ይሙቱ ይኑሩ የሚያውቅ የለም እንጂ ያውም ምህረት ይደረጋል ብለዋቸው በምህረት ከገቡ በኋላ አሰሯቸው በዓለም ህግ መሰረት ምህረት ከተባለ በኋላ ሰው ታስሮ የትም አይጣልም:: አሁን እነዚህ ሰዎች የት እንዳሉ የሚያውቅ የለም"::

"ጥያቄ ወያኔ የአማራ ሕዝብ ነፍጠኛና ወራሪ ነው ብሎ ያምናል ምናልባት የወልቃይትን መሬት በወረራ የተወሰደብን ነው ቢሉስ? መልስ የጎንደር ሰው ተከዜን ተሻግሮ የወረረ ከጥንት ጀምሮ አይገኝም:: ወልቃይት ከጥንትም ነገሥታቱና ባላባቱ ዝሆንና አንበሳ ያድኑበት የነበረ ለም ቦታ ነው:: የጎንደር ሰው ከውጭ ወራሪ ጋር እየተዋጋ ሀገሩን አስከብሮ የነበረ ነው:: የወልቃይትን መሬት ለመውረር የመጡትን ከጥንትም ተዋግቶ በደሙ ያቆየው እነ ደጃዝማች ነሹ የደሙበት ሀገር እኮ ነው:: ጥያቄ በቦታው ግን ቀድሞም የትግራይ ተወላጆች የሰሊጥ እርሻ ጭምር እንደነበራቸው የቅብ ጊዜ ትዝታ ነው ይሄን እንዴት ያዩታል:: መልስ መልዓከ ሰላም በቅድሚያ ማወቅ የሚያስፈልገው ሁለቱ ሕዝቦች አብረው የኖሩ በጋብቻም የተሳሰሩ ናቸው:: ከትግራይ መጥተው ከወልቃይት ጋር የተጋቡ ብዙ ናቸው:: አዎ በልማቱ ላይ የትግራይ ሰዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ:: እንዲያውም በትራክትር ነበር ያንን ሁሉ መሬት ያለሙት ይሄ ታዲያ የጎንደር ሰው የዋህ ነው ምንም አይልም:: አንተ የውጭ ሰው ነህና ግብር ትከፍላለህ ያላቸው ሰው የለም" ሲሉ መልሰዋል::

ክቡር አቶ ታየ ረታ ከዚህ በላይ የተነገሩት ታሪኮች ለቅምሻ ያክል እንጂ ብዙ የጎንደር ተወላጆች የወያኔን ካርታ የማይቀበሉ ብዙ ናቸው:: ብዙ ጹሑፎች ተጽፈዋል:: ሌላው ይቅር እኔ እንኳን ባቅሚቴይቱ የጻፍኩት አለ:: እራሴን ፀሐፊ ነኝ ለማለት ፈልጌ ሳይሆ ብዙ ጊዜ በወልቃይት ዙሪያ እጽፋለሁ:: በተለይም ወያኔ የትግራይን ምሁራን ወልቃይት የትግሬ ነው ብላችሁ ጻፉ ብሎ በማዘዙ አንዳንድ ግለሰቦች የወያኔን ስሜት እንጸባረቁ:: በተለይ አቶ

ግደይ በላይ በጻፉት መጽሐፍ ላይ ትክክል አለመሆናቸውን አስረግጬ ታሪክ እየጠቀስኩ ጽፌአለሁ::

አማረ አፈለ ብሻው ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 42 "ወልቃይት ጠገዴ፥ጠለምት የጎንደር አካል እንጂ ትግራይ አይደለም:: ወያኔ ቀደም ብሎ ሲመሰረት የትግራይን ችግር ለመቅረፍ ከጎረቤት ክፍለ ሀገራት ለም መሬትና የውጭ መገናኛ የባህር በር ለራሱ ለማድረግ ማሰቡ አልቀረም:: በጎንደር ወልቃይትንና ጠገዴን ጠለምትን ከወሎ ሰቆጣን ሌሎችንም ከአፋር አስተዳደር አሰብን ጨምሮ ሱዳን የሚያስገባ በዓለም ላይ የሚያስዋኝ ባህር ድንበር ከልሎ ተነስቶ ነበር:: ሳሉ ደስ አይበላቸው ሲሞቱ ነፍሳቸው አትማር ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ወደ ሥልጣን ከመጡ ጀምሮ የአፋር የአሰብ ወደ ትግራይ መከለል ሲቀር ሌሎችን ለም መሬቶች ለትግራይ ለማድረግ ታጥቆ ተነሳ::"

"ከፍ ተብሎ የተጠቀሰው የሁለቱ አባቶች ደብዳቤ በጥሞና ሳስተዋለው ትንቢት ነው:: ይህ ወገኔ ከማያውቀው ጋር ሁን ተባለ በማለት ያኮረፉ አካባቢው በጎበዝ አለቃ የሚታዘዙ ፋኖዎች ዛሬ ትግላቸውን ከአገር ቤት ውጭ አገር አስፋፍተዋል:: ለዚህም ነው ንግርት ያለው ደብዳቤ ነው ያልኩት:: ወያኔ ከታሪክ ያገኘው አለመሆኑን ቀደም የወያኔ አባል የነበሩት አቶ አረጋዊ በርሄ ጀርመን በ1991 ዓም ተጠይቀው መሳሳታቸውን ተናግረዋል:: ጀርመን የሚታተም መጽሔት ራዕይ ታህሳስ 1992 ዓም ገጽ 2 የዛሬ ዓመት እዚሁ ፍራንክ ፈርት ከተማ ተካሂዶ በነበረ ሌላ ስብሰባ ይኸው ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦላቸው ጫካ እያለን የሠራነው ስህተት ነው ነበር ያሉት ሲል ጽፏል:: ከወያኔ ጋር ሁነው የታገሉት በመጀመሪያው ጀምሮ ይህን እቅድ ያወጡት ሰዎች ተሳስተናል አይደለም የሚሉት" ሲል ተጽፎ ነበር:: ይህ ታሪክ በመሆኑ ሊካድ አይችልም::

የጎንደር ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድምጻውያኑ በድምጻቸው ሁመራ የትግሬ አለመሆኑን ደግመው ደጋግመው እያሳሰቡ ናቸው:: የጎንደር ባህላዊ ድምጻዊ ሴት ከወንድ ስለ ሁመራ ያልዘፈነ የለም:: ትናንት አዚመዋል ነገም ያዜማሉ ከነገ ወዲያም፥ከዚያ ወዲያም ያዜማሉ:: ይርጋ ዱባለ፥እርጎዬ ሻምበል በላይነህና ሌሎችም ድምጻውያን አዚመዋል:: ሌላው ቢቀር ድምጻዊ የፋሲል ደምወዝ "አለ ነገር" የሚለውን ዘፈን በጥሞና ማዳመጥ መልካም ይመስለኛል::

"አለ ነገር ዘንድሮ አለ ነገር
በጎንደር በጎጃም በመሬ በሸዋ ዘንድሮ አለነገር
አረሱት ይሉኛል የሁመራን መሬት
የአርማጭሆን የመተማን መሬት
ያውም የኛን እጣ
እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ"



የሚለው ዘፈን የሚረሳ አይደለም:: ይህን ዘፈን የሰሙ ስለ ሁመራ ወደ ትግሬ መከለል ያንገበጋቸው ተቀማችነታቸው አሜሪካ የሆኑ ,ትዮጵያዊት! ድምጻዊ ፋሲል ደመወዝን ካነጋገሩ በኋላ በዲቪዲ ተባዝቶ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት እንዲዳረስ አድርገዋል:: እርሳቸው የአገር ጉዳይ ሁኖባቸው እንጂ ዘፈን ገዝቶ አሳትሞ በተለይ እየተቀዳ በሚሸጥበት ዓለም ሊያተርፉ ፈልገው አይመስለኝም::

ይህን ሲያደርጉ ግን ወያኔ እንደሚያወራው ፀረ ትግሬ ሁነው አይደለም:: የትግራይ ልጆች ሁሌም ጎንደር ይኖራሉ:: ሁመራን ከሌሎች ጎንደሬዎች ጋር ሁነው አርሰው ሲበሉ የከለከላቸው አልነበረም ለወደፊቱም አብረን አርሰን እንበላም የሚል የለም:: ነገር ግን በአስተዳደር ወደ ትግሬ አይከለል ይህ ችግር ይፈጥራል በማለት እንጂ? የክቡር አቶ ታየ ንግግር የአፍ ወለምታ አይደለም:: ለ17 ዓመታት በቀልድ ሲነገር የነበረ ነው:: የመሀል አገር ሰዎች "ወያኔን አሳልፋችሁ የሰደዳችሁ ጎንደሬዎች ናችሁ" እያሉ ሲናገሩ ይደመጡ ነበር:: ጎንደርማ ወያኔን ገትሮ ይዞ ነበር:: ተባባሪ አልደረሰለት ብሎ እንጂ? እንዲህ ብለው ስለተናገሩ ጎንደሬዎች ብስጭት ብለው በወያኔ ላይ እንዲነሱ ለማድረግ ታስቦ ከሆነ የሚሰራ አይመስለኝም:: ወያኔን ለመጣል እንቱም ሌሎችም ባንድ ሲቆም ብቻ ነው::

አቶ ታየ ረታ "ደንበሩን ለማየት ስንሔድ አሳሰራ ያሉት የአርማጭሆ ሽፍቶች ነበሩ" አሉ:: የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የኢትዮጵያን ዳር ደንበር ማስጠበቅ ነበረበት ነገር ግን ዝም ስላለ የአርማጭሆ ሕዝብ በራሱ መሳሪያ ደንበር ጠባቂ ሁኖ በማስከበሩ መንግሥት" ሽፍታ" ይላቸው ነበር:: እንኳን በዚያን ወቅት ዛሬም ሳይቀር ያጤው ባለሥልጣኖች ይህን" ሽፍታ" የሚሉትን ቃል ከጭንቅላታቸው ሊፋቅላቸው አልቻለም:: አቶ ታየ ረታ ሰኔ 10 ቀን 2 ሺህ ዓም ተናግረውታል:: እኔ "አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን ሌሎችም ሽፍቶች አልነበሩም" የሚል ሰናገር:: አቶ ታየ ረታ "ይቅርታ ሽፍታ ማለቴ አገር ጠባቂ ማለቴ ነው! ለአንድ መቶ ዓመት ደንበራቸውን የጠበቁ መሆናቸውን አውቃለሁ:: ለምሳሌ አሁን የጠቀስከውን ሰው ስም አልተመዘገበም" ሲሉ ተናገሩ:: ሕዝብን የሚንቅ እንደናንተ ያለ በሥልጣን እያለ ተቀምጠው ሌሎች እንዴት በታሪክ ሊታወቁ ይችላሉ? አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን ሌሎችም ለደንበራቸው ሲሉ ደማቸውን አፍሰዋል::
"ረግ ረግ ይላል ሲረግጡት መሬቱ
ገብሬ ተወልደ መድንህ የወደቀበቱ"
በማለት የአርማጭሆ ሕዝብ የሚያሞግሳቸውን ጀግና እንሆ ሽፍታ ተባሉ? ዳር ደንበሩን የሚያስከብር ወንድ ሽፍታ ሲባል እንግዲህ ወያኔ በዚህ ገብቶ ሻምበል ቻሌን ገድላችኋል በማለት እንሆ ከ200 በላይ የአርማጭሆ ሕዝብ ታስሮአል:: "ስም ይወጣል ከቤት ይከተላል ጎረቤት" ይባላል:: ሽፍታ ማለት እኔን በሚገባኝ በጎንደር አማርኛ የግለሰብ ንብረት ሆነ የመንግሥት ንብረት ዘርፎ የሚበላ ዓላማ የሌለው ለገንዘብ ሲል ያገኘውን የሚገድልና የሚዘርፍ ነው:: ቀደም ሆነ አሁን በቅርቡ የአርማጭሆ ሕዝብ የሞቱት አገራቸው በርሃው አንበሳና ቀጭኔ ነበር ዝሆን የሚያድኑበት መሬታቸውን ሱዳን ተሻግሮ ሲያርስባቸው ማረስ

የለባችሁም ብለው የተዋጉ ናቸው:: በአርማጭሆ ሕዝብ ላይ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና የወያኔ መንግሥት ልዩነት የላቸውም:: የወያኔ መንግሥት የአርማጭሆን ጀግኖች ሽፍታ ማለት ብቻ ሳይሆን ሰላም ነሾች ብሎ ፈርጆአቸዋል:: የሱዳን ወታደር የአርማጭሆን ሆነ ሌላውን ሕዝብ ንብረት ዘርፎ ሲወስድና ሲያስር የአካባቢው ሕዝብ ተደራጅቶ የታሰሩበትን ሰዎች ለማስፈታት ለድርድር አመች እንዲሆን ከሱዳን መሬት ገብቶ ሕዝብ ማርኮ በማምጣቱ ምክንያት የወያኔን ጦር መርተው ሻምበል ቻሌ አለሙ፤ ወደ ሕዝባዊው ሠራዊት ዘመቱ:: በዚህ ጦርነት ተገደሉ:: ወያኔ ተበሳጨ? የታሰሩትን ኢትዮጵያዊ ሳያስፈታ የተማረኩትን ሱዳኖች ለማስፈታት ያዘመተው ሰራዊት ተመታበት::

ክቡር አቶ ታየ ረታ "እኔ ደስ የሚለኝ ስሜንና በጌምድር ሲባል ነው" ብለዋል:: በእርግጥ አልፈርድም እርስዎ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣን ሲሆኑ ዛሬም ያንኑ አረሱትም:: ይህን የከፋፍለህ ግዛው ተግባር ነበር አሁን ግን የለም:: በእርግጥ ወቅትና ጊዜ እየፈለገ ወያኔ በበጌምድርና በስሜን መካከል ሳይሆን በናትና በልጅ በባልና በሚስት የሚገባ መሆኑ አይዘነጋም:: ቢሆንም ደርግ ግንቦት 1966 ዓም ቅድሚያ ካስተካከለው ዋናው አንዱ ስሜንና በጌምድር የሚለውን ጎንደር ብሎ አስቀርቶታል:: ይህ ስሜንና በጌምድር ብሎ የአጤው መንግሥት ሊያይቶ ለመግዛት የተጠቀሙበት ስልት ሲሆን እርስዎ ዛሬ እንኳን ከ40 ዓመት በኋላ ሊረሱት አልፈለጉም:: ለወዲፊቱ አንድ ጎንደር እንጂ ስሜንና በጌምድር የሚለውን ትውልዱ አይፈልገውም:: ነገር ግን "እኔ ደስ የሚለኝ ስሜንና በጌምድር ሲባል ነው" የሚለውን ረሳ ያድርጉት ለወደፊቱ አይሰራም::

"አቶ መለስ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን አይሰጥም" ብለው የተከበሩ አቶ ታየ ተናገሩ:: ክቡር ሆይ! ምነው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር መሬት አልሰጡም? በዚሁ ቀን እርስዎ የኢትዮጵያን ገፀ ምድር (ካርታ) እየነኩ "እኔ አሰብን አለቅም አሰብ የኔ ነው" ሲሉ የተናሩት አሰብን ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ለኤርትራ የሰጡ ስለሆኑ አይደለም እንዴ? ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አገራዊ ፍቅር ስሜት የላቸውም:: የአገር ፍቅር የሚባል እንኳን ሊጠጋቸው ቀርቶ በአካባቢያቸው አልፎ አልሄደም:: የአገር ፍቅር ቢኖራቸውማ ኑሮ ሌላውን ሁሉ ይተውት እንዴት የአባታቸውን አገር ከትግራይ ቆርሰው ለናታቸው አገር ለኤርትራ ሰጡ? ይህን ያደረጉ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ለሱዳን 1600 ሚትር መሬት አይሰጡም አይባሉም ይሰጣሉ:: አሁንም በደንበር ያሉ ሕዝቦች እነሱ እየሞቱ ያዘገዩት ይሁን እንጂ ቀርቷል ማለት አይደለም::

በሰማይ የሚጓዝ ጉም አይዘገንም
አቶ መለስ ዜናዊ አይታመኑም::

ርዕሠ ብሔር አቶ መለስን ማመን ባለት ጉምን እንደ መዝገን ማለት ይሆናል:: ግራዝማች ስንታየሁ ታምራት <u>ለሰዎች ምን ይላሉ ፕሮግራም</u> አዘጋጆች በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 5 "በቴዎድሮስ በነአጤ ዮሐንስ

በምዬ ምኒልክ በኃይለ ሥላሴ በአንድ ላይ ነበርን



ከፉ ቀን መጣና አቆራረጠን
እርግብና ዋኔ ከቤት ስለዋሉ
ድንቢጦች ተነስተው ወፍ ነን ወፍ ነን አሉ
ወልቃይት ጠገዴ እርሻ ማረስ ያውቃል
ጥቁር ነጭ አይለይም አንድ አርጎ ይወቃል
እሰማ ነበረ አባቴ ሲናገር
በሕይወቴ አላይም ወሰኔ ሲደፈር
ተቀልዶም አያውቅም በሚስትና ባገር
ጀግና እንቅልፍም የለው ተኝቶም አያድር
ጫቆና ሰራባ አዳኘ አገር ሁሉ
ቋራና መተማ በሙሉ
ጓንግን ከተከዜ አንገረብ ወንዞችን
ማን ይሻገረዋል ያለፈታዳችን
መግቢያና መውጫውን መልካውን ማያውቁ
እንዋኛለን ብለው ገብተው እንዳያልቁ
ትዕዛዝ ይሰጣቸው እንዲጠንቀቁ" ሲሉ ጽፈዋል::



መልዓከ ሰላም ሲሰይ አየለ!

# ተመልካች

**ለዝግጅት ክፍሉ፡-** ሰላም ጤና ይስጥልን በኢትዮጵያ የምትገኙ የነፃው ፕሬስ አዘጋጆች፤ ነፃው ፕሬስ በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሕዝቡን ጩኸት ከዳር እስከ ዳር ለማሰማት ያደረጋችሁትን ጥረት በአድናቆት እናደንቃለን። ሆኖም ከሀገሩ ርቀትና በመንግሥት ተፅዕኖ ምክንያት፤ በግጠራቀ ኢትዮጵያ ዛሬም ድረስ አስታዋሽ አጥተው በየእስር ቤቱ የሚማቀቁ ወገኖቻችንን ጩኸት ለማሰማት አልተቻላችሁም። ይህ በዚህ ክፍለ ዘመን 'ዴሞክራሲ' ቢባል ለማመን አዳጋች የሆነው አሰቃቂ ተግባር ዛሬም በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ነው። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የቀድሞ የጎንደር ወረዳዎች በነበሩት በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በሁመራ እና በጠለምት ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ እስከ ዛሬ መንግሥት እንዲያውቀው ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም መንግሥት የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለ ጉዳዩ የሕዝቡን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው ምንም ዓይነት መፍትሄ አላስገኘልንም። በመሆኑም ይህን ለመመልከት በውጭው ዓለም ከምንጋለጠች በፊት፤ በነፃው ፕሬስ አማካኝነት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው እንዲደረግልን በማለት የደብዳቤውን ኮፒ ከዚህ ጋር ልከናል። በአንገታም በኩል ያስመታከትና ያስማቀረፕ በአካባቢው የሚደርሰውን ግፍ እንድታጋልጡልን በሚሰቃዩት ወገኖቻችን ስም እንማጸናለን።

## መልስ ያጣ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ዕንባ

**ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

ይህ አቤቱታ የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ሊሆን የሚገባው ሕዝብ ኃይልና ሥልጣኑን በተነጠቀበት፣ ብሶትና በደል በመላው ኢትዮጵያ በተንሰራፋበት፣ ፍትህና ርትዕ እስከባራ ባልተገኘበት በዚህ ሰዓት ከምድረ ወልቃይት እያስተጋባ ያለውን የብዙ ሺህ ሕዝብ ዕንባ ወገን ለሆነው ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳወቅ በጣዕር ወተያዙ ዜጎች ስም የተዘጋጀ መልዕክት ነው።

እነሆ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በወልቃይት ጠገዴ ከርሰ ምድር በጨለማ የተጓደሉ፣ በቃሬጥር ቀዝና ሰው ሰራሽ በሆኑ ጉድጓዶች ውስጥ የታሰሩ፣ የዱር አራዊትን ያህል እንኳ ጩኸታቸውን ለወገናቸው ማሰማት የተሳናቸው፣ እናንት ድምጻችንን አስተጋቡልን ሲሉ የሚማጸኑ በርካታ ወገኖች አሉ።

በደሉ ለዓለምም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታፍኖ የሚካሄደውን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ወገኖች ሆይ ታውቃላችሁን?

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥርዓቱ የደረሰበትን ጥቃትና ውድቀት፣ እንዲሁም በቃይና መከራ ስኖ የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪዎች እንደሚገኙበትም ኢትዮጵያዊ ስንጋፋውና ስንቃወመው ቆይተናል። በወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ላይ የደረሰውንና የሚደርሰውን የግፍ ግፍ፣ ልጅ ከሶቱን ለእናቱ እንደሚያወያይ፣ እናት ለሆነችው ሃገሩ የድም ዕንባውን እያደረሰ ብሶቱን ይገልጻል። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ የአብራክ ክፋይ የሆንን እኛ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ እንዲሁም በሌሎች ዓለማት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በዚያች የትውልድ ቀዬ እና ምድር የሚፈስሰውን ደምና ዕንባ የሚታተተ ሮሮ በመከታተል ልናደርግ የምንችለውን ሁሉ ለ[illegible] ብንቆይም የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ በደል «በጨኸ[illegible] መካከል ተወጦ ያልተሰማ ጩኸት» ሆኖ ስላገኘነው [illegible] ለሌው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይወቀው በማለት ይህን አቤ[illegible] ለማቅረብ ተገድደናል።

[illegible] አላደረገምን? በኢትዮጵያ [illegible] ዘመናት ሁሉ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ የ[illegible] ያወንትቅ ችግር ከማንም በላይ ተካፍሏል። የውጭ ኃይ[illegible] ወረራ በመቋቋም በአርበኝነት ብዙ አንቱ የሚባሉ ጀግ[illegible] አፍርቷል። በከተም ሆነ በደግ ኢትዮጵያዊነትን ለጥ[illegible] ሆነ ለከፋፋይ መርዘኛ ሃሳብ ክቶውንም ለድርድር አላቀ[illegible] በማለት በብዙ የግፍ ጠባቆች ገና በጠዋቱ ጥርስ የተነከ[illegible] መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋልን?

[illegible] ተጋድሎ ሐርነት ሕዝቢ ትግራይ ([illegible] የታላቋ ትግራይ ትግርኝ ሕልሙን እውን ለማ[illegible] የተፈጥሮ ድንበር የሆነውን የተከዜን ወንዝ በማ[illegible] አካባቢውን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ጥረት ማድረግ የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ትናንት በረሃ እያለ ነበር። እጅግ ለም የሆኑትን የሰሜን ምዕራብ ጎንደር ክፍለ ሃገር ግዛት (ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሰቲት ሁመራ እንዲሁም ጠለምት ወረዳዎች) በማንአህሉኝነት ነጥቆ ለመውሰድ ዘመቻ በከፈተበት ጊዜ ሁሉ ሕዝብ ለሃገሩ አንድነት ወገና የጠላቱ ዘረኝነት ሰሜትን በመቃወም ከልጅ እስከ አዋቂ ተከላካሉ አሳፍር ሲመልሳቸው ቆይቷል።

[illegible] ከፍተኛ [illegible]።

ይህ ሕዝብ ለወያኔዎች መስፋፋት ብርቱ እንቅፋት በመሆን ለብዙ ዓመታት መፈናፈኛ አሳጥቶአቸዋል። ለዚህም ነው ታዲያ የወልቃይትና ጠገዴ ከርሰ ምድር የደም ቋምበቀል የሚዘንብበት፣ ትውልድ እንደአዝመራ የሚታጨድበት። [illegible] በዚህ ሕዝብና ትውልድ ላይ አሰቃቂ መዓት አውርደውበታል።

የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የተናገሯቸውን ብዙዎች የሚያስ ታውሱት ነው። ነገር ግን ምንስ የሰው ልጅ በበቀል ሊያምን፣ ጉልበተኛው ጉልበት የሌለውን... ጊዜ ይሰጠው ጊዜ የከዳውን፣ ጠመንጃ የያዘ አቅመ ደካማውን እስት ፀአለት ባልተቋረጡ የጥላቻ በትሮች ሰበዓዊ ፍጡራንን ማሰቃየትና ማጥፋት ከአስር ዓመታት በላይ እንደምን ሳይቋረጥ ሊቀጥል ይችላል?

በመሠረቱ ወያኔ/ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ከወጣና ሕዝቦች ሁሉ ለሰላምና መረጋጋት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ በተሳለፈው የምህረት አዋጅ የወልቃይትና ጠገዴ አርበኛ ሕዝብ አዋጁን አምኖና ምህረቱን ከልቡ ተቀብሎ መሣሪያውን በማስረከብ ሰላማዊ ሕይወቱን ለመምራት ወደ ተለመደው የግብርና ኑሮው ተመልሶ ነበር። ይሁን እንጂ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ያተረፈው ነገር ከወጥመድ እንደገባ የዱር አውሬ መከራን መቀበልና መቀጥቀጥን ነው።

[illegible]

በተጫማሪ [illegible] የታሪክ ምስክር የሆኑ አባቶች ከጠቶ ቀሪው በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው ትውልድና ሌላውም ሕዝብ ለተፈለገው የአካባቢው ንጥቂያ የማይመችና ማንነቱንም አሳወላዳ ስላለ በባንኪራ ስልቶች እንዲሟሸሽ፣ የትውልድ ሂደቱ እንዲመክንና ሥርዓቱ በመረጠለት የትግራይ ክልል ውስጥ እንዲዋጥ ተደርጓል።

ከዚህ ጋር በየጊዜው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የሁመራና የሰቲት ገበሬዎች ከየአካባቢያቸው ተግዘው ወደ ተቆፈሩ የጥልቅ ጉድጓድ እስር ቤቶች እንዲገቡ ተደርጓል። [illegible] ተደርጓል። ከዚህ ያመለጡና የተረፉ ብዙዎች ተሰደዱ፣ ቀሪዎቹም ሰብዕናቸውን አጥተው ጥራሳቸው ተከሳሽተ፤ ከመኖር ይልቅ ለሰመኖርን በሚያስመርጡ ግፎች ከብራቸው ተገፍፎ፣ ከራሱቹ ከልመና ደረጃ እንዲደርሱ ሲደረግ ሌሎች ደግሞ በበሽታ ተጠፍረው የአሊጋ ቁራኛ እንዲሆኑ ተደርጓል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን... ሚስቶች በባሎቻቸው ፊት የሚደፈሩበትን ቅጣት ሳይወድ ተቀብሎ የሚገኘው የወልቃይት እና ጠገዴ ምድር መሆኑን ዓለም ያውቀው ይሆን? ሰውስ ያምነን ይሆን?

እውነቱ ግን ይህ ነው። ነውርን ቢደጋግሙት ያነውራልና፣ ቀበዝ ያሰቀሰበትን፣ እናት ያነባችበትን ትውልድ ዕንባ የተራጨበትን በሙሉ መዘርዘር የሰው ልጆችን ክብር የሚነካ በመሆኑ ጊዜና ታሪክ ይፍረደው እንላለን።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሁመራ እና ጠለምት ወረዳዎች ወገኖችህ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ ሰላማዊ መፍትሔ እንዲያገኝ በማለት ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የሕዝብ አቤቱታ አቅርበን ነበር። እስካሁኑ ድረስ የቂሰጠን መልስ የለም። ጭራሹንም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተላከው ኮፒ በፖስታ ቤቱ በኩል ሶስት ጊዜ መከራ ተደርጎ ተቀባይ ጠፍቶ ተመላሽ ሆኗል። ሆኖም ይሆን በሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ ለመላው የዓለም ኅብረተሰብ፣ መንግሥታትም ሆነ ድርጅቶች ማቅረባችንን እንቀጥላለን!!

በውጭ አገር የወልቃይት እና
ጠገዴ ሕዝብ ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ
ለማንኛውም ጥያቄም ሆነ አስተያየት አድራሻችን
P.O.Box 360983
Columbus, OH 43236- 9997

# የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ አዲሱን ካርታ አልተቀበለውም

ይህንኑ ዓቢይና አንገብጋቢ ችግር መነሻ በማድረግ የሚመለከተውን በር እንኳኳለን ። ስብሰባዎችን ተካፍለናል ። ወረቀቶችን አንብበናል ። ሰው አነጋግረናል ። እናም ወደቢያ ትሩ እንሰፍ ።

ግንቦት 15ቀን 1984 ዓ.ም ታትሞ የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ " ስለብድር ስምምነት " በሚል ርዕሶ ሥር የተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት 13/84 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የተነጋገረባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል ። ምክር ቤቱ በስፋት ከተወያየባቸው አጀንዳ ዎች መካከል የምርጫ ኮሚሽን አሥራ አራቱን የምርጫ ክልሎች ለመጠቆም ይረዳል በማለት ያወጣውን ካርታ ይመለከታል ። በዚህም መሠረት የኢ ትዮጵያ ሶማሊያ ድርጅቶች ለአጀንዳ ያዘቀውን ጉዳይ ምክር ቤቱ በስፋት ከተወያየበት በኋላ የምርጫ ኮሚሽን ክልሎችን በሚመለከት ያወጣው ካርታ ይፋዊ የሆነ ብሔራዊ ካርታ አለመ ሆኑንና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፆ ከሁን በኋላ ከአገልግሎት እንዲ ታገድ ወስኗል ። ከዚህም ጋር በማያ ያገ ካርታው ምክር ቤቱ ሳያየውና ሳይጠቀው የወጣ ከመሆኑም በላይ በአፈጻጸም ላይ አፍራሽ አስተዋጽኦ አበርክቶ በመገኘቱ ከአገልግሎት እን ዲታገድና በምርጫ ኮሚሽኑ በኩል ማስተባበያ እንዲሰጥበትም ትእዛዝ አስተላልፏል ።

ስለአዲሱ ካርታ ያለው እው ነታ ይህን ይምሰል እንጂ የተወካ ዮች ምክር ቤት ውሳኔ ተግባራዊ ምላሽ ሲያገኝ ግን አልተስተዋለም ። ሌላው ቀርቶ ማስተባበያውን ለመስጠ ት እንኳ ፈቃደኛ ሆኖ የተገኘ የለም ። ይኸው የኢህአዴግን ዓላማና እምነት የሚያንፀባርቀው ካርታ ሥራ ላይ ይውል ዘንድ በአንዳንድ ክልሎች ግፊት የመደረጉን ያህል በወልቃይት ጠገዴም ላይ ሁመራን ጨምሮ በክ ልል 1 ሥር (በትግራይ) ለማስገባት ከመስናዶ እንቡጥ እስከተግባራዊ እንቅስቃሴ ድረስ ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል ። በመሠረቱ ብዙሃንም የክልል 1 እንቅስቃሴ እየተባለ ነጋ ጠባ ተጠቅሷል ። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ በበኩሉ በአዲሱ ካርታ እንደ ማይስማማና ተፈጥሮ አደላድላ ከሰ ጠቻው ከጥንቱ ወሰኑ የጎንደር ክልል ውጭ አዲሱን ካርታ ለመቀ በል ፈቃደኛ እንዳልሆነ በተለያየ መድኑና አቀራረብ ራሱን ግልጽ አድ ርጓል ። የተከበረን መንዝ ተሻግሮ ፡ በረሀ አቋርጦ ፡ ግብር እንዲከፍል ፡

ባሻንት እንዲጠይቅና ሌሎችንም ጥያ ቄዎች ለክልል 1 ሹማምንት እንዲያ ቀርብ ሲጠየቅ ሁሉ የሁመራ ፣ የጠለ ምትና የቤቂት ሁመራ ሕዝብ ቅሬታ አልገባውም ማለት አይቻልም «በየ ጊዜው አቋሙን እየገለጸና እየተፈራ ረመ ወደ ሚመለከተው አካል የላካ ቸው ደብዳቤዎች ህያው ማረጋገጫ ዎች ናቸው ።

ሌላው ቢቀር ጥር 30/85 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የጐን ደር ተወላጆች በዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ባደረጉት የጐንደር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ማህበር ስብሰባ ላይ የሁመራ ፣ የወልቃይት ጠገዴና የጠለምት ክልል በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከተሰብሳቢው ተጠይቆ የተሰጠው ምላሽ ከላይ ለማሳየት የሞከርነውን እውነታ ግልጽ ያደርገ ዋል የሚል እምነት አለን ።



በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ ከተነ ሱት ጥያቄዎች መካከል በወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ያለው ፀጥታ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ? አዲሱ ካርታ በክልሉ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል ወይ ? የተሰኙት ጥያቄዎች ይገኙ በታል ። በዚህም መሠረት የልማት ማህበሩ ሊቀመንበር በሰጡት ሥል ታዊ ምላሽ የክልሉን ፀጥታ በተመለ ከተ እስከአሁን በተጨባጭ የሚታ ወቅ ነገር እንደሌለና ሠላም እንዳይ ጠፋ ከመጠበቅ በተር ለጊዜው ሌላ አማራጭ እንደሌለ ያስረዱ ። በሌ ላም በኩል አዲሱን የአስተዳደር ክልል በማስመልከት የማህበሩ ፀሐፊ

ሰሆኑት ለአቶ ፍትሐ አሰ ቀርቦ በሰጡት መልስ የወል ጠገዴ ሕዝብ እስከአሁን ይዞት ውና በሕግ ከሚታወቀው ክልሉ ውጭ አዲሱን ካርታ በል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ፣ በቀ አስተዳደር ክልል (በክልል 1) ይታቀፋል በሚል አንዳንድ ወይም ድርጅቶች የሚያስተጋ ወሬ የማይጨበጥ ተስፋ ዘመግለጥ ለሚመለከተው አካ ቃውሞ ድምፁን ማሰማቱን ሰባው ተሳታፊ አስታውቀዋል

እም ይህን በየሰው አእምሮ የሚጉላላውንና ጦርነት ይካሄ ተብሎ ዘግል ጋዜጣ ሳይቀር ጣቱ ፣ ጋዜጠኞች በሆግ ፊት ርበ ምክንያት የሆነውን ክል ቃሳይ ሁኔታ በተመለከተ የ ከ/ሀገር መልሶ ማቋቋሚያና ማህበር ሊቀመንበርና ፀሐፊ ሲል ለክቡር አቶ መለስ ዜ ኩት ግልጽ ደብዳቤ " . . . ጵያ ድምጽ ሬዲዮ የሽግግሩ ሥት የተወካዮች ምክር ቤት ዮጵያን አስተዳደር በ14 ክ ድቋል ብሎ ያስተላለፈው ሪክ ኮንፈደሬሽል ከተመሠ ጋር የተቀራኘ እንዳልሆነ አለን ። ከሆነ ግን ይህ ንድፍ መንግሥቱ ረቂቅ አካል ሆኖ ዳድቅ ወደ ፊት ለሕዝብ ረጠው ሕገ መንግሥት ጉባኤ ማቅረብ እንዚህን ወ ኞች የትግራይና የጐንደር ካሁን ጀምረው ለፍጅት እ መጋበዝ ነው ከሚባል በ ምክንያትና ትርጉም አይኖረው ጨማሪም በሽግግር መንግሥ ቤት ውስጥ የጐንደር ሕዝ ጠው ተወካይ ባለመኖሩ እ ዳት የምክርንውን ቁስሉንና በማምባር የሚያስረዳለት አ በመሆኑም ከዘንት ዓለም ጀ የውን መብታችንና ታሪካችን የሚመረጥ ሕጋዊ ምክር ቤ ማይነካብን እናምናለን . . . ውን ልማት በተመለከተ ደረጃ ተንቀሳቅሶ በነበረበ ከወልቃይትና የጠገዴ ቀጥሎ ከፍተኛ ተጠቃሚ ራይና የኤርትራ ወንድሞቻች የካርታውን ንድፍ መውጣ ራጩት እንድናቃችንን ለሚ ኖች በጣም አስደሳች ሆኖ ስለዚህ ይህ አሳዛኙ እቅ ነት ካልታረመ ወሬው



ከራዎት

ጀምሮ በሁለቱ ወንድማማቾች ሕዝቦች መካከል በቀላሉና በጥ ቂት ትውልድ ሊታረም የማይችል ቅራኔና እልቂት በመጋበዝ የተሰበሰ ውን የዲሞክራሲ ፋና በዓለም ፊት እንዳያጨልም በመስጋት ይህን የተ ቀጣ የቅስፈት ስይፍ በወቅቱ የመቅ ጨት ኃላፊነት በክብርነትዎ ላይ የተቀ መጠ እንደመሆኑ የበኩላችንን በቅን አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሃሳብ በጐንደር ተወላጅነት ግዴታችን ተኩ ላስተዋና ተፃፋፍተን በትህትና እናቀ ርባለን ። " ሲሉ የአደጋውን አስከ ፊነት ሳይጠቁሙ አላለፉም ።

ከዚያ ወዲህ ያለው ሁኔታ ግን ከህግም ከኃላፊነት ደረጃ ውጭ ሁመራ ፣ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት በክልል አንድ ሥር እንዲተጠቃለል ሁሉ ሕዝቡ ምሬቱን በሆዱ አርግዞ ያለ ባለቤት የቆየባቸው ጊዜያት ጥቂቶች አይደሉም ። አንዳንድ ክል ሎች የመሠረተ ልማቶችን እየዘረጉ የሕዝባቸውን የእድገትና የብልጽግና ተቋርጭሪና ተጠሪ የሌለው የጐንደር ሕ ዝብ ግን በልማትም ሆነ በሌላው እንቅ ስቃሴ ከድጥ ወደማጥ የሚሳብበት ምክ ንያት ዛሬም ግልጽ አይደለም። የትናንት መሪዎቹ በስመ እየነገዱ ድህነት ፣ ሥቃ ይና መከራን አውርሰውት እንዳላለፉ ሁሉ የዛሬዎቹ ገኘሮዎች ደግሞ የራ ሱን ዕድል በራስ መወሰን መብት ለየክልሉ ሰጥን እያሉ ለጐንደር ሕዝብ ግን ያለውንም እንዳያጣ በማ ድረግ ላይ ናቸው ። ይህ ግን ተፋቅረ ውና ተከባብረው የኖሩትን ኩታ ገጠም ሕዝቦች ከማቃቃር በቀር ፋይዳ አይኖረውም ። ሕዝቡ ቻርተሩ በሰጠው መብት በመጠቀም ዳር ድን በሩ እንዲከበርለት ቢጠይቅና አቤቱታ ቢያቀርብ ህጋዊ ምላሽ መስጠትና ለልማት ራሱን እንዲያዘጋጅ ሁኔታ ዎችን ማመቻቸት እንጂ ተቀባይነት የሌለው ካርታ እየቀረፁ በማውጣት ተፋቅሮና ተከባብሮ የኖረን ሕዝብ እርስ በርስ ማቃቃርና ሠላም መን ሳት ሕገወጥነት ብቻ ሳይሆን በታ ሪክም ፊት አስጠያቂ ይሆናል ።

## ምዕራፍ 3

### “ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሁኖአል”

ለአቶ ጎሹ ገብሩ፤ መልሱ ያስፈለገበት ምክንያት በሌላው የጎንደር አውራጃዎችና ወረዳዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር ያለ በመሆኑ ግልጽ ለማድረግ ነው። ወያኔ ያዘጋጀው የተንኮል ሴራ ያልተረዱ አንዳንድ የወልቃይት ልጆች “ወያኔና ደርግ በወልቃይት ላይ የጥፋት ዘመቻ ሲያካሂድ ሌሎች የጎንደር ክፍለ ሀገር ወረዳዎች ዝም ብለዋል” እያሉ መናገር የጀመሩ በመሆናቸው እንዳለ ሁኖ በቅርቡ ደግሞ አጎሹ በመጻፋቸው የጎንደርን ሕዝብ የሚያቀራርብ ሳይሆን የሚያራርቅ በመሆኑ መልሱ አስፈለገ። እኔ ለእርሳቸው መልስ ለመስጠት የፈለኩበት እውነታ ቢኖር ቃሉን ከዚህ በፊት በወያኔዎች ተፈልስፎ ወያኔን በሚደግፉ አንዳንድ የወልቃይት ልጆች የሚነገር ቃል በመሆኑ ነው። እምናለሁ መቶ በመቶ አቶ ጎሹ የወያኔን ሴራ እንደማይደግፉ ነገር ግን እርሳቸው ሳያስቧት ያመለጠች አርፍተ ነገር እንዷን ቃል ወያኔዎች ሲጠቀሙባት በማየቴ ግልጽ ለማድረግ ነው። ወያኔ የትግራይ ሕዝብ ቀደም ቅድሚያ ኢትዮጵያ ከዚያም ትግሬነትን እንቀበላለን ብሎ ስላስቸገራቸው አንድ መላ ፈለገ። ውጭ አገር የመቅረጽ ልምድ ያላቸው ሰዎችን ቀጠሩና ካሜራቸውን አስተካክለው እንዲቀርጹ አሰማሩ። ሕዝቡን ለስብሰባ ሐውዜን ጠራ። ይህንም ወሬ ደርግ እንዲሰማ አደረጉ። ደርግም ፈታሽ ኤሊኮፍተር ልኮ ሲያስጠና የደረሰው መረጃ ትክክል ነው። ወያኔ አስገድዶ የትግራይ ሕዝብ ወደ ስብሰባው እንዲሔድ አደረገ። ከዚህ በኋላ ደርግ አይሮ ልኮ ንጹሕ ሕዝብ ደም በከንቱ እንዲፈስ ሆነ። ከዚህ በኋላ ወያኔን አልደግፍም ያለውን የትግራይን ልጆች ያንን የሥዕል ድም ቪዲዮን ክር በውጭ አገር ያለውን ለማሳመን ቻሉ። በዚህ ዓይነት ሴራ የተካኑት ወያኔዎች ወልቃይትን ከጎንደር ለመለየት ሲሉ ያልፈነቀሉት ድንጊያ የለም። በጥቅም ያደሩ አንዳንድ ሆድ አምላኬዎች ከወልቃይት ልጆች መካከል መለመሉ። እነዚያ ሌሎችን የጎንደር ልጆች “እኛን ወያኔ ሲደበድብን የት ነበራችሁ” እያሉ ሕዝብን እየለያዩ ነው።

ታጋይ ብርሃኔ ገ/ጻዲቅ <u>የኢትዮጵያ ራዲዮ</u> ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም “የዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት የወለደው ጀግናው የኢሕአዴግ ሠራዊት ደርግ ይጠቀምበት የነበረውን የአዲስ አበባ ራዲዮ ጣቢያ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም” ብለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አወጁ። በዚህ ቀን የተደሰቱ ዘረኞች ሲኖሩ አገር አፍቃሬዎች ግን አለቀሱ። ከዚህ ወዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወያኔ ይከፋፍለው ጀመር። እንኳን “ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል” የተባለው ተገለበጠና “ለጠባቦች ጥቅም ተቆጣጥሮታል” መባሉ ነው። አገሪቱን ከፋፍሎ አዲስ የኢትዮጵያ ገጸምድር ካርታ ለሕዝብ ይፋ ሲያደርግ ቅድሚያ የተቃወሙት የጎንደር ምሁራን ናቸው። ወገኖቻችን ወልቃይት ጠገዴንና ጠለምትን ከጎንደር አንለይም።



በቋራ አካባቢ ቤሪ ሻንጉል ለተባለው ክልል የሰተጠው ወረዳ ከጎንደር ወገኖቹ ሊለይ አይገባም ብለው ደብዳቤ የጻፉትን ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይዩ።
ጎሹ ገብሩ <u>ሐዋርያ ጋዜጣ</u> ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሕዳር 22 ቀን 1995 ዓም ገጽ 17 “በአጠቃላይ እነጋገር ወልቃይት በምትባለው ትንሽ መንደር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ከወያኔዎች ስቃይ አልፎ በታገለለት ሌሎች ክ/ሀገራት በሚኖረው ወገኑም ጥሩ አቀባበል አልተደረገለትም። የደመቀ ኑሮውን ትቶ እንዲሰደድ በወያኔዎች ሲገደድ ሳለ ወደ መቀሌ አንድም ሰው አልተሰደደም። የተሰደደው ወደ ጎንደር ነበር። ያገኘው ስጦታ ግን ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሆኖአል። ምንም እንኳ ይህ ዓይነቱ ተንኮል የወያኔዎች እጅ ኖሮት ከጎንደር ሕዝብ ጋር ለመለያየት የተደረገ ዘዴ መሆኑ እየታወቀ አንድም የጎንደር ምሁር ወይም ድርጅት ሁኔታው አሳዝኖት ይህ ዓይነት ድርጊት ስህተት መሆኑን ያብራራ ማንም የለም” ሲሉ ጽፈዋል። አቶ ጎሹ ያሉት ትክክል አልመሰለኝም። የጎንደር ምሁር ሁሌም ስለ ሁመራ ወልቃይት ከመናገር የቦዘነበት ቀን የለም። ሌላው ቢቀር የጎንደር ማህበር ሲመሰረት ጀምሮ ወልቃይት ከጎንደር መለየት የለበትም ብሎ በመነሳቱ አይደለም እንዴ እስከ ዛሬ አንዲት ጎጆ ሳይቀልስ የቆየው። የጎንደል ልማትና ማህበር የሰራው ሕንጻ ባይኖርም መርሃ ግብሩ ግን ምስክር ነው።
<u>የጎንደር ክፍለ ሀገር</u> አውራጃዎችና ወረዳዎች ምክትል ወረዳዎች በተሰኘው መጣጥፍ ገጽ 1 “የጎንደር ክፍለ ሀገር 7 አውራጃዎች 28 ወረዳዎች 119 ምክትል ወረዳዎች” ሲል ከጻፈው መጣጥፍ ላይ ወልቃይት ሆነ ጠገዴ ጠለምት ሌሎችም ወረዳዎች በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ መሆናቸውን ገልጿል። ዋናው የድርጅቱ መርሃ ግብርም ይህን ይዞ የተጻፈ ነው። እርስዎም እንዳሉት ከፋኝ የተመሰረተው በወልቃይት ልጆች ሲሆን መስራቾች ሁሉም ይሙቱ ይኑሩ እኔ ባላውቅም ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር የተባለው ድርጅት መፈክር አንግበው የተነሱ ብዙ የጎንደር ልጆች ነበሩ። አቶ በሪሁን አስፋውና ሌሎች ብዙ የጎንደር ምሁራን ለማጠናከር ጥረት አድርገዋል። በተለይም ይህን ድርጅት ለማሳደግ በገንዛ ገንዘባቸው የለፉት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉት ሊቅ ዶ/ር እንዱዓለም ሙላው፤ አይረሱም። ሌሎች ይረሱ እርሳቸው ግን ሊረሱ አይገባም። ሕይወታቸውን ሽጠው ሱዳን ድረስ ሕደው አምራኩባ ከተባለው የስደተኞች መንደር ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባርን ለማጠናከር ያደረጉት ጥረት ሊረሳ አይችልም።

<u>የአርበኞች ድምጽ መጽሔት ነሐሴ 1991 ዓም ገጽ 28</u>
አረጀን መሰለኝ መረሳት ጀምረናል
የኛኑ መልሰው ሰዎች ይነግሩናል
ወልቃይት ጠገዴ ትግራይ እንደነበር
ተከዜ ተረስቶ የማይጠፋው ደንበር
ለካስ ከላሽን ነው ታሪክ የሚያጽፈው
ቱባው ጀሌ ሆኖ በዝምታ ሲያልፈው
የእግዜር ቁጣና ጊዜው ሲመቻቹ
ድል መንግት ያለ ነው የላዩን የታቹ
ታዲያ ይህም ቢሆን ተራ ጽዋ አለና

የነገን ማሰብ ይሻል በጥሞና
ጸጸት ማስከተሉ የማይቀር ነውና" ይላል።

አቶ ነሹ ገብሩ እርስዎ እንዳሉት የወያኔ ሴራ መኖሩ ባይካድም ጎንደሬው ግን አቶ ነሹ ገብሩ እርስዎ እንዳሉት የወያኔ ሴራ መኖሩ ባይካድም ጎንደሬው ግን ከፋኝ ኢትዮጵያን አንድነት ግንባር አባል የሆኑት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ጎንደሬዎች ከጹሐፊ እስከ ገበሬ ከገበሬ እስከ ከያኒ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት፤ የትግሬ ነው ብሎ ያመነ የለም። በተለይ የጎንደር ማህበር ተመስርቶ ሁኔታውን ሳልሰሙት እያሰማ ሕዝብ ማጠናከሩ አይካድም። የዚህ ማህበር አባላት በአሜሪካ ቅርንጫፍ ሲከፈት ጽሬት ቤት ወልቃይቴዎችን አቅፎና ደግፎ የያዘ መሆኑ አይዘነጋም። እርስዎ የጎንደር ልማት ማህበር እንደማይደግፉ ባውቅም ቅሉ ታሪኩ ሊካድ አይገባም። የጎንደር ልማት ማህበር በኮሎምቦስ ኦኋዮ ጠንካራ የነበረ በወልቃይት ልጆች ነው። ከብዙ በጥቂቱ ለምሳሌ እነዚህን እስኪ ልጥቀሳቸው።

1ኛ አቶ ላቀው ሕሩይ፤ 2ኛ አቶ ክንፌ ተስፋይ፤3ኛ አቶ ሲያምር ቸኮል፤ በሌሎች ክፍለ ዓለም ያሉትን የወልቃይት ልጆች መጥቀስ ይቻላል። በተለይም አውሮፓ ጀርመን ከሚኖሩት መካከል ወያኔን ባለመደገፋቸው በባንዶች የተደበደቡት አቶ ለፈቀ አብርሃም አንረሳቸውም። እርሳቸው "ወልቃይት የጎንደር ግዛት ነው። እኛም ጎንደሬዎች እንጂ ትግሬዎች አይደለንም "በማለታቸው ወያኔ አስደበደባቸው። የወልቃይት ልጆች እንኳን አገር ውስጥ ያሉት ቀርቶ ተሰደው በሔዱበት አገር ሁሉ ወያኔ እየተከታተለ እያስደበደባቸው መሆኑን ታሪክ ዘግቦታል። አንባቢያን ይታያችሁ የወልቃይት ልጆች ሱዳን ያሉት አልቀዋል። ወደዚህ ወደ አሜሪካ ስንመጣም ኮሎምቦስ ኦኋዮ የወልቃይት ልጆች ከአንድ አካባቢ ሰብስብ በማለታቸው ወያኔ ባንዶችን አስገብቶ ስለከፋፈላቸው አቶ አባይ መንግሥቱ ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት ከተማ ለወቅ ኦኋዮ በመግባት የወያኔን ሴራ በማጋለጥና የወልቃይት ተወላጆች ወያኔን መደገፍ እንደሌለበት ጠንክረው እያተገሉ ያሉ መሆናቸው ያስመሰግናቸዋል። ሕዝብን ማክበር ማለት እንደ አቶ አባይ መንግሥቱ እንጂ ውጭ ሁኖ መተቸት አስፈላጊ አልመሰለኝም። ወደ ኮሎምቦስ ኦኋዮ ስንመለስ ጎልመስ ያሉት ብቻ ሳይሆን ወጣቶች ሳይቀር ወያኔ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን የጥፋት ዘመቻ እየተጋፈጡ ያሉ ብዙ ናቸው። አቶ ቻላቸው አባይ፤ እንዲሁም ገባ ወጣቱ አቶ በየነ ማማይ፤ ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

አቶ ነሹ አስተውሉ እንጂ እንዴ ኸረ ስንት የጎንደር ልጆች በወልቃይት ምክንያት ደማቸው በወያኔ ፈሷልና አጥንታቸው ሸኽ ሁኖ ይወጋናል። ልንረሳቸው አይገባም። ከዚህ ላይ ጎንደሬዎች ወልቃይቴዎችን አቅፈው የያዙ መሆናቸውን አስመልክቶ ክፍል 4 ምዕራፍ 2 የተጻፈውን ሠነድ ሊመለከቱ ይችላሉ። እርስዎ የሚያነቡት ዲሞክራሲያን ብቻ በመሆኑ ሌሎችን ሠነዶች ስለማያዩ እንጂ የጎንደር ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታውን የሚያውቀው ያልጻፈ የለምና ወቀሳው ትክክል አይደለም። የእርስዎ አባት ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል ስለ ወልቃይት ጎንደሬነት አስመልክቶ የተናገሩትን ከላይ የተጠቀሰውን ሊመለከቱ ይችላሉ። ወልቃይቴዎች ትግርኛ በመናገራቸው አልተናቁም።



ሕዳር 11 ቀን 1984 ዓ.ም

ር አቶ መለስ ዜናዊ
ትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዴንት
ስ አበባ

ር ፕሬዚዴንት፡

ከአክሱም ምሥረታ በፊት ጀምሮ የትግራይና የጎንደር ሕዝብ በበር፤ ቋ፤በባሕል፤በጋብቻ፤በሰም፤በሃይማኖት፤በአገር ፍቅር ስሜት፤ በጂኦግራፊና በኢኮኖሚ ትላልው አነጋገር በታሪክ በኑሮና በባሕል ተግሥሮ፣ የተከዜን ውሃ በጋራ እየጠጣ ድምበር ርስ ክጥንት የወረሰውን የአበውን ታሪክና ቅርስ አክብሮና ተደጋግፎ በመኖር ኢትዮጵያን ሺህ ዓመታት የታሪክ ባለሃብት ያደረገ፣ ሲቀር ቢውል ከአንድ ቅድመ አያት የሚቆጥር ጠግ ሕዝብ ነው።

በመሆኑም የጎንደርና የትግራይ ሕዝብ አንድ ብሔረሰብ እንጂ ሁለት ብሔረሰብ ቅበለ የትና መቆጠር አልነበረበትም። አንዱ በተመቸውና በተማላለት ጊዜም ሌላውን ኢታቃትና መደገፍ እንጂ ማሳፈርና መናቅ ባሕሉ ሆኖ አያውቅም።

በንቀትና በእብሪት አግባብ ምክንያት ግዙፍ ሠራዊት የነበረው የመንግሥቱ ኃይለ ም መንግሥት በቀላሉ ተንኮታኩቶ ሲወድቅ ታይቷል።

ትግራይና ጎንደር ባለፈው 17 ዓመታት የጨለማ ዘመን ውስጥ በሰው ሕይወት ዕትነትና በኢኮኖሚ ውድመት በኩል ያላቋረጠና ከፍተኛ የጋራ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ው በመነሳታቸውና በመታገላቸው ኢትዮጵያን ከጭቆና አገዛዝ ነፃ አውጥተው አሁን ብት የፖለቲካ ነፃነት /ዲሞክራሲ እና የኢኮኖሚ ተስፋ ጭላንጭል በር ላይ ሊያደርሷት ል።

የነዚህ ሕዝቦች የታሪክና የአንድነት ዕውነተኛ ገፅታ ይህ ሆኖ ሳለ ሰሞኑን ፉሐ ኮንፌደንሻል " የሚባለው የ15ቀን መጽሔት ባወጣው ዕትም ከኢትዮጵያ ሽግግር ንግሥት አገኘሁት ብሎ የሳለው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የአስተዳደር ክልል ካርታ ለጎንደር ክና ቅርስ ቀዳሚ ባለቤት የሆኑትን ለም ቦታዎች ማለትም ሰቲት ሁመራን፤ ወልቃይትን፤ ጼግና ጠለምትን ከተፈጥሮና ከታሪክ አካላቸው ከጎንደር ለይቶ የተከዜን ድምበር በመጣስ ግራይ አስተዳደር አካል በማድረግ ቦታዎቹን የትግራይ ልማት ማኅበሪያ ሕዝቡን 2ኛ ደረጃ ግራይ ዜጋ ለማድረግ መታቀዱን ስለተረዳን በተቃጣብን የውርደት በትር እጅግ በጣም ንቀናል/ አዝነናል።

በተጨማሪም ቅዱስ ድርስ የተወለደበትን ቋራን አፅሙ ያረፈበትን ማሕበረ ሥላሴን የሑንስ የተሰቀበትን መተማን እስመልክቶ ቀላማውን አገር በሙሉ ዘሩንና ስሙን አካባቢው ሰምቶት ለማያውቀው "ቤኒሻንጉል" ለተባለ በዚያ አካባቢ ለማይኖር ጎሣ ስመስጠት መታቀዱ ከርታው አሳዳቂል። ይህ ዕቅድ ከአሚድባ እስከ መተማ ባለው ቀላማ መሬት ላይ ከዘንተ ዓለም ጀምሮ ከብቱን እንደልቡ ከቦታ ቦታ እያዘዋወረ የሚያሰማራውን ደገኛ የቋራ፣ የአለፋ፣ የጣቁስ ፣ የተገከል፣ የጭልጋ፣ የመተማና የአዳኝ አገር ሕዝብ እስከ አሁን ፀንቶ የኖረለትን ሕጋዊ መብቱን የሚጋፋ ነው።

ከጥቂት ቀናት በፊት የኢትዮጵያ ድምፅ ሬዲዮ የሽግግሩ መንግሥት ምክር ቤት የኢትዮጵያን አስተዳደር በ14 ክፍሎ አዕድኖል ብሎ ያስተላለፈው ዜና "አፍሪካ ከንፈዴሬሽን" ከቀመው ክርድ ጋር የተቀረፀ እንዳልሆነ ተበሩ ሰምቷል። ከሆነ ግን ይህን ጉድፍ የሕግ መንግሥት አድዳቱ ገባዔ ማቅረብ እነዚህን ወንድማማች የትግራይና የጎንደር ሕዝቦች ካሁን ጀምረው በዩጅት እንዲሰባሰቡ መጋበዝ ነው ከሚባል በቀር ሌላ ምክንያትና ትርጉም አይኖረውም። በተጨማሪም በሽግግሩ መንግሥት ምክር ቤት ውስጥ የጎንደር ሕዝብ የመረጠ ተወካይ ባለመኖሩ እኛ ይህን ለማስረዳት የምክርነውን ቀበሌንና ታሪኩን በግምባር የሚያስረዳ አላገኘም። በመሆኑም ከዛሬ ቀልም ጀምሮ የቆየውን መብታችንንና ታሪካችንን በሕዝብ የሚመረጥ ሕጋዊ ምክር ቤት እንደሚያስከብርን እናምናለን።

ይህን ዕቅድ በተግባር ላይ ለማዋል ቢሞከር በገሃዳዊነት በሚመጣውና በተገፋነት በሚመከተው ወንድማማች ሕዝብ መካከል የሚደርሰው ዕልቂት ቀላልና ቀበሉ ለብዙ ትውልድ የማይሽር በሚሆን ይህ በከባድ መሥዋዕትነት የተገኘ ድልና የተበሩ ጭላንጭል በዚህ ምክንያት እንዳይጠፉብንና እንዳይወድቅብን "በራሱ የተከፋፈለ ቤት አይጸናም" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዳይደርስብን ያስጋል።

ለ17 ዓመታት የተሰቃየው አልበቃው ብሎ ይህን ወንድማማች ሕዝብ ለእርስ በርስ ግጭት መዳረግ በወርቅ ቀለም ሊፃፍ የሚገባውን ይህን ዓቢይ የትግራይ ፣ የጎንደርና የወሎ ሕዝብ የትግል ታሪክ ጊደትና የድል ውጤት የሁፍረት ማቅ መልበስና የወደፊት ትውልዶች ዕርግማን ማድረግ እንዳይሆንብን ያሰጋል።

የአካባቢውን ልማት በተመለከተ ለምሳሌ ስቲት ሁመራን ብንወቅስ ልማቱ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሶ በነበረበት ወቅት ከወልቃይትና ከጠገዴ ተወላጆች ቀጥሎ ከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚዎች የትግራይና የኤርትራ ወንድሞቻችን ነበሩ። በዚህ ሁኔታ የጎንደር ሕዝብ ይደሰት ይበረታታ ነበር እንጂ ምንም ዓይነት ቅሬታ ወይም ማጉረምረም እንዳልነበረበት በሁላችንም ልቦና ውስጥ እስካሁን የሚበራ ሕያው ትዝታ ነው።

ይህ የሚያንፀባርቀውም በጎንደር ሕዝብ ዓይን የትግራይና የኤርትራ ሕዝብ በድምበ ሳይገታ በአንድ ቤተሰብነት ተሳስሮ በክፉውና በበጎው ጊዜ አንድ ትብስ፣ አንድ ትብስ ተባብሮ አብሮ የመኖር ዘላቂ ባህርይ ያለው አንድ ወጥ ሕዝብ መሆኑን ነው።

የክርታው ጉድፍ መውጣትና መሥራጨት እንድንታችንን ለሚጠሉ ወገኖች በጣም አስደሳች ወሬ ሁኖላቸዋል።

ስለዚህ ይህ አሳዛኝ ዕቅድ በፍጥነት ከልታረመ ወሬው ካሁን ጀምሮ በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል በቀላሉና በጥቂት ትውልድ ሊታረም የማይችል ቅራኔና ዕልቂት በመጋበዝ የተሰበከውን የዲሞክራሲ ፋና በዓለም ፊት እንዳያጨልመው በመስጋት ይህን የተቃጣ የቅስቀሳ ስዩፍ በወቅቱ የመቅጨት ኃላፊነት በከበርነትዎ ላይ የተቀመጠ እንደመሆኑ የበኩላችንን በሰላማዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሀሳብ በጎንደር ተወላጅነት ግዴታችን ተነሳስተንና ተገፋፍተን በትኅትና አቅርበናል።

ከማክበር ሰላምታና ከበጎ ምኞት ጋር

ዳኘው ወልደ ሥላሴ
ም.ሚ.ቁ. 70556
ስልክ ቁ. 201851
አዲስ አበባ

ፍትሕአየ አበጉ
ም.ሚ.ቁ. 26800
ስልክ ቁ. 513870
አዲስ አበባ

ግልባጭ ፡ - ለክቡር አቶ ታምራት ላይኔ
- ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ምክር ቤት



## ምዕራፍ 4

## ለወልቃይት የጎንደር ልጆች!

*የሐዋርያት ሥራ* 23.11 "በሁለተኛው ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ-ጳውሎስ ሆይ! በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርክ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው" ሲል ተጽፏል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጌታን መንግሥት እየመሰከረ ሲታሰር ሲደበደብ ሲሰደድ ኑሮ በመጨረሻው ራሱን ለጌታ ሲመሰክር አልፏል:: በሀገራችን ኢትዮጵያ በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ የወልቃይት ተወላጆች "ጎንደሬዎች እንጂ ትግሬዎች አይደለነም" ሲሉ ታስረዋል! ተገድለዋል! ተሰደዋል! ዛሬ ድረስ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ መሳሪያ አንስተው በመዋጋት ላይ ናቸው:: ከአገር ውጭ ያሉ እንዲሁ የወያኔን ሴራ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነው በማጋለጥ ላይ ይገኛሉ:: ይህ ታሪክ ለተወላጆች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ኢትዮጵያውያን አጠናካሪ መሆኑ ግልጽ ነው:: ወልቃይትን በተመለከተ የሩቁን ታሪክ ትተን የቅርቡን ታሪክ ብንጠቅስ ለኢትዮጵያ ታላቅ ተግባር የፈጸሙ ጀግኖች የወለደች ናት:: እኔ ስማቸውን የምጠቅሰው ግለሰቦች በታሪክ ተጽፈው ካገኘሁት መረጃና በዓይን አይቼ ምስክር የምሆንባቸውን ስም ብቻ ጠቀስኩ እንጂ ሌሎች ብዛት ያላቸው ታሪክ ሰሪዎች መኖራቸው አይዘነጋም:: ስለዚህ ሌሎችን ስማቸውን ያልጠቀስኩበት ካለማወቄ መሆኑን አንባቢያን እንድትረዱልኝ አሳስባለሁ:: ጣልያን አገራችንን በወረረችበት ወቅት ብዛት ያላቸው የወልቃይት ልጆች ለሀገር ክብር ሲሉ ደማቸውን አፍሰዋል:: አቶ ገሪማ ታፈረ የጎንደር ክፍለ ሀገር አርበኞች ፀረ ጣልያን ጦርነት ለማድረግ መጀመሪያ ጥይት በጣልያን ላይ የተኮሱትን መዝግበዋል::
ገሪማ ታፈረ <u>ጎንደሬ በጋሻው</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 17 "በወልቃይት ፊታውራሪ መስፍን ረዳ+አባይ ወልደ ማርያም+መለሰ ኃይሉ÷ቸኮል ብቅአለ" የመጀመሪያውን ጥይት ተኳሽ ጀግኖች ሲመዘግቡ ዛሬ ወደ ትግሬ በክላሽ የተከለሉትን ወረዳዎች በጎንደር ውስጥ መሆናቸውን ያሳያል:: ለምሳሌ ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 17 "በጠገዴ+ በጠለሉ+ በወልቃይት በጠለምት" እያሉ ጽፈዋል:: በነዚህ ወረዳዎች ቅድሚያ በጣልያን ላይ ጠይት የተኮሱት ስማቸውን ከጠቀሷቸው ገጽ 17 "አዳነ መኮንን፤ዓለማየሁ ንጉሴ፤ገብረ ማርያም ፈንታ፤ አያናዬ ይልማ፤ ገብረ ሕይወት ሲሳይ፤ ቃታው ፏፏቴው፤ ተክሌ፤ መንግሥቱ፤ ነጋ አበራ፤ደበብ፤ እንዴት ሳርግህ፤ ኀሹ ለውጠ፤ መኮንን ነጋሽ፤ ደስታ ማሩ፤ በየነ አባ ጋራ፤ ፊታውራሪ መስፍን ረዳ፤ አባይ ወልደ ማርያም፤ መለሰ ኃይሉ፤ ቸኮል ብቅአለ፤ ቀኛ ጥሩነህ ፈለቀ፤ፊታውራሪ በላይ እረታ፤ ደስታ ይግዛው፤ ታፈረ ወርቄ፤ አምባው ፈለቀ፤ እየለ ተሰማ፤በላይ አረጋይ፤ ሺፈራው አምባው፤ ቸኮል ሺበሽ፤ ሞገስ አሊ" ሲሉ የመጀመሪያውን ጥይት ተኳሾች ጽፈዋል::

ግደይ ባሕር ሹም አሞራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 189 "አባት አርበኞች የወልቃይት ታጋይ መሬዎች የሆኑ ፊታውራሪ የሸወንድም ናደው፤ፊታውራሪ ሰረበ ለማ ፤ልጅ ተድላ ወልደማርያም፤ ባላምባራስ በዛብህ አደመ ልጅ አስማማው መንግሥቱ" ሲሉ ጽፈዋል። የአቶ ግደይ ባህር ሹምን መጽሐፍ ጥቅስ የጠቀስኩት ከዚህ ላይ አቶ ገርማ ታፈረ ካልጠቀሱት አባት አርበኞች መካከል ለመጨመር በመፈለጌ ነው። የአቶ ግደይ፤ ትግራይ ይንቀሳቀስ የነበረውን ሲመሰረት ጠራናፊት ይባል የነበረውን ኋላ የኢዲዩ ጦር የሆነውን ሠራዊት ይዘው በወልቃይት ሲገቡ የተደረገላቸውን አቀባበል ሲጽፉ ከዘገቡት ስሞች መካከል ሲሆን ሌሎች ታላላቅ አርበኞች በወልቃይት ነበሩ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ስሞች ጋር የተወሰኑ ተቀራራቢ የሆኑ ጨርሶም ሳይጠቀሱ የቀሩ ስሞች ልጨምር። በቅርቡ ከወጣ አንድ በራሪ ወረቀት የተገኘ ጹሑፍ ነው።

ከስሜን አሜሪካ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ ከተባለው መጣጥፍ ገጽ 1 "የሩቁን ትተን የቅርቡን ብንመረምር እንኳ ፊታውራሪ መለሠ ኃይሉ፤ ፊታውራሪ ጎሳ፤ ፊታውራሪ ሠረበ ለማ፤ ፊታውራሪ የሸወንድም ናደው፤ ቀኛዝማች አያልነህ አዛገ፤ ፊታውራሪ ቢተው ገፋ፤ ግራዝማች ተገኘ ቢተው፤ ባሻይ መአዛ ፊታውራሪ መስፍን መ/ቶ ፍትሃለው ደምስስ ባላምባራስ በዛብህ አደመ፤ ቀኛዝማች ገብሩ፤ አዝማች ይርጋ ነጋሽ፤ ደጃች ደስታ ማሩ፤አቡሃይ አብተው፤ ሁሪ ጎላ እና በዚህ ውስጥ ስማቸውን አካተን ለማቅረብ ያልቻልን እጅግ በርካታ አገር ወዳዶችና ጀግኖች ሕዝባቸውን አስተባብረው ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የኖሩባት የአገራችን ክፍል ለመሆኗ አጠያያቂ ሊሆን የሚችል አልነበረም" ሲሉ ጽፈዋል። በነገራችን ላይ ይህን ጥቅስ ከዚህ ለማስገባት የፈለኩት ስሞችን ለመጨመር ፈልጌ መሆኑን ለአንባቢያን ማሳሰብ እወዳለሁ። አገር ከወራሪ ነፃ ስትወጣ የሁመራ የእርሻ ልማት መስርተው ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ሲያስገባ የነበሩ ናቸው። በአጤውና በባለሥልጣኖቻቸው ድክመት ሁመራን ለሱዳን ለመስጠት ቃል በተገባበት ወቅት በልጅ ተድላ ወልደማርያም አስተባባሪነት ሱዳንን የመለሱ መሆኑ አይዘነጋም።

አሞራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 99 "ያኔ ሁመራ ከተማ ከተያዘች በኋላ ሁለት መቶ ሰባ ሺህ ብር ከሁመራ ባንኮች የተገኘውን ገንዘብ የሁመራ ባንክ በእኛ በሁመራ ባላባቶችና አዝማኞች ብቻ የሚተዳደር ንብረት ነውና ከዚህ ቅስቅስ አይልም ብለው ለአሳደሙት ከእነ ደጃዝማች ታየ ጎላ አፈሙዝ ነጥቄ ገዳሪፍ ጽፈት ቤት ድረስ ወስጄ እንዳደረስኩ ሟቹ ዶ/ር ሻለቃ ተፈራ ባዘዘኝ መሰረት አድርሁሉት" ሲሉ ጽፈዋል። ከሁመራ ባንክ ኢዲዩ የወሰደውን ብር ብዛት በተመለከተ መላከ ሰላም ሲሳይ አየለ "ከሁመራ ባንክ የተወሰደው ከ3 ምልዮን ብር በላይ ሲሆን ጥጥና ሰሊጡ ሳይቀር ተጭኖ ሱዳን ገብቷል" ሲሉ ነግረውኛል። ደርግ ሁመራን ሰኔ 1969 ከያዘ ጀምሮ የወልቃይት ሕዝብ ሱዳን ተሻግሮ አምራኩባ ከሚባል ቦታ ላይ ከትሞ ሌሎችን የኢትዮጵያን ሕዝቦች እያስተናገደ የሳከ ሕዝብ ነው። የወልቃይት ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት ትግል ሲሉ የተሰቃዩ ካህናት ሳይቀሩ ደክመዋል። መላከ ሰላም ሲሰይ አየለ፤ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እኔ መጽሔቱን ማተም ሳቆም ሉስ አንጀለስን



ለቅቄ ሲያትል ስመጣ ሐምሌ 18 ቀን 1995 ዓም ቁጭ ብለን ስንጫወት ልብ የሚነካ ቃላት ተናገሩ።


"ለአገር ለዳር ደንበር የለፋው ልጅ ተድላ ወልደማርያምን ኢሕአፓ በ1979 ዓም ነሐሴ ቋራ ላይ ገደለው። እነ አቶ ጌታቸው ይርጋንና ሌሎችን ጀግኖች ወያኔ ከሱዳን መንግሥት ጋር በመስማማቱ አስረው ገደላቸው። እኔን ከባለቤቴ ጋር ለያይቶን ሳንተያይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች። ልጆቼ ግማሾቹ አውስትራልያ ሲሰደዱ ግማሾችን የአሚሪካ መንግሥት አምጥቶልኝ ከኔ ጋር አሉ። ለወልቃይት ሕዝብ አሌንታ ይሆናሉ የተባሉት ታስረዋል። ሽሬ ላይ ከ1000 በላይ ታስረው ይሰቃያሉ። ከመያዝና ከሞት የተረፉት እንሆ ከፋኝ ብለው በዱር በገደል ይሰቃያሉ" ሲሉ አጫወቱኝ። እርሳቸው የነገሩኝ እነ አቶ ጌታቸው ይርጋንና ሌሎችን ከሱዳን አስሮ ለወያኔ የተሰጡ መሆናቸውን ነው። አቶ ግደይ ባህር ሹም አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 284 "ጌታቸው ይርጋና ሌሎችም አርበኞች የወልቃይትና የአርማጭሆ ደግኖች በሥዩም ትእዛዝ በሱዳን ታፍነው ጥይት እንዳይጮህ ሰው እንዳይሰማቸው ብዙም ሳይርቁ ዶካ ከተባለው ከተራራው በደርቡሾች ካራ ታርደው ከአንገታቸው ከበርሃ ጥለው ለአሞራ ሰጧቸው። በራስ ልጅ በሥዩም ሰው እየተሸጠ በጭካኔ ታርዶ ለአሞራ ተሰጠ። ልዑል ራስ መንገሻ ዘር ይፋረዳቸው በእሳቸው እንዳይበቃ ደግሞም በልጃቸው መሬያችን እያለ ታጥቆ እንዳልተዋጋ ክህደትና ትዕቢት ሆን የሰው ዋጋ" ሲሉ ጽፈዋል። አቶ ግደይ የጻፉት በግጥም ሲሆን እኔ በስድ ንባብ ጽፌዋለሁ። ከላይ መላከ ሰላም ሲሳይ እንዳሉት ከሞት የተረፉት ዛሬም ቢሆን እየተዋጉ ናቸው።

እኔ የትጥቅ ትግል የምጠላ ብሆንም ታሪካቸውን መመዝገብ የግድ ይመስለኛል ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ እጥፊ መሆኑ ባይካድም ለጊዜው መፈናፈኛ በማጣት ከሻዕቢያ ተጠግተው ወያኔን እየወጉ ያሉት የዱር ኢዲዮች የቅርቡ ክፋኞች የአሁኑ የአርበኞች ግንባር በሚል ስም የሚሞቱት የወልቃይት ልጆች ናቸው። የወልቃይት ልጆች ቀደም ሲል ዘመናዊ ተማሪዎች የኢሕአፓ በመሆን የሞቱና የቆሰሉ የተሰደዱ ናቸው። በጠቅላላው ታላላቅ የወልቃይት የሁመራ ሰዎች ለኢትዮጵያ አንድነት ታግለዋል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ጄኔራል አሰፋ አያናን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከ1966 ዓም ወዲህ ደግሞ የተለያዩ ድርጅቶች ሲመሰረቱ ታግለዋል። በተለይም ኢዲዩን ለማሳደግ ያደረጉት ትግል መጠቀስ አለበት። በነገራችን ላይ ወይዘሪት አዜብ ወይም ለምለምን ያሳደጉ ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ናቸው። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ከደርግ ጋር የተጣሉት በአረመኔነቱ ምክንያት ጥላቻ ስላደረባቸው ነው። የኢዲዩን መርሃ ግብር ይዘው እንደገና ጎንደር ገብተው ለሌሎች የተማሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለአቡነ እንድርያስ ሳይቀር አድለዋቸው በርሃ ገብተዋል። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ኢዲዩ ሲደክም ሱዳን ተሰደው የኖሩ ሲሆኑ ምግብ ቤት ከፍተው ማንኛውንም የሰው ልጅ እየረዱና እያገዙ የኖሩ ሲሆን ስደተኛው ሕዝብ" እማምዬ" ብሉ ይጠራቸው ነበር።

ከሱዳን ወደ አሜሪካ መጥተው ሉስ አንጀለስ አብረን እንኖር ነበር። አንድ ቀን ከቤታቸው ሀጄ ቡና አፍልተው እየጠጣን ሳለ ስልክ ተደወለ። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ትግርኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ ታዲያ ስልክ ወዳይዋ የሚያወሩት

በትግርኛ ሲሆን እርሳቸው የሚያናግሯቸው በአማርኛ ነው:: " ለምን በትግርኛ አትናገሪም" የሚል ጥያቄ ከወይዘሪት ለምለም ወይም አዜብ ሲቀርብላቸው መልሳቸው "ትግርኛ እኮ ወያኔ አስጠላኝ ብለው መለሱላቸው:: እንደገና ወንድማቸው ደጃዝማች ታዮ ጎላ ሙተው ሐዘን ተቀምጠው ሳለ ወይዘሪት አዜብ ስልክ ደውለው እርሳቸው በትግርኛ ሲያወሩ ወይዘሮ ማንያሉሽ፣ በአማርኛ ተናገሩ:: ወዲያው ደግሞ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ከትምጣቸው ስልኩን ተቀብለው በአማርኛ አናገሩአቸው::ወይዘሮ ማንያሉሽ ወያኔን የሚደግፉ ወልቃይቴዎች በትግርኛ ሲያናግሯቸው እርሳቸው የሚመልሱት በአማርኛ ነው::

ወይዘሮ ማንያሉሽ ጎላ አገራቸውን አጥብቀው ይወዳሉ:: በዚህ አረጋዊ እድሜያቸው ወያኔን አጥብቀው ይጠላሉ:: ወይዘሮ ማንያሉሽ ለኢትዮጵያ አንድነት አቅዋም ያለውን ድርጅት ይደግፋሉ:: የጎሳና የጎጥ ድርጅት ደግሞ አጥብቀው ይጠላሉ:: እርሳቸው ወልቃይት ወደ ትግሬ መከለሉን አጥብቀው ይቃወማሉ:: ወያኔን የሚጠሉት ወልቃይት ወደ ትግሬ በመከለሉ ብቻ ሳይሆን የወያኔን አስተዳደር ለወደፊቱ የኢትዮጵያን አንድነት ይበትናል ብለው ይናገራሉ:: ወይዘሮ ማናሃሉሽ "ወያኔ በኢትዮጵያ እስካለ ድረስ በሕይወቴ ወደ ኢትዮጵያ አልሄድም ብለው ዛሬ ኮሎምበስ ኦሃዮ ይኖራሉ:: በቅርብ የማወቅ እድል አግኝቼ እርሳቸውን ጠቀስኩ እንጂ እጅግ ብዙ የወልቃይት ልጆች ወያኔን አይፈልጉም:: ለወደፊቱ ታሪካቸው ተለቅሞና ተበጥሮ እንደሚጻፍ አምናለሁ:: በእርግጥ አ|ወልቃይት ያልታተመ መጽሐፍ ብዙ የአካባቢውን ሰዎች ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ዘግቦ የያዘው መጽሐፍ ለታሪክ ተመራማሪ በር ከፋች ይሆን የሚል እምነቴ የጠነከረ ነው::



ወይዘሮ ማንያሉሽ ጎላ ጎሹ!



እያናእገዚ አ|ወልቃይት ያልታተመ
"የፍየል ግልገሎች መንትያ ተወልደው
የናት ሆድ ኽርንኩርኩር አፈጣጠራቸው
የጧት ዕድላቸው አንደኛው ብራና ሌለኛው
ቅራና ሆኑ እጣ ፈንታቸው
ብራናው በመቅደስ ሲከበር ሲወደስ
ቅራናው ካመድ ላይ አየሁ ሲልከሰከስ
አምላክ ወልደ እግዚአብሔር ለይኩን እንዳለው
ለካ እጣ ፈንታ ነው ክጥንት የበየነው
አንደኛው ቆራጥ ነው
ሁለተኛው ባንዳዳው" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 5

## ወያኔ ለሆናችሁ የወልቃይት ልጆች!

ወደዋናው የምዕራፉ መነሻ ወደሆነው ከመግባቴ በፊት ባንዳ ማለት ምን ማለት ነው? ባንዳ ጥሬ ቃሉ የሀገር ፍቅር የሌለው| ለወገኑ የማይቆረቆር! ሆዱ ከሞላ ለምንም ለማንም የማይቆጭ| በቅርሱና በታሪኩ የማይኮራ ለጥቅም ሲል ለመታዘዝ የተዘጋጀ|ክብርና ኩራት የማይሰማው ብሔራዊ ሠንደቅ ዓላማ የሌለው ከወላጆቹ የወረሰውን ሃይማኖት እንኳ የሚጠላ፣ በጠቅላላው ለሆዱ የሚታዘዝ ከውሻ የበሰ በሆዱ ያደረ ማለት ነው:: ወገኖቻቸው ለአገር አንድነት ሲታገሉ እነሱ ለጥቅማቸው የሚስገበገቡ ተፈልፍለዋል:: አገሪቱ ተቆርሳ ለጎረቤት አገር ስትሰጥ ዝም ብለዋል:: ባንዶች ከዚህ በፊት ሕዝባቸውንና አገራቸውን የካዱት ለጥቅም ሲሉ ነው:: ለጥቅም ያደረ ሰው ደግሞ ከአህያ ተለይቶ አይታይም:: በእርግጥ በአርያ ስላሴ የተፈጠረን ሰው ከአህያ ጋር ማመሳሰሉ ትክክል ባይሆንም በሆዳምነቱ ግን ትክክል ነው:: አህያ ጥሬ ከሰጧት ወደ ቤቷ አትሔድም:: ጥሬ ካገኘችበት ቤት አትለቅም ስለዚህ በሆድዋ ተገዛች ማለት ነው:: ባንዳ ወገኑን ገድሎ እንካ እንጀራ ብላ ሲባል የሚበላ ሰው "ለምን ገደልክ ሲባል መልሱ የእንጀራ ጉዳይ ነው" ይላል::

በጣሊያንኛው ሹምባሽ ቡልቃሽ እያሉም ይጠሯቸው ነበር:: እነ ደ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ረግጠው የሮማን ባንዴራ ያከበሩት ባንዶች ዛሬም የልጅ ልጆቻቸው ኩራት መስሉአቸው አንስተውታል ባንዳ የራሱ ሕዝብ እንዲሰለጥን አይፈልግም:: ቅኝ ግዛት ሊይዝ የመጣ መንግሥት ያንን ሕዝብ አደንቁሮ ለመያዝ ያስባል እንጂ እንዲሰለጥን አያስብለም በዚህ ምክንያት ጣልያን ኢትዮጵያውያን እንዳይማሩ ለማድረግ ጥረት ያደረገው በገንዘቡ በገዛቸው ባንዳ ባለሥልጣን ምክንያት ነበር:: ከዚህ

በላይ ስለ ባንዳ ሰፋ ብሎ የተብራራ መሆኑ እንዳለ ሁኖ በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃና ያሉ አንዳንዶቹ በሆዳቸው ተገዝተው "እኛ ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም" ያሉ ስላሉ እነዚህ ሰዎች ለምን ይህን አሉ ተብሎ ሲፈተሽ መልሱ ሁለት ሁኖ ይገኛል። 1ኛው ወያኔ ውሻ ይመስል አጥንት ዲቃሎችን የራሱ አድርጎ የያዛቸው ሲሆን 2ኛው ደግሞ ለሆዳቸው ያደሩ ባንዳ ግለሰቦች በመኖራቸው ነው።

የወያኔ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይደግፈው መሆኑን አውቆ በገንዘብ ሕዝቡን ገዝቶታል። ለምሳሌ መስሪያ ቤት አንድ ሰራተኛ ሲቀጥር ጥያቄና መልስ ካደረገለት በኋላ ለሁለተኛ ግዜ ይጠራና "ባለህ የትምህርት ደረጃ ልንቀጥርህ ተዘጋጅተናል ነገር ግን ማሟላት ያለብህ ጉዳይ ያለ ያም የኮር አባል ካልሆንክ ሥራውን ልታገኘው አትችልም" ሲባል ቆራጥ ከሆነ ግለሰቡ "እኔ የምኮራው ባለኝ የስራ ልምድና በትምህርቴ እንጂ የኮር አባል አልሆንም" ብሎ ይወጣል። ሆዳም ከሆነ ግን ሥራውን ለመቀጠር ሲል "እሺ ይነገረኝ" ይላል። ይህ ግለሰብ የተማረ ከፍተኛ የሥራ ልምድ ቢኖረውም የኮር አባል በመሆኑ የተሥተካከለ ስራ ሊሰራ አይችልም።

ይህ ግለሰብ እያወቀ እንዳላወቀ ሁኖ የአገር ጥቅም ሲጎዳ ይመለከታል። ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ወገኖቹ እየተበደሉ እያየ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ ጀሮ ዳባ ልበስ ብሎአል። ለዚህም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ይቅርና በስደት ያሉት የጥቅም ሰዎች የገዙት ቤት፥በነፃ የተሰጣቸው መሬት እንዳይነጠቁ ሲሉ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ሲደፈር ዝም ማለትን መረጡ። ይህ የአገር ጠላት ከመሆን ተለይቶ አይታይም። በተለይ ይህን ምዕራፍ በተመለከተ ጠንከር ያለ ነቀፌታ የማቀርበው ከውጭ ወደ አገር በሚገባው ወገኔ ላይ ይሆናል። እኛ ዛሬ በአሜሪካን ሆነ በሌሎች አገሮች ያለን መኪና ጠብቀን ሆነ ሳንቲም ቆጥረን፣ ቤትና ግድግዳ አጥበን ሆነ ሳህን ወልውለን ታክሲ ነድተን ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ወገናችን የተሻለ መኖራችን አይዘነጋም። ይህን ደም ተፍተን የምናገኘው ዶላር ወደ ኢትዮጵያ ሲለወጥ ብዙ ነው። እኛ ስላለን ብቻ የሌላውን እድል መሻማታችን በታሪክ የሚያስወቅሰን ይሆናል። ይህ ብቻም አይደለም ወያኔም ለራሱ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ቁማር አድርጎ ስለወሰደው አንዳንድ ጥቅማጥቅም ማስገኛ መንገድ አድርጎ መመሪያ ሰጥቶበታል።

<u>ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ኤምባሲ፣ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት</u> የተሰኘው መረጃ ገጽ 3 "በውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን በመረጡት አጀንዳና አደረጃጀት ዙሪያ እንዲሰባሰቡ በማድረግ በቀጣይነት ጥቅሞቻቸው እየተከበረ ተሳትፎዎቸው እንዲጠናከር ይደረጋል። በአገር ውስጥና በውጭ አገሮች የሚኖራቸው መብትና ጥቅም እንዲረጋገጥ ወደ አገር ቤት እንደልብ እንዲመላለሱ ንብረት በሕጋዊ መንገድ እንዲያስገቡና ቤት እንዲሰሩ፣ኢንቨስትር እንዲያደርጉ፣ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ እንዲያስተላልፉና የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ የትውልድ ኢትዮጵያዊ



መታወቂያ እንዲያገኙ ማገዝና በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ከነሱ ጋር አብረን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።"

"በዚህ ዕቅድ ውስጥ በውጭ የሚኖሩ የኮሚዩኒቲ አባላት በመረጡት አጀንዳና በፈለጉት አደረጃጀት ዙሪያ ተሳትፎዋቸውን ለማጠናከርና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሰፈሩ ጉዳዮች አተገባበር ቅደም ተከተል በአሁኑ ወቅት የጥቂት ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት የተከተሉትን አፍራሽ አቅጣጫና በየአህጉሩ እየመሠረቱት ያለውን የግንኙነት መረብ (ኔት ወርክ)ሊመክትና በሂደትም ሊያከሽፍ በሚችል አግባብ መሆን ይገባቸዋል። ከዚህም አንፃር በዕቅዱ ውስጥ በውጭ አገሮችም ሆነ በአገር ውስጥ የሚከናወኑ ጥናቶች ለብቻቸው ተነጥለው የሚሰሩ ሳይሆን የኮሚኒቲ አባላትን እያሰባሰብን መረጃ እየሰጠንና እያደራጀን ጎን ለጎን የምንተገብረው ይሆናል" ይልና ገጽ 22 "ከውጭ አገር መጥተው በቀጥታም ሆነ በሽርሽርና በኢንቨስትመንት ላይ ለሚሠማሩና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር ለሚጠይቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያለው አሠራር ተፈትሾ ቀልጣፋ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት" ይላል።

ወያኔ ከዚህ በላይ ያሰራጨውን ሰነድ ተጠቅሞበታል። ከውጭ አገር እድሉ ስላላቸው ብቻ ገብተው ነዋሪውን ሕዝብ የተጋፉ ብዙ ናቸው። አንዳንዶቹ የድሃ ቤት ፈርሶ መሬት ሲሰጡ በደስታ የተቀበሉት ብዙ ናቸው። ባንዳ ማለት ከዚህ የበለጠ ምንም ነገር የለም። ስለ ባንዳ ይህን ከጻፍኩ በኋላ ስለ ወልቃይት ልጆች ወያኔን ስለደገፉት አንዳንዶች ልጽፍ በማሰቤ ነው። ከላይ እንደጠቀስኩት ባንዳ ማለት ለሆዱ ያደረ ማለት ሲሆን ከወልቃይት ልጆች አንዳንድ ባንዳ የሆኑ አሉ። ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከቆጠረ ጀምሮ እምላክ ከልሎ የሰጠን የተፈጥሮ ደንበር ተከዜ መሆኑ እየታወቀ ባንዶች "እኛ ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬ" አይደለነም አሉ። ስለዚህ ትግሬ ነን በማለታቸው የዘፈን ምሳሌም ከኪሮስ አለማየሁ ዘፈን ልጥቀስላቸው። ድምጻዊ የኪሮስ አለማየሁ፣ "አይበልናዶ" አሉ። ይህን አይበልናዶ የሚለውን የትግርኛ ቃል ወደ አማርኛ ስንቀይረው "አላልናችሁም" የሚል ነው። በትክክል ሳልረዳው ቀርቼ ከሆን እናንተው ባንዶች አስተካክሉኝ። ጎንደሬ እንጂ ትግሬ አይደለነም ያሉት የወልቃይት ልጆች ደግሞ ወያኔን እናንተን ቀደም ጀምረው መክረው ነበር። "ተው ወያኔ አያዋጣችሁም ከወገኖቻችሁ ጋር አትጋጩ" በማለት ሲመክሩ መቆየታቸው አይዘነጋም። ለዚህም ነው አሁን "አላልናችሁም" የሚሉት። ወያኔም የነዚህን ለጥቅም ያደሩ መሆናቸውን በመገንዘብ ገንዘብ ለሚፈልገው ገንዘብ ሰጥቶ አንበሸበሻቸው። አሁንም እነዚህ ወገኖች ከስተታቸው ላይ ስህተት እየጨመሩ መሄድ እንጂ ትምህርት አልወሰዱም። ድምጽዊ ሻምበል በላይነህ ደግሞ "ከጥፋት ላይ ጥፋት፣ከስተትላይ ስተት" ብለዋል።

ግደይ ባሕር ሹም <u>አሞራ</u> በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 202 "ታሪክ ይውቀሳቸው እንጂ አገር እንደያዙ አዲስ የትግራይ ክልል ብለው ደጋግመው በአወጡት የመልክዓ ምድር (ካርታ) ላይ ከአማራው ጋር ለማቀያየም፥ወልቃይትና ጠገዴን ተሻግሮ አዲስ ድንበር ከመጠየቅ ይልቅ ትናንት ደጃዝማች ገብረ

ሥላሴ በወጨፎ ጠመንጃ የሸጡትን አውጋሮ፤የእምኒሐጀር የጎሉጅ፤ የተሰነይንና የከሰላን በር የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኩታ ገጠም ድንበር ለምን አላወሱትም" ሲሉ ጽፈዋል:: ከፍ ተብሎ የተጠቀሰው የታሪክ ጥቅስ የሚያመለክተው ወያኔ ወልቃይትን ወደ ትግራይ ሲከልል ተባባሪ በመሆን አብረውት የቆሙ አንዳንድ የጥቅም ተቋዳሽ ግለሰቦች አልያም አጥንት የቆጠሩ በዘር ትግሬ ነን ያሉ ካልሆኑ በቀር ወልቃይት የትግሬ ነው ብለው ሊቆሙ አይችሉም::

ራስ መንገሻ ስዩም <u>ዶቼ ቨሌ ጀርመን ራዲዮን</u> ሰኔ 11 ቀን 1990 ዓም የአማርኛው ጣቢያ ተጠይቀው ሲመልሱ "ወልቃይት የትግሬ ሁኖ አያውቅም:: የጎንደር ነው" ሲሉ መልሰዋል:: ለትግሬ ከራስ መንገሻ የሚቀርብ የለም:: ምክንያቱም የክፍለ ሀገሩ ጠቅላይ ገዥ ሁነው የኖሩ ሲሆን የዛሬው የትግራይ ትውልድ ባያመሰግናቸውም ለትግራይ ግን ሰርተዋል:: የሚገርም ነገር ደግሞ ዛሬ ተኩራርተው የሕወሓት ታጋዮች ነበርን የሚሉት አንዳንድ የወልቃይት ልጆች ወልቃይት በአማራ የተወሰደብን መሬት ነው ብለው የትግራይን ሕዝብ ሲቀሰቅሱበት እየሰሙ ሕዝባቸውን ሲጨርሱት ተባባሪ መሆናቸው ነው::

ታጋይ ገሠሠ ረታ <u>ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያው ደብተራ</u> የተባለው መጽሐፍ ገጽ 71 " በአማራ የተወሰዱብት እንደ ወልቃይት ጠገዴ ሁመራ አሉውሃና ሌሎች የትግራይ መሬቶች እናስመልሳለን" እያሉ ይቀሰቅሱ እንደነበር የሕወሓት ታጋይ ጽፈዋል:: የወልቃይት የጎንደር ልጆችን እንዚህን የአገር ወዳዶች ያስገደሉአቸው ባንዶች የወያኔ ቡችሎች ናቸው:: የወያኔ ቡችሎች ባንዶች በቁሳቁስ በቤትና በመሬት እየተገዙ ወገኖቻቸውን አስፈጅተዋል:: ዛሬ አገር ወዳዶችን ባንዶች ፈጅተዋቸው ባንዶች በዝተው በትግርኛ አልቅሱ፥ በትግርኛ ዝፈኑ እያሉ ያሰቃዩአቸዋል:: ባንዶች ሌላም ጉድ ሰርተዋል:: አገር ውስጥ ወልቃይት ንዋሪ የሆኑትን ወገኖቻቸውን በትግርኛ ካላለቀሳችሁ በትግርኛ ካልዘፈናችሁ ተብለው ትውልድ አገራቸውን ለወያኔ ሰቀው ወደ ጎንደር እንዲሰደዱ አድርገዋ:: ወያኔ ሁመራን ለትግሬ ሳይሆን ለሱዳን ሲሰጥባችሁ ከእንቅልፋችሁ አትነቁም? በጎንደርና በሌላው አውራጃዎች ቤትና ቁሳቁስ ተቀብላችሁ ከሆነ አገርን አሳልፎ ከመስጠት በታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ለመዳን አታስቡም?የጎንደር ተወላጆች ሆነ ቁጥሩ ይነስ እንጂ ሌላው ኢትዮጵያውያን አይታችኋል ሁመራ የኢትዮጵያ እንጂ የሱዳን አይደለም" ብሎ ሲነሳ እንኳን አትባንኑም?

ማንም ሰው ሳይገባው በልጅነቱ አልያም ባጋጣሚ ሊሳሳት ይችላል:: ፍጹም በዚህ ምድር የለም:: ነገር ግን አዋቂ ማለት ከስተቱ መታረም ነው:: አባቶቻችን ሲተርቱ "አውቆ የሰራ ነቢይ ነው! ሲመክሩት የሰማ አዋቂ ነው" ይላሉ ምክሩን አልሰማ ብላችሁ ቆይታችኋል:: ወያኔ የሚሰማው ካገኘ አንዱን ደብር ካንዱ ደብር ጋር ያለያያል:: ጠብ ለመፍጠር የማይፈነቅለው ድንጊያ የለም:: ለዚህም ዋቢ የሚሆን ወያኔ መንግሥት ከሆነ ጀምሮ ሕዝቡን ባንድነት ሊመራ ያወጣው መርሃ ግብር የለም:: የሚገርመው ነገር መሳሳት የጀመረ ሰው ከስህተቱ መማር አለመቻሉ ነው:: ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም



ብላችሁ ወገኖቻችሁ ሲጎዱ ዝም ብላችሁ ስታዩ መቆየታችሁ አይዘነጋም:: ታዲያ ከ17 ዓመታት እንቅል በኋላ መንቃታችሁ ባልከፋ ነገር ግን የባሰ ደግሞ ስህተት ላይ ወደቃችሁ:: በቅርቡ ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን 10 ትዕዛዝ ያለው መግለጫ አውጥታችኋል::

<u>ከሰሜን አሜሪካ የወልቃይት ጠገዴ</u> ተወላጆች ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ! ገጽ 2 አንቀጽ 1 "የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ እራሱን በራሱ የማስተዳደር ሕገ-መንግሥታዊ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን" ይላል:: ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የሚሰጠው እንዴት መሆን እንዳለበት የተረዳችሁት አልመሰለኝም:: ምናልባት ታይፕ ሲደረግ ሳይታረም ቀርቶ እንደሆን እንጅ ጥያቄያችሁ "የአገሩን ስርዶ በአገሩ በሬ መንደሩን ተወላጁ ያስተዳደር ለማለት ፈልጋችሁ ይሆናል እንጂ ካሳበዳችሁ በቀር ራስ ገዝ ብላችሁ የምትጠይቁ አይመስለኝም:: ወደ ኋላ መለስ ብለን የኢትዮጵያን አስተዳደር ስናጤን በደርግ ዘመነ መንግሥት ራስ ገዝ አስተዳደር የነበራቸው ትንሽ ክፍለ ሀገራት ነበሩ:: ጎንደር 7 አውራጃ 28 ወረዳና 119 ምክትል ወረዳ ያለው ክፍለ ሀገር እንኳ ራስ ገዝ አስተዳደር ይሰጠኝ ብሎ አልጠየቀም:: ሊጠይቅም አይችልም እንኳን ግማሽ አውራጃ:: ወይም ደግሞ ወያኔ አደናግሩ ብሎ ልኮአችሁ እንደሆን እንጂ ይህን ጥያቄ እንደማትጠይቁ ርግጠኛ ነኝ:: ከላይ እንዳልኩት አንድም ሲጻፍ ተሳስቷል አልያም ወያኔ አደናግሩ ብሎ አሂል:: ለኢትዮጵያ ውድቀት ራቢጣ ያመጣው ጣጣ አያልቅምና ምናልባቶ ራቢጣዎች ከትበዋችሁ ይሆን? ለነገሩ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስም ግማሽ ራቢጣ ስለሆኑ አንዳንዶች ወደ አዲስ አበባ ጎራ ስትሉ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊን ውሽማ አልያም ቅምጥ ወ/ት አዜብን ልትጠይቁ ገብታችሁ ሳለ ተከትባችሁ ይሆናል:: ይቅርታ ወ/ት አዜብ ማለቴ በኢትዮጵያ ፍትሃብሔር ህግ መሰረትባልና ሚስት አይባሉም::

<u>መጽሐፈ ሕግጋት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 1161 "ጋብቻ ባንድ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊደረግ ይቻላል:: እንዲሁም ሕጉ በሁለቱ ወገኖች ሃይማኖት ወይም ባገር ልማድ መሠረት የሚደረጉትን ጋብቻዎች ያውቃል (ይቀበላል) ጋብቻ ለማድረግ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በክብር መዝገብ ሹም ፊት ሲቀርቡና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹምም ፈቃዳቸውን ሲቀበላቸው ጋብቻ ተፈጸመ ይባላል" ይላል:: ስለዚህ በሃይማኖት አልያም ደግሞ በባህል ፊት ወይም ደግሞ በህግ ያልተጋቡ በመሆናቸው ባልና ሚስት አይባሉም:: 20 ልጅ ቢወልዱም 60 ዓመት አብረው ቢቀመጡም የሰማኒያ ባልና ሚስት አይባሉም:: አንዳንዴ የጭን ገደር ይባላሉ:: አልያም ደግሞ ውሽማ ቅምጥ ተብለው ይጠራሉ:: በ1967 ዓም ጀብሃ የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ምንሃጅር ላይ ጣላት:: ተብሎ ሁመራ ሲነገር ልጅ ተድላ ወልደማርያም የሁመራን ሕዝብ እየመሩ ኤርትራ መሬት ገብተው ጀብሃ የደበደቡ ስለመሆናቸው ታሪክ የመሰከረላቸው ጀግና ሲሆኑ እናንተ ግን የወልቃይት ጀግኖች ብላችሁ ስም ከዘረዘራችሁበት ላይ የእርሳቸው ስም ሳይጠቀስ ቀረ?::

ለካ ራቢጦችን ደብድበው ያባረሩ መሆናቸውን እናንተንም አስቆጥቶ ኑሮአል:: የራቢጣ ተማሪዮች ቀደም ትግሬ እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም ብላችሁ ሄዳች

ሁ:: ውሳችሁ አድራችሁ ደግሞ ወልቃይት ጠገዴ ራስ ገዝ ያስፈልገዋል ብላችሁ ተነሳችሁ? ገጽ 3 ቁጥር 9 "በወልቃይት ጠገዴ የሚቋቋሙ የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት ትምህርት ቤትና የመሳሰሉት ባስያየምም ይሁን በይዘት በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ታሪክና ማንነት ላይ ተመስርቶ እንዲሆን እንጠይቃለን" ይላል:: ተመልከቱ ቀደም ሲል ወያኔዎች ማንነታችሁን ሊያስክዱ ታሪካችሁን ሊያጠፉ ሕዝባችሁን ሊያስድዱና ሊያደህዩ መሆናቸውን አስመልክቶ ስትንገሩ መኖራችሁን አትረሱትም:: ያም የሚከፈተው ትምህርት ቤት ሆነ ተቋም በማታውቁት ስም በመሆኑ ዛሬ ራሳችሁ ከጥያቄያችሁ አንዱ አድርጋችሁ አቅርባችሁታል:: አበው ሲተርቱ "ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው" ይላሉ::

መከራ መክሮአችሁ ከሆነ የጀመራችሁትን ማጋለጥ ጨምሩበት የተፈጸመውን በደል ዘርዝራችሁ አቅርቡት:: ገጽ 1" ከአብራኩ የተፈጠሩ ተወላጆች ትምህርታቸውን ጨርሰውም እንኳ ያለ ሥራ እየተንከራተቱ ከሌሎች አካባቢዎች እየመጡ ሲቀጠሩ በግልጽ እያየን ነው" ይላል:: ከሕዝባችሁ ጋር አትቀያየሙ ብለው ወገኖቻችሁ መከረዋችሁ ነበር:: ነገር ግን እናንተ ማየት አልቻላችሁም ከ17 ዓመታት በኋላ ማየት ስትጀምሩ ከሌሎች ወገኖቻችሁ ጋር ሁናችሁ መነሳት ሲኖርባችሁ ብሳችሁ ቁጭ አላችሁ:: ከሌሎች አካባቢ እየመጡ ሲቀጠሩ የምትሉት ዛሬ ከወያኔ በቀር ከሌላ ክልል ሐዶ የሚሰራ ማንም የለም:: ስለዚህ ገልጻችሁ መነሳት አልፈለጋችሁም::

ለዚህም ነው ወይ ሀዱ
አልያም አታወናብዱ

የምለው:: የሚገርመው ነገር ደግሞ ይህ ሁሉ ሲሆን ሁመራ ለሱዳን ሲሰጥ መሆኑን ሳትገልጹ መቅረታችሁ ወያኔ አወናብዱ ብሎ የላካችሁ መሆናችሁን ያረጋግጣል:: ይህ ሁሉ ሕዝብ እያለቀና በመሬቱ ላይ ሱዳኖች አርሰው እየበሉና እየተዝናኑ ቅድሚያ መሬታችን ይከበር የሚል ጥያቄ እንኳን ሳይጠቀስ ይቅር? ይህስ እውነትም ወያኔ የላካችሁ ናችሁ:: ቀደም ሲል ባህርዳር ወይዘሪት ለምለም የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ውሽማ ሰብሳቢነት የወልቃይትን ችግር ለመፍታት እንሞክር ተብሎ የታቀደ መሆኑ ሲታወቅ ኋላም በኮሎምቦስ አጓዮ በተደረገው ስብሰባ ከላይ የተነበበው አሳፋሪ መግለጫ ከወጣ በኋላ የተወሰኑ ሰዎች አዲስ አበባ ሐደው ስብሰባ ተደርጎ ያለ ምንም ስምምነት መበተኑ ታውቋል:: ስለዚህ በዚያም ሆነ በዚህ የወያኔ እጅ ያለበት ነው:: ወያኔ ከ300 ሺህ ሕዝብ በላይ ከትግራይ አምጥቶ ወልቃይት አስፍሯል:: የወልቃይት ነዋሪው ሕዝብ ወያኔን ያልደገፈ አገሩን እየለቀቀ ተሰዷል:: የቀሩት ቀንበር የጠበበባቸው መፈናፈኛ ያጡት ናቸው:: ይህ በዚህ እንዳለ እናንተ የራስ ገዝ መብት ይሰጠን ብላችሁ እንድትጠይቁ ተደረገ:: ከዚያ በኋላ ጨዋታው የወልቃይት ሕዝብ ይምረጥ ሲባል ነው:: ከትግራይ ወልቃይት መጥቶ የሰፈረው ሕዝብ "እኛ ወደ ትግራይ እንድንከለል እንወዳለን" ብለው እንዲመርጡ ሊደረግ ነው:: ከዚያ በኋላ የወልቃይት ሕዝብ ትግሬ እንጂ ጎንደሬ አይደለሁም ብሎ ድምጽ ሰጥቷል ሊባል የታቀደ መሆኑን ከውስጥ አወቅ ምንጮች መውጣት ጀምረዋል::



ገጽ 2 "በወልቃይት ጠገዴ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች በዓመት ከመቶ ሽህ ብር በላይ ግብር እንዲከፍሉ ሲደረግ አርሶ አደር ገበሬው ከሃያ እስከ ሠላሳ ሽህ ብር በአማካይ ግብር የሚከፍልበት አካባቢ ነው:: ሌላው ቀርቶ በወልቃይት በመቶ ብር የምትከራይ ጎጆ 30% ለመንግሥት ገቢ የሚሆንበት ሲሆን በአንጻሩ በአዲስ አበባ ከተማ ግን ከሃያ ሽህ ብር በላይ ገቢ ያለው ነው 30% ለመንግሥት ገቢ የሚያደርገው" ሲሉ ጽፈዋል:: ድሮም የወልቃይት ተወላጆች የጎንደር ልጆች ተናግረው ነበር::

ተናግሬ ነበር ከአጥር ተንጠልጥዬ
ሕወሓት ገዳይ እንጂ ገዥ አይሆን ብዬብለዋል::

ይህ እንደሚሆን ቀደም ሲል ጀምሮ የታወቀ በመሆኑ የወልቃይት ሕዝብ ከስደት ላይ ሰደት እየደረሰበት ነው:: አንዴ እሁድ ቀን መምህር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሰብኩ ምዕመናኑ ጭብጨባ ጀምሮ ሞቅ ሳይል በመተው መምህር አባ "የምታጨበጭቡ ከሆነ አጨብጭቡ የምትተውት ከሆነ ተውት" ብለዋል:: ስለዚህ ወያኔን የማጋለጥ ተግባር ከሆነ ጠንክር ብሉና ማጋለጥ ሞክሩ አለበለዚያ ግን አታወናብዱ ተመለሱና ወደ ወያኔ ሕዱ?

ገጽ 3 ከሌሎች አካባቢዎች እየመጡ አካባቢያችንን የሚያስተዳድሩ ወገኖች ባለፉት 17 ዓመታት እንደታየው ጥፋት እየፈጸሙ ሲኑሩና በሕግ ሲጠየቁ የታየበት ሁኔታ መኖሩ እየታወቀ አሁንም በመንግሥት በኩል ይህ ከሌሎች አካባቢ የሚመጡ ሰዎችን በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የመጫን አሰራር ስለቀጠለ ከአሁን በኋላ ይህን መሰሉ አሰራር እንዲቆም እንጠይቃለን" ይላል:: ለመሆኑ ዛሬ ነው እንዴ ያወቃችሁት? ወያኔ ከገባ ጀምሮ ሲፈጽመው የነበረ መሆኑ ተረሳ? ለመሆኑ በተወሰኑ ወረዳዎች ከመቼ ወዲህ ነው የራስ ገዝ ጥያቄ የሚሰጠው? ስለዚህ ገና ብዙ የሚፈተሽ ጉዳይ መኖሩ እንዳለ ሁኖ ትንሽ ጭላንጭል በማውጣታችሁ በእኔ በኩል መልካም ጅምር ሲሆን ለወደፊቱ ከመላው ጎንደር ሕዝብ ጋር አብረን እንራመድ ብላችሁ ትነሱ ይሆናል የሚል እምነቴ ነው:: ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም የምትሉ ካለፈው ስሁተታችሁ ታርማችሁ ከወገኖቻችሁ ጋር አብሮ ቀጣዩ የሁመራ መሬት ዓለም አቀፍ ደንበሩ እስኪታወቅ ብዙ ተግባር የሚጠበቅባችሁ ይመስለኛል::

ይህ በአንዳንድ ግለሰቦች የሚነሳው ጉዳይ እናንተ የወረዳው ልጆችን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ሌሎችን የክፍለ ሀገሩን ተወላጆች ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብረን ዳር ደንበራችን እንዲከበር መታገል አማራጭ የሌላው ጉዳይ ነው:: ሰፈርተኝነት ለማንም አይጠቅምም:: ሠፈርተኝነት የሚያመጣው ለአካባቢው ድክመት እንጂ አንድነት አይሆንም:: የሰፈርተኝነት መነሰኤ ወደ ልዩነት ይመጣል:: ልዩነት ደግሞ ውሎ አድሮ አደገኛ ይሆናል:: ሰፈርተኝነት ወደ ገለልተኝነት ይመራል:: ገለልተኝነት ደግሞ ወደ ቡድን ይዞራል:: ቡድን ደግሞ ወደ ማህበር ይቀየራል፤ ማህበር ደግሞ ወደ ሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅትነት ይለወጣል::

"ማህበር" የሚለው ቃል እንዴት ሊመጣ ቻለ? ማህበር በምን ምክንያት ይመሰረታል? የልማት ማህበር ማለት ምንና ምንን ያጠቃልላል? የሚለውን በጽሞና መመልከት ያስፈልጋል:: ማህበር የሚለውን ቅድሚያ በተረዳሁት መሰረት ላብራራ:: ማህበር ማለት በአባቶቻችን ባህል መሰረት የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች በከተማ ሆነ በገጠር ሰብሰብ ብለው በወር አንድ ግዜ የሚገናኙበት ሲሆን ሃይማኖታዊ ነው:: የወንዶች ማህበር በመላዕክታንና በቅዱሳን በጻድቃን ስም የሚመሰረት ማህበር አለ:: አንዳንድ ማህበር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ሲሆን ግዙፍና ጠንካራ ወሀራዊ መዋጮ ያለው ከመካከል አንዱ ቢቸገር አራጣ ብድር የሚበደርበት ገንዘብ ያለው ማህበር አለ:: እንዲሁም እናቶቻችን የሴቶች ማህበር ሲኖራቸው በብዛት በቅድስት ማርያም በባዕታ በኪዳነ ምህረት ስም የጽዋ ማህበር ይጠጣሉ:: ይህ ከዚህ በላይ የገለጽኩት በብዛት በገጠር ያለና ሃይማኖታዊ የጽዋ ማህበር ነው::

በዘመናዊው የማህበር አጠራር ከወሰድነው ደግሞ የአንድ አካባቢ ሕዝቦች በስራና በሌላ ምክንያት ከሩቅ አገር ይሄዱና ይኖራሉ:: ታዲያ እነዚህ ሕዝቦች በተወሰነ ግዜ እየተገናኙ አብረው ይውላሉ:: የበረቱ ከሆነ ራሳቸውን የሚረዱበት ወይም ደግሞ ለአካባቢያቸው ተባብረው አንድ ነገር ይመሰርታሉ የዚህ አይነት ማህበር አንዳንዴ ከፍና ዝቅ ሲል በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በርታና ደከም ሲል ሳለ አንዳንድ ተንኮለኞች እየገቡ የልማቱን ማህበር ለግላቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ሲሉ ወደ ሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅት ተቀይሯል:: የወያኔ ጥንስስ ቅድሚያ ተጋሩ ይባል የነበረው የልማት ማህበር ሲሆን ሜጫና ቱለማ ይባል የነበረው የልማት ማህበር ወደ ሥነ መንግሥት ፖለቲካ ተለውጦ እነግን የወሰደ መሆኑ አይዘነጋም:: "ልማት ማህበር" የሚለው ትልቅ ነው:: የአንድ ክፍለ ሀገር የልማት ማህበር ቢመሰረት ሊደገፍ የሚገባ ሲሆን የአንድ አውራጃና የአንድ ወረዳ የልማት ማህበር ፈጽሞ ሊመሰረትና ቢመሰረትም ሊሰራ አይችልም:: ሊሰራ የሚገባው በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉ ልጆች በአካባቢያቸው የፈረሰ ቤተ ክርስቲያን ወይም ትምህርት ቤት ለማሰራት አጭር እቅድ ነድፈው ለአንድ መርሃ ግብር ሊያሰሩና ከሌላው ወገናቸው እርዳታም ሊጠይቁ ይችላሉ:: በዚህ በኩል ብዙ ትብብሮች ሲደረጉ ተመልክቷል:: የጎንደር የልማት ማህበር ከተመሰረተ ወዲህ የወያኔን እቅድ የማይደግፍ በመሆኑ ማለትም በጎንደር ክፍለ ሀገር 7 አውራጃ 28 ወረዳና 119 ምክትል ወረዳ መሆኑን በማስተማሩ ወልቃይት ጠገዴንና ከሰሜን አውራጃ የወሰደውን ወረዳ ሕዝብ አልቀበለው በማለቱ አንድ አፍራሽ ሴራ ፈጸመ::

አቶ ክንፌ ገብረ መድህን ተወልደው ያደጉት ጎንደር ዳባት በመሆኑ የሚያውቃቸውን ልጆች አሜሪካ ሰላሉ ራሳቸው ዋሽንግተን ዲሲ መጥተው እንደሚደግፉአቸው ቃል ገብተው ከትልቁ የልማት ማህበር ሌላ ማህበር እንዲመሰረት ሆነ:: በእርግጥ ይህ ራስ አገዝ ጎንደር ማህበር የወልቃይትን ወረዳ ልጆች የኳስ ጨዋታ ላይ ሳይጋብዛቸው ቀረ:: ነገር ግን እነ አቶ በረከት ስምዖን ለማበረታታት ሲጠሩአቸው ከአሜሪካ የሄዱት ልጆች በተለይም አቶ ሀቢቡ ታከለ "በጎንደር ሰላም ይውረድ ከተባለ ወልቃይትና ጠገዴን ሌሎችንም ወረዳዎች ወደ ነበሩበት መልሱ" ብለው በመናገራቸው የወያኔ ባለሥልጣኖች



ተበሳጭተው ወጥተዋል:: ይህም ማህበር ደከም ማለት ሲጀምር ደግሞ የወልቃይት የልማት ማህበር ተብሎ ተመሰረተ ይህንም ማህበር ባንዶች ካልሆኑ ሌሎች የወልቃይት ልጆች ተቃውሞ አሰሙበት የሚሰራ አይመስለኝም:: አሁን በቅርቡ ደግሞ የትኛው አርማጭሆ እንደሆነ ባላውቅም የአርማችሆ የልማትና መደራጃ ማህበር ተመስርቷል:: አርማጭሆ ሁለት ወረዳ ሲሆን ላይ አርማጭሆና ታች አርማጭሆ ይባላል::

እኔ የወረዳ የልማት ማህበር ሊመሰረት አይገባም ስላቸው፣ አንዳንዶች "አንተም ከመሰሎችህ ጋር ሁነው የወረዳ ማህበር ማቋቋም ትችላለል" ይሉኛል:: በእኔ እምነት እንኳን በወረዳ በአውራጃ የሚቋቋም ማህበር ኤድስ ነው:: ኤድስ በሽታ ሕዝብ መያዙ ብቻ ሳይሆን ታማሚውን ጤነኛው ፈርቶ አልቀርበው በማለቱ የኤድስ በሽተኞችን ማግለል እንደሌለብን የሃይማኖት አስተማሪዎች በማስተማር ላይ ናቸው:: ልድገመውና እንኳን የወረዳ የአውራጃ የልማት ማሕበር ኤድስ ነው:: ሕዝብ ከህዝብ የሚያለያይ በሽታ ነው:: ወያኔ የሚፈልገው ይህን ነው:: ታዲያ በዚህ አይነት የልማት ማህበር ሊመሰረት አይገባም:: የጎንደር ሕዝብ አንድ ሁኖ ለልማት እንዲነሳ ስለማይፈልግ የጎንደር ማህበር ከተመሰረተ ጀምሮ እስከዛሬ አንድ ክፍል ቤት አልሰራም::

ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ሲነሳ በተለይ አርማጭሆ ሕዝብ መሬቴን አልሰጥም ብሎ ሲቃወም በውጭ ያሉትን የወረዳውን ልጆች ሰላይ በነበሩ ሰው የአርማጭሆ ልማትና ማደራጃ ማሕበር ብለው እንዲመሰርቱ አደረገ:: እቅዱ ይህን የአርማጭሆ ልጆች ብቻቸውን ለልማት መደራጀታቸውን ሌላው የጎንደር ሕዝብ ሰምቶ አብሮ እንዳይቆም ለማድረግ አስቦ የጠነሰሰው ሲሆን በቅዱ መሰረት ተመሰረተ:: ከዚያም ግማሾቹ የወያኔ ሰዎች እንዳሉበት ሲታወቅ እነሱን የተቃወሙት ለብቻቸው የአርማጭሆ መረዳጃ ማህበር ብለው መሰረቱ:: አልሸሹም ዘወር አሉ ይሉሃል ይህ ነው:: ይህን ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የአርማጭሆ ሕዝብ መሬታችን ለሱዳን አንሰጥም ብሎ ሲዋጋ የወያኔን ጦር መርተው የመጡት የአርማጭሆ ተወላጅ ሻምበል ቻሌ አለሙ ሲሆኑ ከወገኖቻቸው ጋር ተታኩሰው ተገደሉ:: ወያኔ የተወሰኑትን አሳምኖ ለሻምበል ቻሌ ቤተሰቦች መርጃ ገንዘብ እንዲዋጣ ልመና እንዲያደርጉ አሰማራ::

አሽብር ተቆርቋሪ የለለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ወያኔ በቆፈራቸው ጉድጓዶች የቀም ሥቃይ እያየ የወገን ያለህ ይላል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 10 " መረዳጃ ማህበር አቋቁመው ሕብረተሰባቸውን ቢረዱ የሚያስመሰግን ሥራ ነበር:: ነገር ግን ጠግቦ ሲተፋ ሲያድር ለነበረው አንዳንድ የወያኔ ቅጥረኛ ሻምበል/ሻለቃ ድጎማ ለማድረግ መራወጡ የሚያሳዝን ትዝብት ነው:: መረዳት የነበረባቸውስ ከግብርናቸው ላይ እያሉ በነዚሕ ሻምበል/ሻለቃ በታዘዘው የአጋአዚ ጦር የተጨፈጨፉት የድሃው አርሶ አደር ቤተሰቦችን ነበር" ሲሉ የተሰማቸውን ጽፈዋል:: ለምን ገንዘብ አስፈለገ ሲባሉ መልሳቸው "ለሻምበል ቻሌ አለሙ ቤተሰቦችን ልንረዳ ነው" ሲሉም መልሰዋል:: ወያኔ

ከልቡ ካሰበ ለምን ለኮሎኔል ናቃቸው ጫቅሴ፣ቤተሰቦች ይረዱ ብሎ አልጠየቀም:: ኮሎኔል ናቃቸው በሻዕቢያና በወያኔ ጦርነት ወቅት ጀብድ ሰሩ::

ተወልደ ገ/ተንሳይ (ኮ/ል) ባድመ እንደምክንያት የፍፃሜው መባቻ በተባለው መጽሐፋቸው ኮሎኔል ናቃቸውን በተመለከተ ገጽ 389 "በ31ኛ ክጦር የብርጌድ አዛዥ በመሆን በሰኔ 3/90 ዓም አኩሪ ጀግንነት የፈፀሙ፣በዘመቻ ፀሃይ ግባት በደምበ ገዳሙ የነበረውን የጠላት ኃይል እየቀጠቀጡ ግርመ የደረሱ ጠላት ሰኞ ባድመ ብሉ በተነሳበት ወቅት እጅግ አኩሪ ጀግንነት የፈፀሙ በመጨረሻ ማጥቃት የ38ኛ ክ/ጦር አዛዥ በመሆን በሩባተጋሩ የነበረውን የጠላት ኃይል እየደመሰሱ ሽምበቆ የደረሱ ጀግና ወታደር አዛዥ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ጀብድ ለሰራ ገንዘብ እናዋጣ ቢባል እንኳን ከውጭ ጠላት ጋር ነው የተዋጉት ይባል ነበር:: ሻምበል ቻሌ የወያኔ መሳሪያ ሁነው መቆየታቸው ብቻ ሳይሆን መሬት ለሱዳን ይሰጥ ብለው ሲዋጉ የሞቱ በመሆናቸው መዋጮ የሚያስፈልግ መስሉ አይታየኝም:: በነገራችን ላይ ቀደም አርማጭሆ ባንዳ አልነበረም:: የጣሊያን ባንዳ እገሌ ነው ተብሎ ስሙ ሲጠራ ሰምቼ አላውቅም:: ምነው የዛሬው ትውልድ የአባቶቹን ጋሻ ማንሳት አቃተው? እብረን ለደንበራችን ለመሬታችን እንቁም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተነሳበት ወቅት በተወሰኑ የወያኔ ሰዎች ተጃጅለው በመጀመሪያ የአርማጭሆ ልማትና ማደራጃ ማህበር እንዲሁ ደግሞ የአርማጭሆ መረዳጃ ማህበር መመስረታቸው ለአርማጭሆ እየሰሩ ሳይሆን እየጎዱት መሆኑን አልተረዱም:: በጣም የሚገርመው ደግሞ በጎንደር ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ አንቱ ይባላሉ ተብሉ የሚገመቱ ከንዲህ ዓይነቱ ከወያኔ ሴራ ሳያስቡት መግባታቸው እኔን ብቻ ሳልሆን ብዙ ኢትዮጵያውያንን አስገርሟል::

ወያኔ ቅድሚያ ራስ አገዝ ጎንደር ኋላ ደግሞ የወልቃይት የልማት ማህበር፣ ቆይቶ ደግሞ የአርማጭሆ የልማትና ማደራጃ ማህበር በቅርቡ ደግሞ የአርማጭሆ የመረዳጃ ማህበር ብለው እንዲመሰርቱ መክሮ አስመሰርቶአል:: እምነቴ ለአንድ ሀገርና ለአንድ ሃይማኖት ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው ለጥቅም መገዛት የለበትም:: አንድ ሰው ለጥቅም ከተገዛ በዘመኑ ቋንቋ ባንዳ ሲባል በሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ይሁዳ ይባላል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው ሐዋርያት መካከል ይሁዳ አንዱ ነበር:: ነገር ግን ጌታውን ለ30 ብር የሸጠ መሆኑ ታሪክ ይነግረናል:: ጌታችንን ካስገደለ በኋላ በድርጊቱ አፍሮ ገንዘቡንም ሳይበላው ራሱን ሰቅሎ የሞተ መሆኑን ነው መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን የሚነግረን:: ስለዚህ አንድ ሰው ለጥቅም ካደረ ሃይማኖተኛ አይሆንም:: አንድ ሰው ለጥቅም ካደረ ለአገር ተቆርቋሪ ሊሆን አይችልም:: ባንዳና ይሁዳ ይባላል! ስለዚህ ሳታውቁት ተሳስታችሁ ከሆነ መመለስ ይቻላል:: ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ም/13 ቁ 11 "ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፣እንደ ልጅም አስብ ነበር፣እንደ ልጅም እቆጥር ነበር፤ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ" ይላል:: በታሪክ ከመወቀስ ዳኑ::



# ክፍል አምስት

## ምዕራፍ 1

## ለወያኔ ደጋፊዎች የትግራይ ልጆች?

የወያኔ ደጋፊዎች ያልተረዳችሁት ታሪክ ቢኖር እናንተ ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ላለው የኢትዮጵያ መሬት ዳር ደንበር ልትቆረቆሩ ቀርቶ ጠባብ ሁናችሁ በተደራጃችሁበት የክፍለ ሀገር መሬታችሁ እንኳን ተቆርቋሪ ልትሆኑ አልቻላችሁም:: ለዚህም ነው የእናንተው መሪ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ የትግራይን መሬት ለኤርትራ ሲሰጡባችሁ እንኳን ድምጻችሁ አልተሰማም:: እንዳንዶችስ በሚያሳፍር "መሬት ከኤርትራ ሄጉ ስለሰጠን የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ አለብን" እያላችሁ ቅስቀሳ ስታደርጉ የነበራችሁ ናችሁ:: ዛሬ የደንበር ጉዳይ ሲነሳ "ይህ የቅንጅት ወሬ ነው" የሚሉት አባባል ከጠባብነት የተነሳ ነው::

ጌታቸው ወልዴ የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሐምሌ 1985 ዓም ገጽ 2 "ነፍጠኞች ሲፈራ ፍክራ ያበዛል ይባል የለ! መጽሔታችሁ በመሰረቱ የማን እንደሆናችና ምን እንደምትሰራ እናውቃታለን:: ዛሬ ይህች ኢትዮጵያ የምትባለው ፀሐይ ወጥቶላት ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋቸውና በታሪካቸው ኮርተው እየኖሩ ነው:: እነ ነፍጠኞች ግን ዛሬ መሬትና ሰማይ ዞሮባቸዋል! የባሰም ሊዞርባቸው ነው:: ቁጭ ብሎ መብላት ምርጥ መዝናኛ ቦታ ከእንግዲህ አይገኝም:: ሚሊዮን ጊዜ ስለባንዴራ ቢያወሩ በክልል አስተዳደር ባንዲራውን ለማየት አንፈልግም:: ስለአንድነት ሺ ጊዜ ብትደነፉ ከነፍጠኞች የሚመጣ አንድነት እና ተለጣፊ ኢትዮጵያዊነት ገደል ይግባ:: ለአንተ ሥልጣን ሊሰጥህ ነበር ወይስ ለመሐይማን ፕሮፌሰሮች ከታሪክ የማትማሩ በዚህ ጦርነት ተነሳ ብላችሁ በመጽሔፍ ጉራ አታብዙ" ሲሉ ጽፈዋል:: በ1983 ዓም አካባቢ ጀምሮ ወያኔዎች ትቢታቸው እንኳን ሰው አምላክ የሚደፍራቸው አልመሰሉም:: ወያኔዎች መለስ ብለው የአክሱምን ሥርዕዎ መንግሥት አወዳደቅ ታሪክ ቢመረምሩ ኑሮ ይህን የመሰለ ትቢትና ጥላቻ ሊናገሩ አይችሉም ነበር:: ከአክሱም ሥርዕዎ መንግሥት ይቅርና እኛ ከተወለድን ወዲህ እንኳን የቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ገርስሶ ይጥላል ብሉ ያሰበ አልነበረም:: የእርሳቸው መንግሥትም ወደቀ የደርግ መንግሥትም እንዲሁ ወደቀ:: ያውም በኢትዮጵያዊነት ሽማ አሽብርቆ የነበረ መንግሥት ስለዚህ ወያኔዎች ለሁሉም ጊዜ አለውና ባትደነፉ መልካም ነው:: ለነገሩ የኢትዮጵያን ታሪክ በጥሞና ለመረመረው የትግራይ ልጆች ሥልጣን ሲይዙ ሁሌም ብጥብጥ መፍጠራቸው አይዘነጋም:: እኛ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ትግራይ ውስጥ የተፈፀመውን ሥህተት ብንጠቁም "ነፍጠኞች፣ትምኪተኞች" እንባላለን::

እስኪ ከትግራይ አብራክ የወጡት አቶ ግደይ ባህር ሹም የጻፉትን መጽሐፍ ጥቅስ እንውሰድ፡፡

*<u>አሞራ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 231 "የዛሬውን ትውልድ አይበለውና ትግሬ ለእምነቱና ለጀግንነቱ ከአባቶቹ ጀምሮ በታሪክ ያስነገረ ነበር፡፡ እንደአሁኑ የትግሬ ወጣት ትውልድ ለጥፋት ለመገንጣጠል ሳይሆን ጥንት አባቶቹ ውሻ የጊታውን ንብረት አጥብቆ እንደሚጠብቅ ሁሉ የዱሮው የትግራይ አርበኛም አገሩን ኢትዮጵያን በሰሜን ቀይ ባሕር በጥቂት ባንዶች ተመርተው ከሚዝቱ ከባእዳን ወራሪ ኃይላት በፊታውራሪነት ጠብቆ እየተዋጋ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት አረበኞች ጋር በመተባበር አገራችን በወራሪ ሳትቆራረስ አንድነትዋል አስከብሮ ያቆየት አገር ለመሆንዋ በዘመኑና በጊዜው የነበሩ የታሪክ ጸሐፊዮች ነግረውናል፡፡ ታዲያ ወደ ባህሪው ልመለስና ልግለጽላችሁ የምፈልገው ትግሬዎች በአርበኝነት ድል ሲኖራቸው ለስምምነት በጠባይ ከፉኛ ነሳቸው፡፡ እንደ ውሻ እርስ በእርስ መናከስ ማን ችሎአቸው፡፡ ቅናት ምቀኝነት ጭቅጭቅ ተዘርታ የበቀለችው ከትግሬ ጎሮ ነው ብል ፍጹም አልተሳሳትኩም፡፡ የትግራይን ምድር ዙረው ቢምሱት የትም ቦታ የንትርክና የእልክ ሥር አይጠፋም ማለት እችላለሁ፡፡"*

*"እርስ በእርሱ የሚናከስ ጎሳ (ዘር)ለመሆኑ ዘመነ ነገሥታትና ዘመነ መሳፍንት ጓላም ዘመነ ነገሥታት ታሪክ ላይ በጥሞና ብትመለከቱት የትግራይ መሳፍንትና ነገሥታት ተስማምተው የኖሩበት ዘመን ግልጽ አይደለም፡፡ ለረጅም ዘመናት ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ ያለፉት የትግራይ ነገሥታትና መሳፍንት አብዛኛዎቹ ሥልጣናቸው በኃይልና በጦርነት የተቀሙ ነበሩ፡፡ የእያንዳንዱ ንጉሥ ሠራዊት ለንጉሡ በጣም ታማኝ ሲሆን ነገሥታቱ ወይም መሳፍንቱ ግን ተስማምተውና ሥልጣኑን ተከፋፍለው በሰላም መኖር አይወዱም አልለመደባቸውም ነበር፡፡ ከአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ጀምሮ አብዛኛዎቹ አንዱ አንዱን እየደቆሰ ንጉሥነትን ይቀማ ነበር፡፡ አያሌ ታሪክ ጸሐፊዮች ጠቅሰውታል፡፡ ይህ የአሁኑ የትግራይ ትውልድም ድሮ ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ በወረሰው ባህሪው መሠረት እርስ በእርሱ ተስማምቶና ተማምኖ መኖር አይችልም፡፡ እያንዳንዱ አንዱ በአንዱ ለማጥፋት ተንኮል እየሰማ ከእገሌ ብቻ መሆን አለብኝ የሚል ትዕቢትና ትምክህት ወጥሮት የወገኑን ድርሻ ነጥቆ ለብቻው አትረፍርፎ ለማከበት ወገኑን ለማጥፋት በግልጽና በእጅ አዙር ሲተነኩልና ሲተናነቅ ይታያል" ሲሉ ጽፈዋል፡፡*

ወያኔዎች እናንተ ለሕዝብም ለአገርም የምትበጁ አይደላችሁም፡፡ ኢትዮጵያን ልትሸጡ የተነሳችሁ ናችሁ፡፡ አንዱን ዘር ካንዱ ጋር እያጋጫችሁ በማለያየት የኢትዮጵያን ሕዝብ አብሮ ለጋራ ጥቅሙ እንዳይቆም እያደረጋችሁ ነው፡፡ በእናንተ እምነት ከትግራይ በስተረቅ በሌሎች ክፍለ ሀገራት ችግር እንዲፈጠር መርዝ በመርጨት ላይ ናችሁ፡፡ ይህንም የምታደርጉት የእናንተ ፍላጎት ብቻ እንዲሟላ ስለምታስቡ ነው፡፡ ሻዕቢያ አይደር ትምህርት ቤት ሕጻናትን ፈጅቶ የትግራይ ወረዳዎችን ሲይዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅጽበት አብሮአችሁ ቆሞ አቅም ያለው ዘምቶ አቅም የሌለው በጸሎቱ የልጆች ደም ተመልሶ የተወሰደ



መሬት ተመልሶ ገብቶአል፡፡ ነገር ግን ከ70 እስከ መቶ ሺህ ሕዝብ ያለቀበትን መሬት የሰጠ ገዥያችሁ ነው፡፡ በሂጉ የተወሰደ መሬት ሕጋዊ አይደለም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጮህ እናንተ ድምጻችሁ ጠፋ? ከአገር ውስጥ ያሉት አንዳንድ ችግር ኑሮባቸው ይሆናል፡፡ ነገር ግን ውጭ አገር ያላችሁ የወያኔ አባላት ምን ዝም አሰኛችሁ? ለወደፊቱ የወሰን ጉዳይ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ክፍለ ሀገር ይልቅ በትግራይ ላይ ያነጣጠረ ይሆናል፡፡ በተለይም በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አቅዋም ኢትዮጵያን ማድቀቅ ሲሆን የእርሳቸው አቅዋም ትግራይን ያለሙ ይመስለናል፡፡ ይህ በጥሞና ታቅዶ የተሰራ መሆኑን የወያኔ ደጋፊዮች አልተረዱትም፡፡ እነሱ የሚያዩት በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በስልጣን ላይ መቀመጣቸውን ልማቱ ከሌላው ክፍለ ሀገር ይልቅ ትግራይ መልማቱን ሌላውንም አንዳንዱን ቁሳቁስ በመመልከት ሲሆን አርቀው አላሰቡም፡፡

<u>ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ኤምባሲ፤ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት</u> የተሰኘው መጣጥፍ ገጽ 7 "ዋና ዋና ተግባራት የአክራሪውን የተቃዋሚ ጎራ ለማዳከም እንረዳ በውጭ አገሮች ያሉ ቀንደኛ አስተባባሪ የሆኑ አባላትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ፣ ከዋናው መ/ቤት በሚደርሳቸው የእነዚህ አክራሪዎች የተለያየ መረጃ /በዘር ማጥፋት ወንጀል በገንዘብ ዝርፊያ በመንግሥትና በሕዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት አላግባብ ተጠቅመው የኮበለሉትን ወዘተ.. ለአብዛኛው የኮሚኒቲ አባላት ማጋለጥ የሚያስችል የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት፡፡ከእነዚህ መካከል በዘር ማጥፋትና የሕዝብና የመንግሥት ንብረት በመዝረፍ የተሳተፉትን መሪ-ተዋንያን በሕግ ለመጠቀም የሚያስችል የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማካሄድ ተጠያቂዎቹን ለፍርድ ማቅረብ፡፡ አክራሪ ተቃዋሚዎች ከሚኖሩባቸው አገሮች መንግሥታት ጋር በድፕሎማሲያዊ መስመር በመገናኘት የአገራችንን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን በየአገሮቻቸው እንዲካሄዱ የተለያዩ የሕግ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ነጥቦችን በማንሳት በጋራ መተባበር የሚቻልባቸውን ሁኔታዎችን መፍጠር ከዚህም አንጻር የአክራሪ ተቃዋሚዎቹ መሪዎች የሚኖሩባቸውን አገሮች ዜግነት የወሰዱ ስለሆነ በእኛ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው የእነሱንም ሆነ የአገራችንን ሕጎች በመጥቀስ ማስረዳት አክራሪ ተቃዋሚዎቹ ሕገ-ወጥ የማስፈራሪያ መንገዶችን በመጠቀም ንፁሃን ዜጎች በሰላም የሚኖሩባትንና የፈለጉትን የፖለቲካ አቋም እንዳያራምዱ ተፅዕኖ የሚያደርጉና የአገሮቹን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የሚጥሱ መሆናቸውን ማሳየት" ይላል፡፡

ከዚህ በላይ የተጻፈው መረጃ የሚያመለክተው እያንዳንዱ ሰው ባለው አገር ፍቅር ተጠቅሞ ለትውልድ አገሩ ለማሰብ ሲነሳ በውጭ አገር ያለው የወያኔ አባላት ያልተባለና ያልሆነ ነገር እየሰሩ ይወነጅላሉ ማለት ነው፡፡ ለእነሱ መመሪያ የሰጣቸው ከአዲስ አበባ መሆኑን ከላይ የተነበበውን መመልከት ይቻላል፡፡ ውጭ አገር ያለውን ኢትዮጵያዊ በዚህ መልክ ካስቃዩት አገር ቤት ያለውን ኢትዮጵያዊማ ያለበት ችግር ማን ቆጥሮ ይዘልቀዋል፡፡ ስለዚህ በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በአገር ቤት ወያኔ የሚያደርገውን ድርጊት ትክክል

አይደለም ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ ድምጹን ያሰማ በወያኔዎች ሰላይነት ይሰቃያል ማለት ነው። ወያኔዎች ሕግና ሥርዓት እናስከብራለን ብለው ያላዝናሉ። ደግሞም በዓለም አቀፍ ሕግ እንመራለን ብለውም ይጮኻሉ። አንድ ወንጀለኛ ሰው በሰራው ወንጀል ተከሶ ይታሰራል እንጂ ንብረቱ ይዘረፍበታል የሚል ሕግ የለም።

ሻለቃ መላኩ ተፈራ ኢትኦጵ መጽሔት ቅጽ ቁጥር 7 ታሕሳስ 1992 ዓም ገጽ 40 "ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ወያኔ-ሻዕቢያ/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በመኖሪያ ቤቴ በቀጠና 5 ከፍተኛ 9 ቀበሌ 09 የቤት ቁጥር 213 የነበረኝ ንብረቴ በሙሉ በወያኔ-ሻዕቢያ/ ኢሕአዴግ ከመዘረፉም በላይ ከጂቡቲ ስመለስ የነበረኝ ንብረትም የማዕከላዊ ምርመራ ማስተባበሪያ መምሪያና የልዩ አቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ባለስልጣናት አቶ ዘርዓይ ይህደጎ፣ ሻለቃ ጣሰው መለስና ግብረአበሮቻቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 422/ለን በመተላለፍ ቀምተውኛል። ያለ ሕግ በጉልበት የተወሰደብኝ ንብረቴ በሙሉ እንዲመለስልኝ 5 ጊዜ ለጻፍኩት ማመልከቻ ከባለስልጣናቱ የተሰጠኝ መልስ ንብረቱ ሳይሆን እንደተለመደው ተራ ስድብ ዛቻና ማስፈራሪያ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ሁለት ትምህርት ይሰጠናል።

1ኛ ይዘገያል እንጂ የሰው ልጅ ፍርዱን የሚያገኝ መሆኑን ነው። ሻለቃ መላኩ ተፈራ በሕዝብ ላይ ያደረጉት ግፍ እርሳቸው እንዲሁ እስረኛ መሆናቸው። የእርሳቸው ስልጣን የማይገረሰስ መስሎአቸው ነበር ያን ሁሉ በደል በሰው ላይ ሲያደርሱ ነበሩ። 2ኛ ወያኔዎች የኢትዮጵያውያንን ንብረት መዝረፋቸው ነው። ሻለቃ መላኩ እንዴ ታስሬአለሁ ብለው በመጻፋቸው እንጂ ብዙ ሕዝቦች እንገደላለን እያሉ ያላወጡት ቤቱ ንብረቱ በወያኔ የተዘረፉ ብዙ ናቸው። በውጭ የቀሩ አዛውንት የነገሩኝ "ከአዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ውጭ ስወጣ ቤቴን ለአንድ ዳኛ በ1000 ብር አከራይቻው መጣሁ። ብዙም ሳይቆይ ወያኔ ገባ። ወያኔዎች ወዲያውኑ ቤቴን ወርሰው ለዚያው ዳኛ በ150 ብር አከራዩት። በወኪል ክስ ስመሰርት ክሱን የሚያየው ሰው ያ ዳኛ ሲሆን የራሱን ቤት ሰርቶ አከራይቶ በ150 ብር ክራይ ይኖራል። ክሱ 12 ዓመት እስካሁን አልተፈረደም" አሉ። ወያኔዎች የመንግሥት የሆነውን ንብረት ሳይሆን የተራ ዜጎችን ንብረት ሳይቀር ወርሰዋል።

በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የነበሩ የተወሰኑ ግለሰቦች ያከማቹትን ንብረት ደርግ ወረሰ። ይሆን ከግለሰቦች የወረሰውን ንብረት የመንግሥት ንብረት አድርጎ ይዞት ነበር። ወያኔ ይህን የመንግሥት ንብረት ሸጦ ብሩን ከራሱ ካዝና አስገብቶ በተለያዩ የወያኔ አባላት ስም አከፋፍሎ ትግራይ ውስጥ ልማት እንዲለማ አድርጓል። መፈከራቸው "ትግራይ እስክትለማ ሌላው አገር ይድማ" ብለው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሳያፍሩ አወጡት። እናደርጋለን ብለው ባሰቡት መሰረት አደረጉ በመላ ኢትዮጵያ የልማት አውታር ለመዘርጋት ታቅዶአል በማለት ቅስቀሳውን ሲያናፉት ቆዩ እውነቱ ግን ልማት ሲለማ የታቀደው ትግራይ ውስጥ ብቻ መሆኑ ከዚህ ዝቅ ብሎ ያለውን ሠንጠረዥ ያመለክታል።



ወልዱ ሃይሌ ሩሕ መጽሔት 1ኛ ዓመት ቁ 1 ጥቅምት 1993 ዓም ገጽ 10 "የመሪዎች የልማት ራዕይ ለአንድ አገር ልማትና ብልጽግና የወሳኝነት ድርሻ አለው። እይታው ከአድማስ አድማስ የሰፋ መሪ ማግኘት እንደመታደል ይቆጠራል። ሰላምና መረጋጋትም ይኖራል። ራዕይ በዘርና በተወለደበት አካባቢ ብቻ የተሸበበ መሪ ለተወለደበት አካባቢም ሆነ ለአገሩ ጠንቅ ከመሆን ሌላ ምንም ፋይዳ ያለው ተግባር ሳይከናወን ያልፋል። ፕሬስና ኢንፎርሜሽን መምሪያ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ዓይነት ኢንቨስትመንት በየትኛው ክልል ማካሄድ እንደሚቻል የሚጠቁም ነው የተባለ ብሮሸር ተዘጋጅቷል። በብሮሸሩ ውስጥ እየደተጠቆመው ከሆነ ከሐምሌ 1984 እስከ ጥቅምት 30/1992 ዓም ባሉት ጊዜያት 41.54 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያላቸው 5061 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል። እስከ መጋቢት 30/1991 ባሉት ጊዜያት ፈቃድ አግኝተው ስራ የጀመሩት 1469 ፕሮጀክቶች ብቻ መሆናቸው ተገልጿል። የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ባለሃብቶች መካከል 3/4ኛ የሚሆኑት ፕሮጀክቶቻቸውን በስራ ላይ ለማዋል ያልቻሉበትን ምክንያት በዚህ ጽሑፍ በዝርዝር ለማቅረብ ያዳግታል" ሲሉ ከጻፉ በኋላ ገጽ 11 ከዚህ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ለንባብ አቅርበዋል።

| ክልል | የሕዝብ ብዛት | የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተመዘገበ ካፒታል | የሥራ ፈቃድ ያገኙ ባለሀብቶች | ሥራ የጀመሩ ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 3,593,000 | 4.24 ቢሊዮን ብር | 401 | 279 |
| አፋር | 1,185,000 | 572.70 ሚሊዮን ብር | 82 | - |
| አማራ | 15,860,000 | 3.106 ቢሊዮን ብር | 399 | 124 |
| ኦሮሚያ | 21,694,000 | 6.48 ቢሊዮን ብር | 1149 | 399 |
| ሶማሌ | 3,,602,000 | 144.97 ሚሊዮን ብር | 19 | 7 |
| ቤኒሻንጉል | 523,000 | 331.78 ሚኒዮን ብር | 44 | 21 |
| ደቡብ ሕዝቦች | 12,132,000 | 2.13 ቢሊዮን ብር | 624 | 344 |
| ጋምቤላ | 206,000 | 56.53 ሚሊዮን ብር | 15 | - |
| ሐረሪ | 154,000 | 441.01 ሚሊዮን ብር | 1973 | 255 |
| አዲስ አበባ | 2,424,000 | 21.47 ቢሊዮን ብር | 136 | 13 |
| ድሬደዋ | - | 35.38 ሚሊዮን ብር | 219 | 19 |
| ድምር | - | 41.54 ቢሊዮን ብር | 5061 | 1469 |

ከዚህ በታች ደግሞ የማቀርበው ዝርዝር በኢትዮጵያ ውስጥ የአንድ ጎሳ መንግስት የተመሰረተ መሆኑን ያሳያል። የአንድ አገር መከላከያ ኃይል በአንድ ጎሳ ብቻ ተይዞ እንዴት ሕዝብ ሰላም ይኖራል።

ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ነሐሴ 1996 ዓም ገጽ 23 "የችግራችን አንዱ መፍትሔ ከእንግዲህ በግልጽ መነጋገር ነው ብለናል። በአሁኑ ጊዜ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ70 ሚሊዮን በላይ ነው:: ከዚህ ውስጥ ሕወሓት እወክለዋለሁ የሚለውን ከ3.4 ሚሊዮን የሚሆን የትግራይን ሕዝብ ነው:: ሕወሓት ማለትም የትግራይ ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት አስኳል ነው:: ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ወኪል ስለመሆኑ እርግጠኛ ባንሆንም ዛሬ በአገራችን የሚሰራው የተሳሳተ ተግባር ግን የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት አለመሆኑን አፋችንን ሞልተን እንናገራለን:: ይልቁንም የትግራይ ሕዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በማስተናነት በሕዝብ ሥልጣን ላይ የመቆየት ዓላማ ያላቸው አጥፊ ግለሰቦች በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ እየሰሩ ናቸው የሚል ጥርጣሬ አለን:: የእነዚህ ግለሰቦች ጠባብ ፍላጎት ግን ለዛሬው ሰላማችንና ለተከታታይ ትውልዶች ጦስ እንደሚሆኑ ይታየናል:: አሁን ሰሞኑን ከተሾሙት 17 ጄኔራሎች መካከል ከ10 በላይ ሕወሓት የበቀለበት የአንድ ብሔረሰብ አባላት ሆነው ተገኙ:: ይሉኝታ የለም! ያሳፍራል! የፌዴራሉ ሕገ.መንግሥት አንቀጽ 87/1 ግን የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮችን የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል ይላል:: ይህ ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጽ የሠራዊቱን አመራር አይመለከት፤ እንደሆን አናውቅም:: በመጨረሻ ጥቂት ጥያቄዎችን እንጠይቅና ሃሳባችንን መቋጫ እንባጅለት:: የሸዋ አማራ አገዛዝ እያሉ የመጡት ዛሬ እነሱ ምን እየሰሩ ናቸው? በዚህ አካሄድ በአገራችን ሰላም ይኖራል? በየሕዝባቸው ስም ተደራጅተው ኢሕአዴግን መሥርተዋል የሚሉ ወገኖች ምን ይላሉ? በመሰረቱም ይሆን ኢ-ፍሀትሓዊ ሥርዓት እየተንከባከበ ያለው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አሁን በተያዘው የተሳሳተ መንገድ ሰላም ጠፍቶ ጥፋት እንዳይከተል የሞራል፤የሕግም ኃላፊነት አለበት:: የተሾሙት ጄኔራሎች ማን ናቸው?"

| የተሰጣቸው ማዕረግ | ስም | ብሔር |
|---|---|---|
| ሜጀር ጄኔራል | ሰዓረ መኮንን ይመር | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ብርሃነ ነጋሽ በየነ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ታደሰ ወረደ ተስፋዬ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ዮሐንስ ገ/መስቀል ተክለ ማርያም | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ገዛኢ አበራ ደስታ | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | መሃሪ ዘውዴ ገ/ማርያም | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይለ ሥላሴ ገ/ሚካኤል | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ፀጋየ ተሰማ ንጉሥ | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይለ ሥላሴ ተ/ ኃይማኖት | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ሙሉጌታ በርሄ ይልማ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ዓለሙ አየለ ተሰማ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ተመስገን አበበ ካሳ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | አሳምነው ፅጌ ተበጀ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ባዩ ወንድ አፈራሁ | አማራ |



| | | |
|---|---|---|
| | ኃይሌ | |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይሉ ጎንፋ ኢ.ዶሳ | ኦሮሞ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | አልሀዲ መሀመድ ሰይድ | አይታወቁም |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ፍስሀ ኪዳኑ ፈንታ | አይታወቁም |
| ምንጩ | አስኳል ጋዜጣ | ነሐሴ 11 ቀን 1996 ዓም |

ወያኔ በርሃ የገባሁት የአማራ የገዥ መደብ ጭቆና ስላበዛብኝ ነው እያለ ያላዝን እንደነበር አይዘነጋም:: በደርግ የነበረውን ይቅርና ዘረኛ ነበር ተብሎ የሚወቀሰው የአጼው መንግሥት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተካፍሎ የሰራ መሆኑን አማራ ያልሆነ ቢመሰክር መልካም ይሆናል:: ይህን እውነታ ጥሩ አድርገው የሚያውቁ አምባሳደር አሐዱ ሳብሬ እንዲል ይላሉ::

አምባሳደር አሕሱ ሳቡሬ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 1 ቁ 6ጥር 1996 ዓም ገጽ 32 "አማራው የርዕሠ ብሔርነቱን ሥልጣኑን ይዟል ይባል እንጂ በእውነቱ ሥልጣኑን አካፍሎ ነው ከሌሎቹ ጋር ሲሰራ የኖረው:: አማራ ስለሆነኩ ሥልጣኑን ለብቻዬ ይገባ ልግዛ ብሎ ያለበት ጊዜ አልነበረም:: እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ተነስቶ አያውቅም" ሲሉ ጽፈዋል::

የህወሓት ኮሞኖስት ሃይል የ10 ዓመት ጉዞ ግምገማ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 12 የአማራ ገዥ መደቦች ተቀናቃኝ የነበሩትን የትግራይ ገዥ መደቦች ለማዳከም ሆን ብለው የትግራይን ሕዝብ ለማደህየት በመንቀሳቀስ በህዝብ ላይ ከፍተኛ አድሎዎን ስለፈፀመበት በትግራይ የነበረው ብሔራዊ ጭቆናም እጅግ አስከፍ ነበር" ይላል:: ይህ ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚያሳየው የትግራይን ሕዝብ ፀረ አማራ አድርገው ለማስነሳት በማሰባቸው ነው:: ለነገሩ ተሳካላቸው ብዙም ዘር ዘሩ የሀሰት ታሪክ አጻፉ የትግራይን ደራሲያን ሁሉ አሳመኑ:: ለዚህም ከ1984 ዓም ወዲህ ብዛት ያላቸው የሐሰት መጽሐፍ ተጻፉ:: በተለይ ትግሬን ትልቅ ለማድረግ ሌሎችን ክፍለ ሀገር ለማውደም ታጥቀው ተነሱ:: ወሎንና ጎንደርን ሕዝቡን በመፍጀትና መሬቱን ለመያዝ ብዙ ጣሩ:: የሀሰት ስብከት የሰበኩ መሆናቸውን እኛ ሌሎች ከምንጽፈው ይልቅ ራሳቸው ወያኔዎች የጻፉት ዋቢ ይሆነናል::

ታጋይ ገሠሠ ረታ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያው ደብተራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 71 "የህወሓት መሪዎች የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ በተለይም ለጋ ወጣቱ ወደ ትግሉ ሜዳ ለማሰለፍ ይጠቀሙበት ከነበረው ሌሎች የቅስቀሳ ዘዴዎች አንዱ በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ፕሮፓጋንዳ መካሄድ ነው:: የአማራ ገዥ መደቦች የትግራይ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶች ናቸው: ለስደት የዳረጉትን አማሮች ናቸው:: በአማራ የተወሰዱበት እንደ ወልቃይት ጠገዴ ሁመራ አሉውሃና ሌሎች የትግራይ መሬቶች እናስመልሳለን ወዘተ እያሉ ነጋ ጠባ በመቀስቀስ ሕዝቡ በሌላው ወገኑ ላይ የከረረ ጥላቻ እንዲኖረው ለማድረግ ይሞክሩ ነበር:: ይህንንም በተጨባጭ በዘፈናቸውና በፅሁፋቸው ተቀርፆ

የሚገኝ ሐቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ቅስቀሳ አድርገው የትግራይን ወጣት አሰልፈው ደርግን የጠላሁን ሁሉ ሰብስበው እያስመሩ ሥልጣን ያሉ:: የኢትዮጵያውያንን ክብርም አዋረዱ::

ሊቀ ጠበብት መድኃኔ ታደሰ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ግንቦት 1997 ዓም ገጽ 8 "በሀገራችን አንድ ኃይል ብቻውን ማስተዳደር የሚችልበት ሁኔታ የለም" ሲሉ ጽፈዋል:: ለአንባቢያን ማሳሰቢያ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የወያኔ ቡድን ጠባብነት የሚጠቀም መሆኑን ባምንም ይህን ለታሪክ ልንጠቀምበት እንጂ ጥላቻን ልናጸባርቅበት አለመሆኑን አሳስባለሁ:: በእኛ በኢትዮጵያውያን መካከል በዘር ልዩነት የለብነም:: ነገር ግን ሥልጣን በሚያፈቅሩ አንዳንድ ግለሰቦች ሕዝብ ከሀዝብ እየለያዩ የሚያጣሉን ቡድኖች ናቸው:: ተመልከቱ ደቡብ አፍሪካን ተመልከቱ የአሜሪካን ሕዝብ ጥቁሩን ሕዝብ እንደ እቃ ይጫወቱበት የነበሩት ዛሬ ወጣቱ ነጭ ቀርቶ አዛውንቶች የአፍሪካውያንን ልጅ ርዕሠ ብሔር አቶ ብራክ ሁሴን አባማን የመረጡት ቂም በቀል ባለመያዛቸው ነው:: በእኔ በራሴ ከማንም ጋር ቂምና በቀል የለኝም:: አገሬን የገደሏትን ሕዝቧን ያጠፏትን ግለሰቦች ግን መጥፎ ተግባራቸውን መጻፍ ማለት ጥላቻ ማብዛት አለመሆኑን አምናለሁና ሌሎች ጠባችን በአመለካከት እንጂ በጎሳ በሃይማኖት አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል እላለሁ::

አቶ ስዬ አብርሃ ዋሽንግተን ዲሲ ኢትዮጵያውያንን ስብሰባ ጠርተው ንግግር ሲያደርጉ የሰሙ አቶ ብርሃኑ በላይነህ፣ እንዲህ አሉ ተብሉ ሰማ:: "ታስሮ መውጣት እንደዚህ አርቆ የማሰብ ጭንቅላት የሚያሰፋ ከሆነ የወያኔ ባለሥልጣኖች ሁለት ሁለት ዓመት ቢታሰሩ የጠባብ ሸሚዛቸውን አውልቀው ይጥሉት ነበር" ብለዋል አሉኝ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ሰላምንና አንድነትን በመሆኑ አስቀድሞ "ተሰባበሩ ወይ ተባበሩ" የሚል መፈክር አንስቶ ለብዙ ዓመታት ከሎሽ በኋላ ቅንጅት ተመስርቶ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም ታሪካዊ ምርጫ አድርጎ ነበር:: መራሹ ወያኔ ቀደም ሲል የመንግሥት ካዝና ሲገለብጥ የለመደ የምርጫ ኮረጆ ገልብጦ ምርጫውን አሸንፌአለሁ አለ:: አላሸፈንክም! በሚል ክርክር ከቆየ በኋላ በተፈጠረው ግርግር 193 ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች አለቁ:: ወዲያው የቅንጅትን መሪዎች አስሮ እኔ ያልኳችሁን ካልፈጸማችሁ የሞትና የእድሜ ልክ እስራት እፈርድባችኋለሁ" ብሎ በዛተው መሰረት ፍርድ ጥፋተኞች ናችሁ ብሎ ፈረደ:: የወያኔ አባላት አንድ እንድትገነዘቡት የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቂመኛ ሕዝብ አለመሆኑን ለአቶ ስዩ አብርሃ ያደረገው አቀባበል ምስክር ሊሆን ይገባል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አቶ ስዩ አብርሃን ይቅር ያላቸው ያጠፉት ጥፋት አንሶ ሳይሆን በመጨረሻው ሰዓት ለኢትዮጵያ ጥቅም ሲሉ በመታሰራቸው ምክንያት መሆኑን ልትረዱ ይገባል::

እ!ወልቃይት ያልታተመ!
ወያኔ አሁንስ ምን ትሉ
ውሉውና ውሉ ከጠላቱ ጋራ
ለእሀት ለወንድሙ ትልቅ ባላንጋራ



የባድሜ ሽንፈት በቋራ ሲከሰት
ያውም ጨካኝ በጣም የለየለት
ግዳይ ሳቀረበ ከሞተ አስከሬን ላይ የቆረጠ ለአንገት
ኧረ ጎበዝ ወያኔ ምክሩ ሳለፈው ግድየለም
ጦቢያ ፀንታ ኖረች በአባቶቻችን ደም
ትግራይ በስምህ ሲነገድ በስምህ ሲኮራ
አየን የጠጅ ልጅን ውሉውና ውሉ ከጠላቱ ጋራ" ሲሉ ጽፈዋል::

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ለመታደግ የተፈጠርኩ ነኝ ይለናል:: ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክ ስንቃኝ ግን የትግራይን ሕዝብ ሌሎች መንግሥታት ካጠፉት ይልቅ ያጠፋው ወያኔ መሆኑን ነው:: ሻዕቢያን ለመርዳት የሻዕቢያ ደጀን ሁኖ የትግራይን እንቡጥ ወጣቶች በኤርትራ ምድር ደርግን እንዲገጥሙ አድርጎ ፈጅቷቸዋል:: እኛ ይህን እያልን ስንናገር ወያኔዎች "ይህ የነፍጠኞች ወሬ ነው" ይሉናል:: እውነት መናገር ነፍጠኛ ካሰኘ ልባል አላፍርበትም:: ሱዳን ሳለሁ ጀምሮ የትግራይ ልጆች ማለቃቸውን እንሰማ ነበር:: ዛሬ አንዳንድ አባሎቻቸው ከታሪክ ተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ይመስላል ተግባሩን አውግዘው እውነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየገለፁ ናቸው:: ወያኔን ከመሰረቱት 11ዱ የሆኑት አቶ አሰገድ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል እውነቱን ጽፈዋል::

አሰገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል ጋሀዲ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 131 "አንድ ነገር ላስታውሳችሁ:: ህወሓት በሳሕልም ሆነ በመላ ኤርትራ እስከ ከ1976 ዓም ቁጥሩ 65900 ከሆኑ ሠራዊት ተዋግተዋል:: ጀብሃን ተሻግሮ ለማለፍና መንገድ ለማስከፈት የተደረገው ጦርነት ካልሆነ በስተቀር 4 ዓመት ከ9 ወር በላይ ሻዕቢያን ለማዳን የተደረገው ጦርነት የህዝባዊ ግምባርም ሆነ የህወሓት መሪዎች ለአንድ ቀንም ቢሆን በመጽሔትም ይሁን በሌላ የመገናኛ አውታር ዘግበውትም አያውቁም" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 2

## ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም

ገብረ መድኅን አርአያ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሕዳር 1986 ዓም ገጽ 15 "ገና ሕወሓት ሲፈጠር ይዞት የወጣ ፕሮግራም ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት፣በጎሣ (ጠባብ ብሔርተኝተኞች) የተቀነባበረ ለኢትዮጵያ ሳይሆን መጀመሪያ ኤርትራን ለማስገንጠል ቀጥሎም የትግራይ ሪፑብሊክ መንግሥት ለመመስረት የተነደፈ ነው:: አሁን በአስመሳይ ምላሳቸው የሚናገሩት ለኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ የሚለው በጥር ወር 1981 ዓም ቀጥሎም 1982 ዓም ባካሄዱት ጉባኤ ያስራጩት ፍጹም ሕብረተሰቡን ለማወናበድ የወጣ የሽፍን ፖሊሲ ነው:: ኢትዮጵያ ሲሉ ኤርትራ ውጭ ማለት ነው:: መሰረታዊ የወያኔ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም በፍቅር በአንድነት ለመኖር እንዲችል ነው የሚል እምነት የለኝም:: እነዚህ የማሌሊት መሪዎች በሰኔ 1983 ዓም ቻርተር ብለው

ያወጡት በአንቀጽ ሁለት ሐ/ ማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ እስከ መገንጠል (ነፃነት) ይደርሳል በሚል ሐረጋቸው ያወጡት ይፋ ቢሆንም ይህ መገንጠል (ነፃነት) የሚለው አንደኛ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ ካልታገለው በኢትዮጵያና በሕዝቦችዋ የሚያደርሰው አደጋ እጅግ የከፋ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>አሞራ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 202 "ታሪክ ይውቀሳቸው እንጂ አገር እንደያዙ አዲስ የትግራይ ክልል ብለው ደጋግመው በአወጡት የመልክዓ ምድር (ካርታ) ላይ ከአማራው ጋር ለማቀያየም፥ወልቃይትና ጠገዴን ተሻግሮ አዲስ ድንበር ከመጠየቅ ይልቅ ትናንት ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ በወጨፎ ጠመንጃ የሸጡትን አውጋሮ፣የእምኒሐጅር የጎሉጅ፣የተሰነይንና የከሰላን በር የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኩታ ገጠም ድንበር ለምን አላወሱትም" ሲሉ ጽፈዋል::

**Kshsay Berhe <u>Ethiopia:Demcratization and Unity</u>** በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ **284" TPLF and thereby the EPDRF and Ethiopia have been anti Ethiopia from the very beginning, when they wrote a manifesto in 1976 in which they declared their aim to be the independence to Tigray from Ethiopia, thess indiduals had only the borders of Tigray in their program, the Limitations of Tigray, like the lack of a port,"** *ሲሉ ጽፈዋል:: ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ ፀረ ኢትዮጵያ ሁኖ የተነሳ መሆኑን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ የትግራይ ሕዝብ ጠንቀቆ ያውቀዋል::* የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመን ታሪኩ ያስመዘገበው ያስተዋይነቱ የትግዕስቱ ማስረጃ ጠቅሶና ታሪክ ዘርዝሮ ማስረዳት ይቻላል::

ግደይ እቁባይ <u>ልሳነ ሕዝብ</u> መጽሔት ቅጽ 2 ቁ 11 ሰኔ 1997 ዓም ገጽ 3 "አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕወሓትን ከትግራይ ሕዝብ ነጥሎ መመልከት የቻለ አይመስለኝም:: የትግራይ ሕዝብ ስለወደደውና ስለፈለገው አይደለም:: የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት አገዛዝ ይበልጥ የተበደለና የተጨቆነ እንጂ የደላውና የተመቸው ሕዝብ አይደለም:: የትግራይ ሕዝብ ምንም የተሻለ አማራጭ አልቀረበለትም" ሲሉ ጽፈዋል::አንድ ለማሳሰብ የምፈልገው ታሪክ ቢኖር የትግራይን ሕዝብ ሌሎች ድርጅቶች ገብተው ማደራጀት አልቻሉም:: እንዚያ ሕዝቦች ሌሎችን ድርጅቶች ቢደግፉ በበነገታው ከቤታቸው ታፍነው መወሰዳቸው መሆኑን ልናውቅላቸው አልቻልነም::

ብሥራት አማረ <u>ኢትአጵ መጽሔት</u> ቅጽ 4 ቁጥር 044 የካቲት 1995 ዓም ገጽ 23" ለውትድርና አልሰለጥንም ያለ ገበሬ መሬት አይሰጠውም፣የንግድ ፈቃድ አይሰጠውም ወይም ይወሰድበታል ይታሰራል እስከ መገደልም ይደርሳል:: ከ1970-1971 በመጨረሻዎች በርካታ ተማሪዎችና ምሁራን በቀይ ሽብር ምክንያት ከከተማዎች እየሸሹ ወደ ትግሉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ነበሩ የተቀላቀሉት:: እነዚህ አዲስ ሰልጣኞች በስልነጣ ጣቢያቸውና በተመደቡበት ቦታ ሆነው ለሚያነሱት ጥያቄዎች ሳይቀር እንደተሳሳተ የፖለቲካ ዝንባሌ



እየተቆጠረ የሞት ዕዋን እንዲጎነጩ ተገደዱ:: በሺዎች የሚቆጠሩ ምሁራን ተገደሉ" ሲሉ ጽፈዋል:: አንባቢያን የትግራይ ሕዝብ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ያለ ሕዝብ መሆኑን ልንረዳ ይገባል:: ለዚህም ነው ወያኔንና የትግራይን ሕዝ ለይተን ማየት ያለብን:: የትግራይ ሕዝብ በተለይ ትግራይ ውስጥ ያለው የሌሎች የኢትዮጵያውያንን መጎዳት ላያውቅ ይችላል:: በነገራችን ላይ የተማረውንና በውጭ ያለውን የትግራይ ተወላጆች ከብዙኀኑ ጋር አብረን ማየት የለብንም::

በውጭ አገር ሁነው ወያኔን የሚቃወሙ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ የትግራይ ልጆች መኖራቸው አይዘነጋም:: እነዚህ ግን ወያኔን የሚነቅፉት እነሱ ባሉት የማይሄድላቸው በመሆኑ እንጂ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በድሏል ብለው ጠንከር ያለ ትግል አልሞከሩም:: እነሱ ራሳቸው ከትግራይ የተወለደ በቤተ ክህነቱ ሆነ በቤተ መንግሥቱ ኢትዮጵያን ማስተዳደር አለበት ብለው ያምናሉ:: የተማሩት የትግራይ ልጆች ስልጣን ከትግራይ እጅ እንዲወጣ አይፈልጉም:: ወያኔን ይጠላሉ የሚጠሉበት ግን በእነሱ አስተሳሰብ ስለሄደላቸው እንጂ በሌላ አይደለም:: በስደት ዓለም ያሉት በትግራይ ስም ተደራጅተው ነበር:: አሁን በቅርቡ አንድ የሰማሁት ዜና አለ:: ያም በጎሳቸው ስም ብቻ ተደራጅተው የነበሩ ከብዙ ውትወታ በኋላ ከ4 ሰዎች በስተረቅ ሌሎች በኢትዮጵያ ስም ለመደራጀትና ሰፋ ያለ አመለካከት መያዛቸውን ነው:: ግፋበት በርቱ ያሰኛል:: ነገር ግን አማራው በጎሳ መደራጀት ከኤድስ ለይቶ አያየውም:: ታላቁ ሊቀ ጠበብት አስራት ወልደየስ የአማራ ድርጅት ሲመሰርቱ አማራው እየተገደለ በመሆኑ ያንን ለመታደግ ብለው ሲነሱ ተቃዋሚ የነበረው አማራው ነበር:: አማራው ለብቻ መደራጀትን አንፈልግም:: አማራው በሌሎች ጎሳዎች ቀደም ተጠቃሚ ነበር ተብሉ ሲለፈለፍ ነበር ግን አልተጠቀመም::

ለምሳሌ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ገዥው አማራ ተደርጎ ይወሰድ ነበር:: በተለይ የሸዋ አማራ ነገር ግን የሸዋ አማራ ደብረ ብርሃን ለገቢያ የሚመጣው የበግ ለምድ እንደለበሰ ነበር:: በእርግጥ ከ20 የማይበልጡ በቤተ መንግሥቱ ይንደላቀቁ የነበሩ መሆናቸው ባይካድም:: ከሌሎች ጎሳዎች ጭምር የሥልጣንና የጥቅም ተጋሪ ሲሆኑ ሌላው አማራ ግን ከዋለልኝ መኮንን ጽሑፍ ጀምሮ በመወገዝ ላይ ያለ ሕዝብ ነው:: የእኔን የዘር ሀረግ ለመዘርዘር ጊዜው ባለመሆኑ ባልፈውም የተወለድኩበት ጎንደር ደብረታቦር ፋርጣ ግራሪያ ወርቄን ጽዮን ሲሆን አባቴም በባዶ እግራቸው ይሔዱ እንደነበር አስታውሳለሁ:: እንኳን ሽፍን ጫማ ነጠላ ጫማ ለእግራቸው አልነበራቸውም:: እኔ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ መቀየራቸውን አውቃለሁ:: ስለዚህ አብዮተኞች ሆኑ ዘረኞች ይህን አማራ እንደበላ አድርገው ሲከሱት መኖራቸው አይዘነጋም:: ይህን ከወላጅ አባቴ ጀምሮ እስከ ክፍለ ሀገር አልፎም በሌሎች አካባቢ የአማራው ሕዝብ በእኔ አባት አይነት የነበረ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል:: ይህን በአማራው ሕዝብ ላይ በሀሰት ይከሰስ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም የትግራይም ሕዝብ በዚህ ዓይነት መከሰሱ እርግጠኛ ነኝ:: በእርግጥ ወያኔ ከሌላው ክፍለ ሀገር የኢትዮጵያን ንብረት ጭኖ ትግራይ ማስገባቱ

አይከድም::ይህ ማለት የትግራይ ሕዝብ ፈቅዶ የተቀበለው ንብረት ነው ማለት አይደለም:: በውጭ አገር ያለው ምሁራን ለብቻው በመደራጀቱ የትግራይ ሕዝብ ሊወቀስ አይገባም:: ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን ሲሰጥ መሆኑን የትግራይ ሕዝብ ያውቃል ማለት አይደለም:: በእርግጥ የተማረውና በውጭ አገር ያለው ጥሩ አድርጎ ያውቃል:: ሊወቀስ አይገባም::

ወያኔ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይቀራረብ ስለፈለገ ድርጅታቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተጠላ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ እንዳይነሳባቸው ስለፈለጉ "ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ፥የትግራይን ሕዝብና ወያኔን መለየት አይቻልም" እያሉ ያሳዝናሉ:: በመሰረቱ ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም፡ ይህን ቅድሚያ ማወቅ ይጠይቃል:: ይህ ቡድን በጥቅም የሚገዙ ግለሰቦችን ይዟል:: ከሸዋ ወንድ መሰን ከበደ፥ከወሎና ከጎንደር አቶ ታምራት ላይኔንና ሌሎችን ብዙ የጥቅም ሰዎችን እንደገዛ ሁሉ ትግራይ ውስጥ ለጥቅም ሲሉ የተገዙ ሊኖሩ ይችላሉ:: ያ ማለት ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ይወክላሉ ማለት አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመኑ ያስመዘገበው ተቻችሎ የመኖር ታሪክ አስተዋይነቱ መጋባቱና መዋደዱ በዘርና በሃይማኖት በመደባለቁ ይህ አንቱ የሚያሰኘውን ተግባር እንሆ ወያኔ ሊያጠፋው እየተሯሯጠ ነው:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተለያዩ ፈተናዎች ደርሰዋል ነገር ግን በሕዝቡ በኩል ምንም አይነት ጉምጉምታ ታይቶ አይታወቅም:: ይህን አኩሪ ታሪኩን ነው ወያኔ በጥቂት እውቅ ባይ የሥልጣን ጥመኞች የሥነ መንግሥት ፖለቲካቸው መሳሪያ ለማድረግ ሌት ተቀን የሚለፉት ሕዝቡ የማይለያይ ሁኖ ሲያስቸግራቸው መታወቂያውን ቀየሩት:: አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ከአንድ መስሪያ ቤት ሲገባ ተሉ ተቀሳጥፎለት ይሄዳል:: የዋህ የሆኑት በዚህ ብቻ ተታለው ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለዩ የሉም ማለት አይደለም::

እንባቢያን እኔ ለወደፊቱ የሚያስፈራኝ በአቶ መለስ ዜናዊይና በአንዳንድ አፍቃሪ የሻዕቢያ ደጋፊዎች የሚጠነጠነውን ከፋፋይነት ሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዳያስተጋቡት ነው:: ምክንያቱም ወደድነም ጠላን ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት መፍለጥና መቁረጥ የሚችሉት የወያኔ አባላት ናቸው:: በዚህ ምክንያት በየክፍለ ሀገሩ ንብረት እየተዘረፈ ትግራይ ገብቷል:: በተለይም በጎንደርና ከወሎ ጋር ከፍተኛ የሆነ ችግር ይፈጠራል:: አቅም አለን ብለው ከሁለቱ ክፍለ ሀገራት መሬት ቆርሰው ወደ ትግራይ ወስደዋል:: ወያኔን የሚደግፉ የትግራይ ልጆች አልገባቸው ብሎ እንጂ ከጎንደርና ከወሎ ሕዝብ ጋር ሊያጣላቸው ስለፈለገ መሬት ቆርሶ ሲሰጣቸው በደስታ የተቀበሉ የሉም ማለት አይደለም:: ይህን አድርጎ ደጋፊዎቹ ካደረጋቸው በኋላ ደግሞ ሁመራን ለሱዳን አሳልፎ ሊሰጥ ሲስማማ የወያኔ ደጋፊዎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ትዝብት ጣላቸው::

በ1990 ዓም ሻዕቢያ የትግራይ ልጆችን በግፍ በደበደበ ግዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ቆሞአል:: በእርግጥ አንዳንድ እነሱን የመሰሉና ሲጀመር ጀምሮ ሥልጣን የናፈቃቸው ቡድኖች ከሌላው ጎሳ የተወለዱ የሻዕቢያ አሽከር የሆኑ



ነበሩ:: በገንዘብ የምገዛ ብሆን ኑሮ እኔ ቅድሚያ እሆን ነበር:: በዚያን ወቅት በተለይ ባድሜን ከሻዕቢያ ለማስለቀቅ በሚደረገው ግብግብ ወራት አንዳንድ ምሁራንና ዛሬ ድረስ ሰላም የማይሉኝ ወዳጆቼ ከሻዕቢያ ጋር መሞዳሞዳቸውን አጥብቄ በመቃወሜ እኮራበታለሁ:: በዚህ ወቅት ወያኔ ያጠፋ ቢያጠፋ በራሳችን ይቅር ብለን አብረን ቆመናል:: ከዚህ ወዲህ ብዙ ችግሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ደርሷል:: በተለይም በ1997 ዓም ምርጫ ወያኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲጋጭ የወያኔ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ዘር ቆጥረው ማለት ይቻላል ከወያኔ ጋር አብረው ቆሙ:: በምርጫ 97 ወቅት ውጭ አገር የነበሩ የወያኔ ደጋፊዎች ባንድ ሰብሰብ አሉ:: የተጣሉ ታረቁ ሌሎችን ለመዋጋት አንድነት ፈጠሩ:: እነሱ እንደዚህ ቢሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አስተዋይ ሕዝብ መሆኑን አስመዝግቧል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይና አመዛዛኝ ነው:: አቶ ስየ አብርሃ፥አሜሪካ ሲመጡ እክብሮ የተቀበላቸው ከነበረው ስህተታቸው በመመለሳቸው መሆኑን ጠንቅቆ አምኗል:: ይህን ያህል ሲሆን በተለይ በውጭ አገር ያላችሁ የወያኔ አባላት እንዴት ማስተዋል አቃታችሁ:: ወያኔ ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን ጥፋት ከላይ የዘረዘርኩት አንዳንድ የወያኔ አባላት እንደማትቀበሉት አምናለሁ:: ረጋ ብላችሁ ስታስቡት ግን እናንተን አቶ መለስና ሌሎች አንዳንድ አፍቃሪ ኤርትራ ግለሰቦች ከኢትዮጵያውያን ጋር ለይተው ካስጠሉአችሁ በኋላ እነሱ ግማሽ ትግራይን ለሻዕቢያ አስረክበው ርዕሠ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ እንዳደረጉት አውሮፕላናቸውን አስነስተው አስመራ ቢገቡ ምን ታደርጋላችሁ? ለዚህ ቅድሚያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አንድ ሁናችሁ ካልሰራችሁ ከሌሎች ክፍለ ሀገራት ይልቅ ጉዳት የሚደርስባችሁ በናንተ ላይ መሆኑን ማሰብ የተሳናችሁ ለምን ይሆን? ዛሬ ዓለም አንድ እየሆነች በመብራት በኤሌክትሪክ መገናኛ በድረ ገጽ ተወጥራ ባለችበት ሰዓት ኢትዮጵያውያን በጎሳ ወጥመድ ተይዘን እንገኛለን:: እኔ ጠበንጃን የጠላሁት ቀደም ብዬ ነው:: ጦርነት ከባድ ነው! ብዙ ሕጻናት በጦርነት አልቀዋል:: ብዙ ንብረት በእሳት ሲጋይ አይቻለሁ:: ዛሬ የወያኔ ባንዶች ሽፍታ እያሉ የሚገድሏቸው የአርማጭሆ ሕዝብ በጦርነት ሲያልቅ አይቻለሁ:: ያን ሕዝብ ያስጨረሰ ኢዲዩ ደብዛው ጠፍቷል:: ያ ትውልድ ያፋጀው ኢሕአፓ ሲከፋፈል ኑሮ ዛሬ በግለሰብ ስም መጠራት ከጀመረ ውሎ አድሯል:: ይህን የጠበንጃ አብዮት ከአንድ ቦታ ላይ መቆም ይኖርበታል የሚለውን አቅዋሜን የሚጠሉ ወገኖቼን አልፈርድባቸውም::

የወያኔ ኢሕአዴግ ወታደሮች በአደባባይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይፈጃታል:: የአገሪቱ ሀብት በአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ይፈሳል:: በአገሪቱ የበላይነት ወሳኝነት ያላቸው የአንድ ክፍለ ሀገር ሰዎች ናቸው:: አገሪቱን የባህር በር አሳጥቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር መንዝሮ አንድ እንዳይሆን አድርጎታል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ አይደለም የዓለምን ሕዝብ አጭበርብሮ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም ምርጫ በጠበንጃ ወስዷል:: መሪዎቹን አስሮ አሰቃይቷል:: ይህ አልበቃ ብሎ 1600 ጋሻ ወይም ኪሎ መሬት ለጎረቤት አገር ሊሰጥ ደፋ ቀና እያለ ነው:: በዚህ መካከል የአካባቢው ተወላጆች ከንብረታቸው ከቤታቸው

ሲፈናቀሉ መርዳት ሲገባው የተፈናቀለ የለም ብሎ በአደባባይ ያሳዝናል:: ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠበንጃውን ያስወረደው ቢሆንም አንዳንዶች እየደበቁ ባስቀመጡት ጠበንጃ መሬታቸውን የሚያርሰውን ሱዳንን በመውጋታቸው ለምን ወጋችሁ ብሎ ደበደባቸው:: በዚህና በሌላውም ምክንያት ሕዝቡ ትግስቱ አልቆ ወያኔ የመጣው በጠበንጃ ስለሆነ የሚወርድ በጠበንጃ ነው የሚሉትን ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ከዚህ ውሳኔ በመግባታቸው ምክንያት ባልፈርድባቸውም ግን መታየት ያለበት ጠበንጃ ምንግዜም ሰላም የማያመጣ መሆኑን ነው:: ጠበንጃ የሚያመጣው ነገር ቢኖር የጠገበን ነብር አባሮ የተራበን ነብር ማስገባት ነው ይህ ደግሞ ውጤቱ ሁሌም ጠበንጃ ነው:: ስለዚህ የሰላም ትግል አማራጭ የሌላው ጉዳይ ነው:: የደቡብ አፍሪካ የሰላም ታጋይ ርዕሠ ብሔር ማንዴላ ለ27 ዓመት ሲታሰሩ በሜታቸው ከሰላም ትግል ፍንክች አላሉም::

ባድመ እንደምክንያት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 363 የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታሪኩም ቢሆን በማንም አገር ሉአላዊነት ላይ ጣልቃ የመግባት ፍላጎት የለውም:: የጥቅም ግጭት አለን ከሚሉ አገሮች አንኳ ቢሆን አብሮ መስራት አብሮ በመኖርና አብሮ በማደግ የሚያምን ማሕበረሰብ እንጂ በጠላትነት የማየት ልምድ የለውም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና እምነት በመጣስ በአገሩ ሉአላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ላይ ጥቃት በሚሰነዝሩ ኃይሎች ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምቹ አይደለም:: ኢትዮጵያውያኖች ከታሪካቸው ነፃ ሕዝቦች ኅበዝ ሕዝቦች ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ እርስ በርሱ ቢዋጉም ጠላት ሲመጣ ግን የውስጥ ቅራኔያቸውን ወደጎን በመተው ወራሪውን ኃይል በአንድነት የሚመክቱ በነፃነት የኖሩ ሉአላዊነታቸውን ፍፁም የማያስደፍሩ በዚህ ጀግንነትም ከአፍሪካ አህጉር ተለይተው የሚታወቁ ሕዝቦች ናቸው:: ይህ ነባር ታሪክ የኢትዮጵያውያን መለያ ታሪክ መሆኑ እየታወቀ በሜካ አስተሳሰቡ ተዘፍቆ የኖረና ያለ የኤርትራ መንግሥት ኃይል በማከማቸቱ ጉልበት የፈጠረ መስሎት በኢትዮጵያውያን ላይ በከፈተው ጦርነት በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ አሳፋሪ በሆነ መንገድ ሽንፈቱን በዓለም ሕብረተሰብ ፊት ገሃድ ሁነዋል:: ከሻዕቢያ መንግሥት ወረራ ከበስተጀርባ ሁነው ሲያጫፍሩና ሲያዳምቁ የነበሩ ኃይሎች ድጋፍም ታክሉበት ይደረግ ስለነበረ ሽንፈቱም የሻዕቢያ መንግስት ብቻ መሆኑ ቀርቶ የአጫፋሪዎቹና የፈንጅ አቅራቢዎቹ ሽንፈት እንደሆነም በግልጽ ገሀድ ሁኗል:: የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ምስጢር ለጠላት ሁሉ ጊዜ ምቹ ሁነው አለመገኘት ነው:: እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ጥቃት ሲነሳ ደሙ ይፈላል፤ ፀጉሩ ይቆማል፤አብሮ ይዘምታል አብሮ ይዋጋል አብሮ ድል ይቀናጃል የአገሩን ሉአላዊነት ያስከብራል" ሲሉ ጽፈዋል::

መድኃኔ ታደሰ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 156 "የሚገርመው የኢትዮጵያ መንግሥት ህግሐኤንና ኤርትራውያንን ለማስደሰት ያደረገው ጥረትም ከኢትዮጵያውያን ይልቅ ያልተረዱት ኤርትራውያን ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል:: ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ንብረት ዘርፎ ለመውሰድ ሲነሳ መውሰድ የለብህም በማለት የታገለው በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ ቡድን ሳይሆን ከታች ያለው የትግራይ ሕዝብ ነው:: ለምሳሌ በ1986



ዓም እስከ ሚያዝያ 1990 ዓም ትግራይ ውስጥ 3 ኃይል ነበረ:: የመጀመሪያው ከሕዝቡ የመጣ ሮሮህ ነው:: ያም የትግራይ ሕዝብ ዓላማ "ቅድሚያ ኢትዮጵያ ቀጥሎ ትግግራይነት" የሚለው ኃይል የሻዕቢያ ተሳቢ ተሽከርካሪዎች ከኢትዮጵያ ጭነው የሚወስዱትን ቁሳቁስ ማቃጠልና ከኤርትራ የሚገባውን እቃ አለማግዛት አመጽ ጀመረ:: ይህ ኃይል ጥላቻው እየበረታ ሲሄድ ሁለተኛው ኃይል የዚህን ሕዝብ ስሜት ሊጋራ ታጥቆ ተነሳ:: ያም ሁለተኛው ኃይል ዓላማ "ቅድሚያ ትግሬነት ከዚያም ኢትዮጵያዊነት" የሚለው ኃይል ኋላ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊን አስጨንቆ በኤርትራ ላይ የምጣኔ ሀብት የኢኮኖሚ እገዳው እንዲበረታ ያደረገው ውሉ አድሮ አንጃ ተብሎ የተባረረው ኃይል ነው:: ሶስተኛው ኃይል ደግሞ በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው "ቅድሚያ ኤርትራ ቀጥሎ ትግራይ ከዚያም ኢትዮጵያዊነት" የሚለው ኃይል አቅም በላነሰው ሊንበረከክ ቻለ::

ነገር ግን ይህ ሶስተኛው ኃይል ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ሁለተኛውን ኃይል አባሮ ብቻውን ቀጭ ብሏል:: ዛሬ ይህ የመጀመሪያው ኃይል ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይገናኝ ይህ ሶስተኛው ኃይል "ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ፣የትግራይን ሕዝብና ወያኔን መለየት አይቻልም ሁለቱም አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው" በማለት ማላዘን ጀምሯል:: ስለዚህ ዛሬ አንዳንድ የዋሕ ሰዎች ትግርኛ ተናጋሪውን ወያኔ አስመስሉ የሚያይ አሉ:: ይህ መጥፎ መሆኑን መገንዘብ ያሻል:: ለወያኔ ቅስቀሳ እየተዘጋጀንለት መሆኑን መረዳት አለብን:: ባለፈው በ1997 ዓም የቅንጅት ምርጫ ወቅት የትግራይ ልጆች ከሌላው ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነው የታገሉ መሆናቸው አይዘነጋም:: ሊቅ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን አልፈን ሌሎች ብዙ የትግራይ ልጆች ታግለዋል:: አቶ ክፍሉ ታደሰ ግንቦት ሰባት በተባለው መጽሐፋቸው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የነገሩአቸውን ጽፈዋል:: ያም ወያኔ ሕዝቡን አስሮ ካሳደረ በኋላ ከ60 እስከ 70 የሚሆኑ የትግራይ ልጆችን መፍታቱን ነግረዋቸው ጽፈዋል:: እንዲሁም ተዋናይ (አርቲስት) ደበበ እሸቱ የትግራይ ልጆች ያደረጉትን ዘርዘር አድርገው ጽፈዋል::

ደበበ እሸቱ የእምነቴ ፈተና በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 135 "የትግራይ ተወላጆች የኛ ደጋፊዎች ናቸው:: ሰዓት ሳይወስኑ መሸ ረፈደ ሳይሉ ልክ እንደራሳቸው ሥራ በማየት ነበር የሚደከሙት:: በሕዝባዊ ስብሰባዎች በአዲስ አበባ፣ በክልሎችም በመስቀል አደባባይም አብረውን ሳይለዩን፣ፕሮግራሙ እስኪያበቃ ድረስ ከያንዳንዳችን ባልተናነሰ መንገድ አስተዋጽኦ በማድረግ ደግፈውናል፤ረድተውናል:: ምንጊዜም ምስጋና ይገባቸዋል:: ኢሕአዴግ ቅንጅትን ዘረኛ ብሎ ሲለጥፍብን አንጀታቸው እያረረ ለምን የማያውቁትን ይዘላብዳሉ? ሌላው ቢቀር እኛን ምን ሊሉን ነው? በማለት ፕሮግራማችን ጥራቱንና ብቃቱን የጠበቀ እንዲሆን የሚለፉ ኢትዮጵያውያን ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል::

አውደ ኢትዮጵያ ልዩ እትም 1 2000 ዓም ለምሳሌ 1997 ምርጫ ምክንያት የጠፋው 193 ሕይወትና 763 የቆሰሉ ዜጎች ፍርድ ይጠብቃል የተባለው

መጣጥፍ ገጽ 3 "እንዳልካቸው ወ/ገብርኤል እድሜ 26 ክልል ትግራይ የሞተበት ጥይት" ሲል ጽፎአል። እንግዲህ ሆደ ሰፊ መሆን ማለት በሃይማኖትና በጎሳ መለያየት መጥላት ይገባል። እንባቢያን ይህን እያልኩ የምጽፈው ወድጄ አይደለም እየፈራሁ ነው። ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም የኢትዮጵያን ሕዝብ የበደለ በመሆኑና ኢትዮጵያን ያፈራረሰ በመሆኑ የሚበሳጭ እንዳለ ስለተረዳሁ ነው። ስለዚህ በትግራይ ሕዝብና በሌላው ሕዝብ መካከል ልዩነት የለም። ሥልጣን የናፈቃቸው የሚያመጡት ችግር እንጂ በሕዝቡ መካከል ልዩነት ኑሮ አያውቅም። ሕዝቡ ተባብሮ ተረዳድቶ የኖረ ለወደፊቱም በዚህ ዓይነት ትብብር እንዲኖር ሁላችን ሆደ ሰፊ መሆን ይኖርብናል።

## ምዕራፍ 3

## የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ!

ዳኛው ወል ደሥላሴ <u>ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 98 "ወገኑን አይወድም እየተባለ የሚወራለትና ስሙ የሚጠፋው የጎንደር ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ጀኔራል ነጋ ተገኝ የሚባሉ የራሱን ልጅ በአስተዳዳሪነት ሲያገኝ" ሲሉ የጎንደር ሕዝብ ተወላጁ ተሹመው ሲመጡለት የተደሰተ መሆኑን ገልጸዋል። ለአንድ አካባቢ ደህናው ነገር አስተዳዳሪው የአካባቢው ተወላጅ ቢሆን ይመረጣል። ተወላጆች በየክፍለ ሀገራቸው ቢያስተዳድሩ ችግሩ ይወገዳል! ኢትዮጲያ የብዝ ጎሳዎች ጎተራ ስትሆን የያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የየራሱ ተወካይ በሀላፊነት መቀመጥ ይኖርበታል። ይህን ብሎ መጠየቅ ሌሎች ዘረኝነት ሳይሆን አገርን ለማሳደግ ያመቻል። ወሎየው የአስተዳደር ችሎታ ቢኖረውና ወለጋ ሀዶ በአስተዳደር ጎንደሬው ሐረር ቢሄድ! ትግሬው ሲዳሞ ሕዶ ቢሾምና ጎጃሜው አፋር ቢሾም፤አርሲው ትግሬ ቢሾምና ኡሊባቡሩ ጎንደር ቢሾም ወለጌው ትግሬ ቢሾም ጋሞጎፋው ወሎ፤ ቢሄድ የተቀላጠፈ ሥራ ለመስራት አይችልም። ምክንያቱም ተሹሞ የሄደበትን ክፍለ ሀገር የሰውን ጸባይና ባህል ሌላውን ሁኔታ እስኪለምድ ድረስ ስራው ይጓተታል።

ይህ አሰራር በደርግ ዘመን መንግሥት በአንዳንድ ክፍለ ሀገራት ተጀምሮ ደህና መሄድ መራመዱ አይዘነጋም። ሞያ ያለው ግለሰብ ቢሆንም ለአካባቢው ባይተዋር ከሆነ ጥሩ አይመጣም። ስለዚህ የአባቶችም አባባል "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" የሚባለው ያለ ምክንያት አይደለም። በእርግጥ ማዕከላዊ መንግሥት ቅድሚያ ተጠሪ አድርጎ የሚሾማቸው የክፍለ ሀገሩን ልጆች መሆኑ እንዳለ ሁኖ ሌሎች ባለሙያዎች ደግሞ ሌላውን ስራ ለመስራት ይችላሉ። በአንድ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪው ተጠሪው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ ከሆነ በኋላ ሌሎችን ማዕከማዊ መንግሥት የሚመድባቸው ሰራተኞች ቢላኩ ከሞያ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ችግር አይፈጠርም። ይህን ባህል ለማዳበር ደግሞ ቅድሚያ የተስተካከለ የማይዛባ ማዕከላዊ መንግሥቱን ሕገ መንግሥት መኖሩ ይገባል።



በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በስልጣን የነበሩት ሰብሰቦች መሆናቸው አይዘነጋም። በ14 ክፍለ ሀገር በብዛት የአንድ ክፍለ ሀገር ተወላጆች ነበሩ። ይህ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን አስከፍቷል። ሌላውን እንተዎው ለ60 ዓመታት ኤርትራ በቅኝ ግዛት የተዳደረች መሆንዋ አይካድም። ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ክቡር አክሊሉ ሀብተወልድ ልፋትና ኤርትራውያን አገር ፍቅር ብለው ታግለው በተባበሩት መንግሥታት የተሰጣቸውን የራስ ገዝ አስተዳደር አፍርሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲቀላቀሉ በጠቅላላ አስተዳደሩ በነሱ ተወላጆች ተይዞ ቢሆን ኑሮ ችግሩ አይበዛም ነበር። አጤው ግን ያደረጉት አስተዳደሩን በእርሳቸው ሰዎች አስይዘው ትምህርት ቤትና ኩባንያ ኤርትራ ውስጥ ከፈቱ የኢትዮጵያን ንብረት አፈሰሱ። ለ3 ዓመታት የመላው ኢትዮጵያ የዓመት መጠን (ባጀት) ኤርትራ ከወጣው ጋር እኩል ሆኑ ነበር። ኤርትራውያን ያዩት አስተዳዳሪ ሁኖ የመጣውን ግለሰብ እንጂ በነዚህ ግለሰቦች አማካይነት የተከፈቱትን ተቋማት ሊያዩ አላሹም። እስኪ በ1960 እስከ 1966 መግቢያ ላይ የነበሩትን የየጠቅላይ ግዛቱን ገዥዎች ስም እንመልከት።

1ኛ ኤርትራ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ፤
2ኛ ትግራይ ራስ መንገሻ ሥዩም፤
3ኛ ወሎ ደጃዝማች ማሞ ስዩም፤
4ኛ ጎንደር ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ፤
5ኛ ጎጃም ደጃዝማች ደረጀ መኮንን፤
6ኛ ሸዋ ራስ መስፍን ስለሺ፤
7ኛ ሐረር ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል፤
8ኛ ባሌ ሜ/ጀኔራል ጀጋማ ኬሎ፤
9ኛ ወለጋ ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም፤
10ኛ ጋሞ ጎፋ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ፤
11ኛ ሲዳሞ ሌ/ጀኔራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ፤
12ኛ ከፋ ደጃዝማች ፀሐይ ዕንቁ ስላሴ፤
13ኛ ኢሉባቦር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ስላሴ፤
14ኛ አርሲ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ፤ ናቸው።

ለምሳሌ ድንበርን ለመከለል በተደረገው ድርድር ወቅት ሊደናበሩ የሄዱት ግለሰቦች ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ካደረጉት ግንኙነት ይልቅ ለንደን ቅኝ ገዥዎች ሥለው ካስቀመጡት ሰነድ ፍለጋ ነው። የአካባቢው ተወላጆችን ማነጋገር ሐፍረት መሰላቸው። ለዚህም በሔሊኮፍተር ከደንበሩ ደርሰው ይመለሱ ነበር እንጂ "ከዜት እስከዜት ድረስ ነው እናንተ እና አባቶቻችሁ ታርሱት የነበረው አስረዱን" ብሎ የጠየቃቸው የለም። እነዚህ በአጤው እየተመለመሉ በተለያዩ ከፍተኛ መስሪያ ቤት የተሰገሰጉት ትንሽ ግለሰቦች የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቀው ሠነድ ሊያዘጋጁ አልፈለጉም። ለምሳሌ በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮን በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ካነጋገራቸው መርጌታ ሲናገሩ "ወያኔ ድንበርን ለመከለል ፈልጎ ሳለ እነሱን ሰብስቦ ገንዘብ እየሰጠ

መሬቱን የሱዳን ነው ብላችሁ ፈርሙ"ብሎ ሲጠይቃቸው አንፈርምም ብለው ተመልሰዋል። እነዚህ ሰዎች እንቢ ሲሉት ሌሎችን ባንዶች ገንዘብ አምላኬን ሰብስቦ ወስዶ እንደነበር መርጌታ ተናግረዋል። ለዚህም ነው እነዚህ በመጀመሪያ ሕደው የነበሩት ደንበራችን እናውቀዋለን ያሉት። ኢትዮጵያ ዛሬም 14 ክፍለ ሀገር ያላት አገር ናት። ወያኔ ክልል ብሎ በ9 ቢሸነሽነው 14 ክፍለ ሀገር ናት። በደንበር ላላችሁ ክፍለ ሀገራት ተወላጆች የማሳስበው ጉዳይ ቢኖር ሕብረት ይኑር ነው። ለወደፊቱ ለኢትዮጵያ አንድነት መሰረቱን ሊያናጉ የሚችሉ የተወሰኑ ክፍለ ሀገራት አሉ። በተለይም ከታሪክ ሠነድ ከምንረዳውና እኛም ደርሰን ካየነው እውነታ ለወደፊቱ ሐረር÷አሰብ÷ትግራይ÷ ጎንደርና ጎጃም ሌሎችም ክፍለ ሀገራት አረንጓዴ ሳይሆኑ ደም የሚፈስባቸው ናቸው። ከዚህ በፊት ደም ፈስባቸዋል ለወደፊቱም ደም ይፈስባቸዋል። ባለቤት አሪ የሚለው ደግሞ ከምክትል ገዥ ጀምሮ ተወላጅ ማስተዳደር ሲችል መሆኑን ጠንቅቀን መረዳት ይኖርብናል።

1ኛ ሐረርጌ አስቸጋሪውና ከሁለት አገር ጋር የሚያገናኘው የወሰን ችግር ያለበት ሲሆን በ1969 ዓም ሐረር አቅራቢያ ድረስ ሱማሌ ገብታ ልታጠፋው የነበረ መሆኑ አይዘነጋም። ይህንም ጥፋት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል አንድ ሁኖ ያስቀረው መሆኑ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው። ሐረርጌ ከቀደም ጀምሮ ቅኝ ገዥዎች ያሰፈሰፉበት አጤ ግራኝ አህመድን ቱርኮች ረድተው በመምጣት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት ሲሆን ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ያላሰለሰ ጥረት ወደ ማዕከላዊው መንግሥት ቢገባም ጠላቶች በሃይማኖት እያመካኙ ከፍተኛ የደም ጎርፍ እንዲፈስ ሁኖበታል። የአጥፍቶ መጥፋት ኃይሎችስ ዛሬ በዚህ አካባቢ አቅድና ዓላማ ሳይኖራቸው ይቀር ይሆን?

<u>መስዓዕትነት እና ፅናት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 98" በዚህን ጊዜ ነበር በጠቅላላ በኡጋዴን ግዛታችን የኢትዮጵያ ሠራዊት የሞት ሽረት ውጊያ የፈጸመው በወልወል፣በገላዲን፣በቀብሪደሃር፣በሙስታሂል፣በአይሻ፣ በቀላፎ የነበረው የ3ኛ ክፍለ ጦር ብርጌዶችና ሻለቆች የሶማሊያ ታንክና መድፍ በመጋፈጥ ከነቤተሰቦቻቸው በዚያ እጅግ ሰፊ በሆነ በርሃ ላይ ውድ ሕይወታቸውን ለአገራቸው አንድነትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ሲሉ ሰጥተው ያለፉት። የተረፉት የጦር ባልደረቦች በጅጅጋ ካራማራ ተራራ ላይ መሽጉ በሚካናይዝድ ታንኮች፣ብረት ለበሶችና ከባድ መድፎች በአየር መቃወሚያ መሳሪያዎች እየተረዳ የሚገሰግሰውን የሲማሊያ ጦር የወገን ጦር በፍፁም መቋቋም አቃተው። የሶማሊያ ወራሪ ጦር በወገን ሰላማዊ ሕዝቦች ላይ ከባድ ጉዳት አደረሰ። በገጠሩ ደጋ ሰፍራዎች በጋራ ሙለታና በኤጀርሳ ጎሮ ቀደም ብለው በሚስጥር ለሽፍትነት ተግባር ሰርገው የገቡት ቤተ በማቃጠል የልማት ድርጅቶች ላይ አደጋ በመጣል ከፍተኛ የማጥቃት ድርጊታቸውን ጀመሩ። በጅጅጋ፣ካራማራ ተራራ ላይ ይከላከል የነበረው የወገን ጦር ከሶማሊያ ጦር የሚወርድበትን ያፈሰሱበት አጥንታቸውን የከሰከሱበት የአባቶቻችንና የአያቶታችን መሬት እየተደፈረ መጣ። የወገን ጦር ወደኋላ በማፈግፈግ ባቢሌ አካባቢ ዳከታ በተባለ ከፍተኛ መሬት ላይ እንደገና የመከላከያ ምስጉን



አዘጋጀ" ይሉና ገጽ 102 " በጥር ወር 1970 ዓም የኢትዮጵያ ሚልሺያ ሠራዊትና መደበኛ ነባሩ ጦር ክፍሉች የተቀዳጀ የመልሶ ማጥቃት ዝግጅት በማድረግ በኤጀርሳ ጎሮ እና በዳከታ አቅጣጫ በወገን አየር ኃይል እየተረዳ ጦርነቱን ጀመረ። በእውነቱ የሶማሊያ ጦር ተቋቁሞ ሊዋጋ ቀርቶ አግበስብሶ ያመጣውን ከባድ መድፎች፣ብረት ለበሶች፣ታንኮችና አየር መቃወሚያ መሳሪያዎች ይዞ በቅጡ ማፈግፈግ ስላልቻለ ሁለት ሶስተኛውን ያህል ወገን ማርኮ ተረከበው" ሲሉ ጽፈዋል። በዚህ ወቅት ሶማሌዎች በሃይማኖት ለማሳበብ ጥረት ቢያደርጉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሃይማኖት መሪዎቹ እስከ ተራው ሕዝብ ባንድ ቆሞ "በሀገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም "የሚል መጽሐፍ ጽፎ ለአገር አንድነት የተነሳ መሆኑ አይዘነጋም።

2ኛ አሰብ ራስ ገዝ አስተዳደር ከአፋር ጀምሬ ብዘረዝር የወደፊቱ አስከፊ ችግር ይገጥመናል የሚል ፍራቻ አለኝ። በመሰረቱ አሰብ አስተዳደር አፋር የኢትዮጵያ እንጅ የኤርትራ አይደለም። አሰብን የአፋር አስተዳደር ከጅቡቴ ጋር ያለው ደንበር የተሰመረበት ነው። ከኤርትራ ጋር ግን ገና ብዙ ጦርነት የሚያስነሳ ኢትዮጵያውያንን ደም የሚያፋስስ ቁርጠኛ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እስኪገባ ድረስ የሚጠብቅ ይመስለኛል። ይህ የእኔ ሕልም ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልም መሆኑን አልጠራጠርም። ዛሬስ ከኛም አልፎ የአደጉ አገሮች ሳይቀር ቀልብ የሚስብ እጃቸው የሚገባበት የአሰብ ጉዳይ መሆኑ አይቀርም። የአረቡ ዓለም የኤርትራን ሕዝብ ፈልጎ ሳይሆን ቀይ ባህርን ፈልጎ ንብረቱን ያፈሰሰ ሲሆን የዓረቡ ዓለም እንሆ ፊታቸውን ወደ ቀይ ባህር አዙረዋል። አሰብ ወደ ኢትዮጵያ ካልተከለለ ለወደፊቱ በኤርትራ ሰላም አይኖርም። አንዳንድ ግለሰቦች አሰብንና ኤርትራን ለይተን እናይም ሁለቱም አብረው ወደ ኢትዮጵያ ይቀላቀሉ ይላሉ። በመሰረቱ አሰብና ኤርትራ ልዩነት አላቸው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ሊጨመሩ አይገባም እኛ አንድ ሕዝብ ነን ስንል እነሱ አይደለነም ብለዋል። 30 ዓመታት ተዋግተዋል ወያኔ ፈቅዶላቸው ከኢትዮጵያ ሲነጠሉ የአሰብን አስተዳደር ጨምሮ ሰጣቸው። ስለዚህ ኤርትራውያን ኢትዮጵያዊ አይደለነም ብለው ወግተውን የሄዱትን የኛ ናችሁ ለምን እንላለል? ወገኖቻችሁ ነን የሚሉንን የአሰብ አስተዳደር ተወላጆች ጥያቄ ማክበርና መተባበር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

3ኛ ትግራይ ክፍለ ሀገር አሁንም ከኤርትራ ጋር ደንበሩ በትክክል አልተሰመረበትም። ይህ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አልቋል የተባለለት ውሳኔ ከተወሰነ ብዙ ዓመታት አስቆጥሯል። ነገር ግን እስከ ዛሬ አንድም ውጤት አልታየም። በዚህ በኩል ገና ብዙ ችግር የሚያመጣ መሆኑን ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የፈሰሰበት መሆኑ መረሳት የለበትም። በትግራይ መሬት ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ፈሷል። ባድሜም ሆነ ሌሎች ወረዳዎች የትግራይ ክፍለ ሀገር አስተዳደር ውስጥ ሁነው የቆዩ መሆናቸውን ከዚህ በፊት ጽፌአለሁ። አማረ አለሬ ብሻው መጋቢት 2 ቀን 1991 ዓም <u>ካለፈው ስህተታችን እንማር</u> በሚል መጣጥፍ ገጽ 9-10 "እነዚህ የተጠቀሱት ወረዳዎች በታሪክ ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ የትግራይ ክፍለ ሀገር እንደሆነ ታሪክ

የያዘው ሐቅ ነው። ይህ መሬት ቀደም ጀምሮ በትግራይ ክፍለ ሀገር ይተዳደር እንደነበር ብዙ የኢትዮጵያ አዛውንቶችና በተለይ የትግራይ ክፍለ ሀገር ተወላጆች የሚናገሩት ታሪክ ነው። ሻዕቢያ እነዚህን ወረዳዎች ለመውሰድ የቃጣው ጨርሶ ከታሪክ ውጭ የመስፋፋት ሙከራ ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር እነዚህ ወረዳዎች በባህረ ነጋሽ በኤርትራ ይተዳደር ነበር የሚል ታሪክ የለም። ሽራሮና ባድሜ ሻዕቢያ አቅም አለን ብሎ ለመውሰድ የከጀለው በመሳሪያ እንጂ በታሪክ አይደለም። ወያኔ በጠበንጃ ተመክቶ ከታሪክ የሌለውን ከጎንደርና ከወሎ ለም መሬቶችን ወደ ትግራይ እንደከለላቸው ሁሉ ኤርትራ ደግሞ በአቅሟ ከትግሬ ለም መሬቶችን ለመውሰድ የተነሳችው ታሪክ ኑሯት ሳይሆን በኃይል መመካት መሆኑን ለማንም ግልጽ ነው" ሲል ከተጻፈ በኋላ ለጹሑፉ ማጠናከሪያ ከታሪክ የወሰድኩበትን እገልጻለሁ።

1ኛ ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች ገጽ 733
2ኛ ጦቢያ ጋዜጣ ቁጥር 12 ሰኔ 25 ቀን 1990 ዓም ገጽ 7
3ኛ ሐዋርያ ጋዜጣ ሕዳር 1991 ዓም አቶ ተስፋዬ ሰቋር ቃለ ምልልስ
4ኛ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም በአሜሪካን ራዲዮ የአማርኛው ቃለ መጠየቅ ሲደረግላቸው የሰጡት መልስ "የግዛት ጥያቄ ማንሳት ያለባት ኢትዮጵያ እንጂ ኤርትራ ልትሆን እንደማትችል" ተናግረዋል። እርሳቸው ሲያነሱት የፈለጉት ከላይ አሞራ ከተባለው መጽሐፍ የተገለጸውን መሬት ሳይሆን አይቀርም። በትግራይ ውስጥ ባሉት ወረዳዎች ከታሪክ የትግራይ ክፍለ ሀገር እንጂ የኤርትራ አለመሆኑን ደግሜ ደጋግሜ ስጽፍ ቆይቻለሁ።

4ኛ የዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆነው ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ያለው 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ወደ ሱዳን ሲሰጥ የታቀደለት ነው። ሁኔታው በኢትዮጵያ አስተየዳዳሪዮች የግል ጥቅም ሲሆን ይችላል። በዘመነ መሳፍንት ወቅት በጎንደርና በጎጃም በኩል መሳፍንቶች ሕዝቡን በማስተባበር ከ42 ግዜ በላይ ጦርነት ገጥመው ከቁርከ ተከላክለው አቆይተዋል። በመሰረቱ አፍንጫ ሲነካ ዓይን ያለቅሳል እንደሚሉት ለጎንደር የመጣው ጥፋት ጎጃምን የማረበት ወቅት የለም። ከላይ እንደተባለው ሱዳን ይህን አካባቢ ሕዝብ ለማስለም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው። በጎንደርና በጎጃም በወሎ በኩል በድንበር ጉዳይ ቅርበት ስላለው በንግድ አመካኝቶ ሕዝቡን ማፋጀትና ሕብረት እንዳይኖረው ማድረግ ተግባራቸው ሲሆን ይህን ሴራ ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቃል። ታዲያ ወያኔ ሕዝቡ አንድ ሁኖ እንዳይነሳ ለማድረግ የማይነፈቅለው ድንጊያ የለም። ስለዚህ በወሎ በጎጃምና በጎንደር በኩል ችግር መኖሩ አይዘነጋም።

5ኛ ኢሉባቦርና ከፋ፣ጋሞጎፋ ሲዳሞ ባሌ፣ እነዚህ ክፍለ ሀገራት ከውጭ ድንበር አገር ጋር ይገናኛሉ። በዚህ በተያዘው የዘር ክፍፍል ምክንያት የውጭ ኃይሎች ለጥቅማቸው ሲሉ እየቀሰቀሱ ችግር ሊያመጡ ይልቹ ይሆናል። የዛሬው ትውልድ ሆነ መጭው ትውልድ ካለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት ወስደን ልንጠነቀቅ ይገባል። እነዚህ የውጭ ኃይሎች እስስቶች ስለሆኑ መምጫቸው አይታወቅም። አንዴ በሃይማኖት በሌላ ጊዜ ደግሞ በንግድ አልያም ደግሞ በጎሳ እየከፋፈሉ ዳር ደንበራችን እንዲደፈር ለማድረግ ይመኛሉ። ስለዚህ እኛ



ማድረግ ያለብን ጉዳይ ቢኖር በንግድ ሆነ በሃይማኖት አልያም ደግሞ በጎሳ አመካኝቶ ከወገኖቻችን ጋር ሊያጋጩን የመነሳው ለእኛስ አዝኖ ሳይሆን ለራሱ ከእኛ ጥቅም ስላለው ነው። ስለዚህ ሁላችን ነቅተን መጠበቅና አገራችን ማክበርና ማስከበር የያንዳንዱ ትውልድ ድርሻ ነው። ስለዚህ ልብ ያለው ሽብ ነው እንደተባለው ሽብ ልናደርግ ይገባል።

6ኛ ወሎና ሽዋ፤አሩሱ ከውጭ ጋር የሚያገናኝ ድንበር የላቸውም። በተለይ ወሎ በአጤው አስተዳደር ወቅት ቢሆን እንደ ቀደሙ የአሰብ የራስ ገዝ አስተዳደር ስለተጀመረና በደርግም ይህ የአሰብ ራስ ገዥ አስተዳደር ተጠናክሮ ስለነበር ማሀል ሆኖአል። ሽዋ አርሲ ከውጭ ማለትም ዓለም አቀፍ ድንበር ጋር አይገናኙም። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም አንዳንድ ግለሰቦች የማሀል አገር ተወላጆች ደንበርን አስመልክቶ ግድ የሌላቸው ናቸው። ይህ እምነታቸው ብዙ ዘር እየዘሩ የጠላት ተባባሪ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ደንበር ብሎ የሚሎኽውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ቅስም የሚሰብሩ ናቸው። በዚህ በደንበሩ ጉዳይ ብዙ ግለሰቦች መግለጫ ሰጥተዋል። ብዙ ድርጅቶች ተንገበግበዋል። አንዳንድ ግለሰቦች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን እነሱ የሚመሩትን ድርጅት ወይም ደግሞ ለሚሰማቸው ሰው የሚያሰሙት ወሬ ከጠላት ጋር የሚያስወግናቸው ነው።

አንባቢያን የአገር ጉዳይ የአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነው። አንድ ተረት አለ ያም "ሁለት ሰዎች ተኝተዋል ታዲያ ጅቡ የአንዱን እግር ሲበላው ሌላው ሰምቶ ምን ነው የሚያነፈንፈው ሲለው ዝም በል ጅቡ አንድ እግሬን እየበላው ነው" አለው ይባላል። ጅቡ አንድ እግሩን ጨርሶ ወደሌላው እግሩ እንደሚሄድ አልገባውም። የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚፈልጉት ልዩነት ነው። ተራ በተራ ካስጠቁ በኋላ ድል ያደርጋሉ። ይህን የኢትዮጵያን ጠላቶች ተንኮል ለምን አንዳንድ ግለሰቦች እንዳልተረዱት አልገባኝም። ተመልከቱ ዛሬ ደንበርን በተመለከተ ስታወሩ አድማጭ የላችሁም። ከፋፋዮች በግል ጥቅም በቂም የተያዙ እርቀው የማያስቡ ናቸው። ጠላቶቻችን የሚፈልጉት ይህን አይነት ሴራ ስለሆነ ከልብ ልታስቡበት ይገባል። በታሪክ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ ለቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ስለተሰጠ እንጂ "አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው" የሚለው መፈክር የተናገሩ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ናቸው። ስለዚህ ይህን የአጤ ልጅ ኢያሱን መፈክር "አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው" የሚለው ማክበር ይኖርብናል። ስለዚህ ዳር ደንበር የሁላችን ናት ብሎ መነሳት ይኖርብናል በ1968-69 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቤቱን ዘግቶ ልጆችን ለርሃብ ትቶ የዘመተው ለአጋዴ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል። ባድሜን ተዋግቶ መልሷል። ዛሬም ሁመራና መተማ ጋንቤላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬት መሆኑን መረዳትና ከዚህ በፊት የነበረው ዓይነት ትብብር ያስገልጋል።

አገርና ሃይማኖት አንድ አይደለም። ኢራክና ኢራን ያን ያክል ደም የተፋፈሱት የመሬት ጉዳይ ሁኖባቸው እንጂ ሃይማኖታቸው ሁሉም እስላሞች ናቸው። አንዳንድ ጠባብ ግለሰቦች በሃይማኖት ተሳበው አያገባኝም የሚሉት ምክንያት ከአገር ጋር ሊገናኝ አይችልም። ስለዚህ በጥሞና ማሰብና አገር የጋራ ነው የሚለውን መፈክር ይዘን ለአንድነት መነሳት አማራጭ የለውም።

## ምዕራፍ 4

## ይድረስ ለድርጅቶች

<u>መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ</u> ታህሳስ 26 ቀን 2001 ዓም ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ሲሰብኩ ብዙዎችን አስቀሰሱ። እርሳቸው "አደራችሁን የማንም ፖለቲካ ድርጅት ለመደገፍ አይደለም። በጎቹ እንኳ ሊያጠቃቸው ከመጣ አውሬ የሚድኑት ትንንሾችን ማህል አስገብተው ትልልቆች ዳር በዳር ከበው በኩርሚያቸው እየገፉ አያስቀርቡትም። ችግሩ የሚመጣው አንዷ በግ ሩጣ ከወጣች ነው። በእኛም አገር የቸገረው ሕብረት ማጣት ነው። ለ34 ዓመታት አንድ ባንድ እየተመረጠ እየተበላ ነው ከመበላት ለመዳን ቅድሚያ እኛ ሕብረት ሊኖረን ይገባል" ሲሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናኘት በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ዘርዝረው ለ48 ደቂቃ አስተምረዋል። በዚህ ቀን እርሳቸው አንድ ጥያቄ ምዕመናኑን ጠየቁ "ለሀገራችን ሆነ ለሕዝባችን ሰላም ለማምጣት ቅድሚያ ምን ማድረግ አለብን? ብለው ሲጠይቁ ምዕመናኑ በአንድ ድምጽ "ከራሳችን ጋር እንታረቅ ከእ እንጀምር" የሚል መልስ ይሰጣል። መምሕርም ቀጠል አድርገው "ከራሳችን መታረቅ ከፈለግን ስንቶቻችሁ ናችሁ ለስጋ ወደሙ የተዘጋጃችሁ" ብለው ሲጠይቁ አንድም የለም። የተረዳሁት ጉዳይ ቢኖር ከእኛው ጋር ካልታረቅን ወደ ድርጅቶች መግባቱ አስፈላጊ አይመስለኝም።

አቶ ስዩ አብርሃ <u>አዲስ ነገር</u> ጋዜጣ 2000 ዓም "ሻዕቢያ በእኛ ውስጥ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ከዚያ ትርፍ ለማግኘት እችላለሁ ብሎ የሚጎትተው ገመድ ካለ ጣልቃ ሊገባ ይችላል። ራሱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አያያዝስ ለእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ አይደለም ወይ? የራሳችንን ችግር በመግባባት ብንፈታ የውጭ ኃይሎች ዕድል አያገኙም ነበር" ሲሉ ተናግረዋል። በትጥቅ ትግል ብዙ ደም ፈሷል። ብዙ ሕዝብ አልቋል። ብዙ ሰው አገሩን ጥሎ ተሰዷል። ብዙ የምጣኔ ሀብት ኢኮኖሚ ወድሟል። የጎረቤት አገሮች ነፃ ጉልበት አግኝተዋል ንብረቱን በርካሽ ገዝተው ተጠቅመዋል። ሕዝቡን እያስተናገድን ነው ብለው ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ገንዘብ እየተቀበሉ ሀገራቸውን አዳብረዋል። በሕይወቴ ያየሁት ነገር ቢኖር በመጽሔት ሆነ በመጽሐፍ ያልተጻፈ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ላይ አርማጭሆ ወረዳ በ1971 ዓም የ21 ቀን ጦርነት ሲደረግ ነበርኩኝ። ቤቶች ተቃጥለዋል! በዚህ ሰዓት ሳይቃጠል የቀረ ቢኖር ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሲሆን የወደመው ንብረት ብዛት የሚያውቅ ያለ አልመሰለኝም። የአካባቢው ሁኔታ ሕዝቡን ለችግር አጋልጦ ሰጥቶታል። የቤት መስሪያ እሳር በግንቦት አይገኝም። ቤት የተቃጠለበት ሕዝብ ክረምት ዝናቡ ሲሄድበት ከርሟል። የመጣው የደርግ ጦር ድርጅቶችን አስጠግታችሁል በማለት ቤቱን ሲያቃጥል እህሉ አብሮ ወድሟል! የሚበላ ጠፍቶ በሰኔ ጫብሌ የሚባል ከመሬት ተምሶ የሚወጣ ስር



ሲበላ ተከርሟል። ይህ ጫብሌ የሚባለው ስር ቅድሚያ ተቀቅሎ ተከትፎ ከወራጅ ውሃ ላይ ተጥሎ ቢያንስ 3 ቀን ውሃ ከሄደበት በኋላ ተቦክቶ እንደ ቂጣ ተጋግሮ ይበላል። ሌላው ስር ስሙ ጠፋኝ እንጂ ተምሶ ሲቀቀል እንደ ድንች ይሆናል። ይህ ሲበላ ከርሟል። ይህን በዓይኔ ተመልክቻለሁ።

ይህ ሕዝብ በርሃብና በዝናብ ሲሰቃይ የከረመው የትጥቅ ትግል በመኖሩ ነው! እኔ የጠቀስኩት የዓይን ምስክር በነበርኩበት ወቅት ያየሁትን እንጂ ሌሎችም በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ውስጥ ብዙ ጦርነት ተድጓል። ታዲያ ዛሬም የሚዜመው ተመሳሳይ ሁኔታ ነው። በእርግጥ የትጥቅ ትግል የመረጡትን ድርጅቶች ልፈርድባቸው ባልችልም የተሻለ ትግል ምርጫ የለም ወይ? ሰላማዊ አመጽ ባንዱ የሚመጣ አለመሆኑን ለምን አልተረዳነም። ሕዝቡን በአንድነት ቁሉም ሸሁም ነጋዴውም አሽከርካሪውም አብራሪውም መስሪያ ቤቶችም ጽፈት ቤታቸውን እንዳይከፍቱ ሁሉም ከቤቱ እንዲውል የዚህ ዓይነት ሠላማዊ አመጽ ቢደረግ ወያኔ ሌላው ቢቀር አፈናውን ሊያቆም ይችላል። አገር እየቆረሰ መስጠቱን ሊተው ይችላል። ከላይ መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ እንዳሉት "ችግሩ የሚመጣው አንዷ ሩጣ ከወጣች ነው" ያሉት የዚህ አይነት አድማ ለማድረግ ሲታሰብ እንደ በጓ አንዱ አፈንግጦ እየወጣ ሕዝቡን ያስደበደበው መሆኑን የወያኔን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ነን ከሚሉትን የዚህ ዓይነት የጥቅም ሰዎች እንዳሉ አረጋግጠናል።

ሠላማዊ ትግል በሩ ክርችም ብሎ ተዘግቷል ይላሉ። በእኔ እምነት ክርችም አድርገው የዘጉት ራሳቸው እንመረሃለን የሚሉት ግለሰቦች ቆራጥነት ስለጎደላቸው ነው። ክህደት ሰላበዙ ነው። የሥልጣን ሱስነት ስለተጣባቸው ነው! ወያኔን ዘረኛ እያሉ እነሱ ከወያኔ የበለጡ ዘረኛ በመሆናቸው ነው። ለሕዝቡ የገቡትን ቃል ኪዳን መፈጸም ሲሳናቸው ነው። አሁንማ ታስሮ መፈታት ጀብድ ሁኖአል። ለውጭ አገር የሞኖሪያ ፈቃድ ማመልከቻም ተቃዋሚ ድርጅት በመሆኔ ታስሬ ነበር እየተባለ ነው። ታዲያ አንዴ ተጀመረና ተደከመ? አታጋይ ይሉሃል ይህ ነው። በእውነቱ ሊቀ ጠበብት መሰፍን ወልደማርያም "ሰላማዊ ትግል አልተጀመረም" ያሉት ትክክል ናቸው። ዳኛ ወ/ት ብርቱካን ዴሜቅሳም "ሰላማዊ ትግል ተጀመረ እንጂ አልተፈጸመም" ያሉት ለዚህ ነው። በገቡት ቃል መሰረት እንዞ በወያኔ ወሕይን ቤት እየተንገላቱ ናቸው። ምናልባት ከዚህ በፊት በሌሎች ግለሰቦች የደረሰው የሞራል ድክመት በእርሳቸውም እንዳይደርስ አእምሮ ሰባራ ሁነው የገቡትን ቃል ኪዳን እንዳይሰብሩት አደራ እላለሁ። ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው አለ እንደተባለው መጠንከር አለባቸው። አቶ ስዬ አብርሃ "በእኔ እምነት የሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል አማራጭ በኢትዮጵያ ተጀምሯል እንጂ አላለቀም። ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግልን ከመንግሥት ለውጥ ባሻገር ነው ማየት ያለብን። የትጥቅ ትግል መንግሥትን ለመቀየር ያስችል ይሆናል፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን በቦታው ለማስቀመጥ የተረጋጋ ማኅበራዊ ኑሮን ለመፍጠር ግን የሚያስችል አይደለም" ሲሉ አቶ ስዬ አብርሃ ተናግረዋል።

ልዑል እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከፈጠረ በኋላ በሰማይ የሚበሩ የማይሞቱ የማይታመሙ የማይጨበጡና የማይዳሰሱ ቅዱሳን መላእክትን ፈጠረ። የእነዚህን ቅዱሳን መላእክታን ቁጥር የሚያውቅ የሥነ መለኮት ሊቅ እንዳለ እንጃ እኔ አላውቅም። እንዳባባላቸው ግን የመላዕክቱ አለቃ ሳጥናኤል ይባል እንደነበር ያስተምራሉ። ሳጥናኤል ከሁሉ በላይ መሆኑን በመረዳቱ እኔነኝ የፈጠርኳችሁ ብሎ ይነሳል። በዚህ ወቅት ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሚካኤል ሌሎችን መላዕክት አስተባብረው የፈጠረን አምላክ ሳጥናኤል ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። ለአሁኑ በአካባቢያችን ባይኖርም እስኪመጣ ድረስ ባላችሁበት ርጉ ቢሉም ሌሎች የእነሱን ትዕዛዝ ከመስማት ይልቅ የሳጥናኤልን ትዕዛዝ በመስማታቸው ምክንያት ከሁለት ይከፈላሉ። በዚህ ወቅት ጦርነት በሰማይ ላይ ይሆናል። ሳጥናኤል ድል ይሆንና ከክብሩ ይባረራል። ስሙም ከሳጥናኤል ወደ ሰይጣን ይቀየራል። ሰይጣን ብቻ ሳይሆን ጋኔን፣ ርኩስ መንፈስ፣ ዲያቢሎስ፣ ሌላም ሌላ ተብሎ ይጠራል። ይህ ከዚህ በላይ ያነበብነው ትንሽ ስለ ሰይጣን ለምን እርሱ እኔ ፈጠርኳችሁ አለ? ወደሚለው ስንመጣ ለዚህ ትቢት ያበቃው ስልጣን በመፈለጉ ነው። ስልጣን የፈለገ ሴት ሆነ ወንድ ካህን ሆነ፣ወታደር ሌላም የሰው ልጅ ሁሉም የሰይጣን ትዕዛዝን እየሰራ መሆኑን መጽሐፍቱ ይናገራሉ። ለዚህም ነው በዚህ በመላዕክት ጦርነት ወቅት ተይዞ ታስሮ የነበረው ሰይጣን ወደ መሬት የተጣለ።

<u>የዮሐንስ ራዕይ</u> 6.12 "ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ሆነ፤ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፤ በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ" ሲል ጽፏል። እነዚህ ወደ ምድር ወደቁ የተባሉት ሰይጣናት ናቸው። እነዚህ ታስረው የነበሩ ሰይጣን ከቅዱሳን መላዕክት ጋር ታግለው ጥቃት ስለደረሰባቸው ወደ ምድር ተጣሉ። የቅንጅት ባለሥልጣኖች የተጣባቸው የስልጣን ስግብግብነት በራሳቸው ተጣልተው ተበታተኑ። እነሱ መበታተናቸው ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ" ብሎ ያስተባበራቸውን ሌሎችን ሕዝቦች ሳይቀር በታተኗቸው። እኔ እገሌ ቅዱስ እገሌ እርኩስ አልልም ነገር ግን ሁሉም ረክሰዋል። የሕዝቡን አንድነት በትነዋል። ለአንድ ዓመት ያክል የተጻጻፉትን የስም ማጥፋት ወረቀት ማንበብ ይዘገንናል። ከላይ ለምሳሌ የሳጥናኤልን ክብር እንደገለጽኩት ሁሉ እነዚህ የቅንጅት መሪዎች ታስረው በነበሩ ወቅት በተለይም በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ ፀሐይ፣ ዝናብ፣ ቀን ጨለማ፣ ሳይል እንዲፈቱ የጮኸው ሊከፋፍሉት አልነበረም። የተፈታው ሰይጣን ዛሬ በዓለም ላይ ሰላም እንደነሳው ሁሉ እነዚህም ከእስር የተፈቱት ወገኖቻችን ሰላም አልሰጡም በእርግጥ ሰላም ማምጣት ይቻላል ያም ይቅር መባባል ሲኖር ነው።

የኢትዮጵያ የሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅቶች ለማን እንደቆሙ የተረዱ አልመሰለኝም። አንዱ ሥህተት ይፈጽማል። ሁለቴ ይደገማል ሶስቴ ይሰለሳል። የኛው የሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅቶች የአገር ጉዳይ ሳይሆን የግል ማህበር አድርገው ማየት ከጀመሩ ከራርመዋል። ሌላው ትልቁ ቁምነገር ስምን እንደቆሙና ለማን እንደሚሰሩ አንዳንዶቹ የተረዱ አይመስለኝም።



ምክንያቱም አገሪቱ ከሌለች ሕዝቡ ከሌላ ለማንና ለምን እንደሚታገሉ አልተረዱም። ዘመኑ ያመጣው የድህረ ገጽ (ወይብ ሳይት) ላይ መግለጫ መስጠት ትግል ከሆነ አርፋችሁ ቁጭ በሉ። ወያኔ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ለያይቷል ትላላችሁ እናንተስ ብትሆኑ እርሱ ከሚሰራው የተለያችሁበት ምንድነው? ልዩነታችሁ ወያኔ በመሳሪያ አስገድዶ ጠበንጃውን ወድሮ መግደል ሲሆን የናንተው ደግሞ በዘር እያጠዛችሁት ነው? ተመልከቱ ውሾች አጥንት ሲያገኙ እኔ እግጥ እኔ እግጥ ሲናከሱ ሲዳሙ ይውላሉ። ነገር ግን ጅብ ሲመጣባቸው ሁሉም አጥንታቸውን ጥለው የጋራ ጠላታቸውን ለማጥቃት ይተባበራሉ። የግል ጠላታቸውን በሕብረት ከመለሱ በኋላ ወደ አጥንት ጠብ ይገባሉ። የኢትዮጵያ ታሪክ ያስተማረን በሥልጣን ምክንያት ይጣላሉ ነገር ግን ጠላት አገራቸውን ሊነጥቃቸው ሲመጣ ተባብረው ያጠቃሉ ይህን ታሪክ የዛሬው ትውልድ ሲሸረው ይታያል። በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመን ደጃዝማች ጓንጓል የሚባሉ የወሎ ባላባት ሸፍተው አውሳ በርሃ የገቡ ነበሩ። ጣልያን ኢትዮጵያን ሊወር በ1888 ዓም ሲመጣ እኒህ ደጃዝማች ለአጤ ምኒልክ የይቅርታ ደብዳቤ ጽፈው አብሬ ልሙት ብለው የገቡና የአድዋን ድል የተጎናጸፉ ናቸው።

ጳውሎስ ኞኞ <u>አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 167 "ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ በአጤ ምኒልክ ላይ ሸፍተው ከምኒልክ ጭፍሮች ጋር በጦርነት የተፈታተኑ ናቸው። በዚህም በትግራይ ዘመቻ ጊዜ በምኒልክ ላይ እንደ ሸፈቱና በረሃ እንደገቡ ናቸው። ምኒልክ 24 ቀን መርሳ ላይ ሠፍረው ሳሉ የደጃዝማች ጓንጉል መልክተኛ ከአጤ ምኒልክ ዘንድ መጣ። መልዕክተኛውም ጃንሆይ ከእርስዎ ተጣልቼ በረሃ ገብቻለሁ። አሁን ግን በአገሬ ላይ የውጭ ጠላት ስለመጣባት የርስዎና የኔ ጉዳይ ቀርቶ ይማሩኝና መጥቼ ከእርስዎ ጋር ሆኜ ያገሬን ጠላት ልውጋ ብለዋል ብሎ ተናገረ። አጤ ምኒልክም ተደስተው ይምጣ ምሬዋለሁ ብለው ላኩ። ደጃዝማች ጓንጉልም መጥተው ካጤ ምኒልክ ጋር ተገናኙ። ሠራዊቱም በእንደዚህ ያለ ጊዜ መጥቼ ከጌታዬ ጋር ልሙት በማለታቸው እግጅ ተደነቀ" ሲሉ ጽፈዋል። (አጤ)ልጅ ኢያሱንና ቤተሰቦቻቸውን አጤ ኃይለ ሥላሴ መግደላቸውና ማሳደዳቸውን በሚመለከት ሰነድ ማገላበጥ አያስፈልግም። ነገር ግን የ(አጤ) ልጅ ኢያሱ ልጅ ማለትም ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ለአባታቸው ገዳይ ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ለንደን ሳሉ ይጽፉላቸው ነበር። ልጅ ዮሐንስ እያሱ የኢጣልያንን ጉዳይ በተመለከተ ሰፋ አድርገው ነው የጻፉላቸው።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ <u>ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ</u> ቅጽ ሁለት ገጽ 152 "ግርማ ሆይ!እንዲሁ ያሉትን መረጃዎች የምንልክልዎት አንድን ሕዝብ ግፍ እንዳይደርስበት ጠባቂ ለሆነው የዓለም ማኅበር አባል አገሮችና እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጅ አገሮች ለሆኑት ሁሉ እርዳታቸው እንዳይለየን እንዲገልጹላቸው በማለት ነው። ፍጹም ትሑት አሽከርዎ፥ፈርማ፥ ዮሐንስ ኢያሱ ሐምሌ 18 ቀን 1930 ዓም" ሲሉ ጽፈውላቸው ነበር። ጽፈዋል። ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ከአባታቸው ገዳይ ጋር ደብዳቤ የሚጻፉት አገራቸውን ከአባታቸው አብልጠው በመውደዳቸው ነው።

ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ በጎንደርና በወሎ 56 ደጃዝማች ብለው ጣልያንን የወጉና ያዋጉ ጀግና አቤ ኃይለ ሥላሴ ከሎንደን ሱዳን ካርቱም ሲገቡ ቅድሚያ ለመያዝ ያሰቡት ልጅ ዮሐንስ ኢያሱን ነበር። አሜድላ ሲደርሱ ልጅ ዮሐንስ እንዲመጡ ተልከባቸው ደብረ ማርቆስ ተገናኙ ከዚህ ግዜ ጀምሮ በግዞት ኑረዋል። ሌሎች ባንዶች አገርን ከወራሪ ጋር ሁነው የጎዱና ሕዝብን ያስጎዱ ወዳጅ ሲሆኑ ልጅ ዮሐንስ እያሱ ግን እንደ ጠላት ታስረው ኖሩ።

የልጅ ዮሐንስ ኢያሱ እና የደጃዝማች ጓንጓል አገር ወዳድነት ዛሬ ላለነው ኢትዮጵያውያን ልንከተለው የሚገባን ነው። ለምሳሌ ወያኔ በሻዕቢያ ሲወረር አያገባነም ያሉ ደግኖች ነበሩ። ለዚህም አስመራ ድረስ የሄዱ የአገርን አንድነት እንዲናድ የተባበሩ ናቸው በዚሁ ዘመን በኢትዮጵያ ርሃብ ገብቶ በነበረበት ወቅት ሕዝቡ ወገኑን ለመርዳት ሲያስብ እንዚህ ዓይነት ግለሰቦች ሕዝቡ ርዳታ እንዳያደርግ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ነበሩ ዛሬ ደግሞ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ወያኔ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ሲባል አያገባንም ያሉ የድርጅት አሉ። የአቶ የኢያሱ ኢሕአፓ አባል የሆኑ ሰው ለአገሩ የሚንገበገብ ግለሰብ ከሰርግ አግኝቶ ሰላም ካላቸው በኋላ "የደንበሩን ጉዳይ እንዴት ተመለከትከው ሲላቸው የኢሕአፓው መሪ መልሳቸው እናንተ ጎንደሮች የራሳችሁ ሲነካባችሁ ትንገበገባላችሁ" በማለት ተናገሩ። እኚህ ግለሰብ በጎንደር ላይ ግዜያቸውን ያሳለፉ ወላጆቻቸውም ጎንደር የነበሩ ናቸው። አልገባቸው ብሎ እንጂ ጎንደሬዎች ጩኸታቸው ለኢትዮጵያ አንድነት እንጂ ለጎንደር ብቻ አስበው አያውቁም። ወያኔ አዲስ አበባን በመያዙ የደርግ መንግሥት ሠንድ ተቃጥሎአል ብለው ካልሆነ በቀር በ1969 ዓም አጋዴን ለማዳን በሬውን እየፈታ ልጆቹን በትኖ የዘመተው ጎንደሬ ዛሬ ማንነቱን በካደ ግለሰብ ሊሰደብ አይገባውም። ጎንደሬዎች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለዳር ደንበራቸው የታገሉ ናቸው። ሻዕቢያ ባድሜን ሲይዝ ወረራ በመሆኑ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር አብረው ዘምተዋል። በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ድርጅት በራሱ ድክመት እየጠፋ አስቸገረ እንጂ ጎንደሬዎች ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጋር ለሠላም መተባበራቸው አይካድም።

በአሜሪካን አገር ብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን እንኖራለን። ታዲያ የኢትዮጵያውያን ከቤተ ክርስቲያን በቀር በኢትዮጵያ መረዳጃ ማሕበር ሥም የተከራየነው ካልሆነ በቀር ሕንጻ አልገዛነም። ታዲያ በሲያትል የጎንደር እድርና መረዳጃ ማሕበር የራሱ ሕንጻ አለው። ይህ መረዳጃ ማሕበር ለቅንጅት መሰብሰቢያ አዳራሹን ሰጥቶ እንዲገለገሉበት አድርጓል። የማሕበራቱ አባላት ከቅንጅት ሆነ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅት ውስጥ በአባልነትና በደጋፊነት ገብተው የሚታገሉ መሆናቸው ተረስቶ "እናንተ ጎንደሮች የራሳችሁ ሲነካባችሁ ትንገበገባላችሁ" በማለት ተናገሩ። ጎንደሬዎች ያለ ኢትዮጵያ ሕልምና ምኞት በቀር ሌላ አሳብ የለነም። ባይሆን እንከባበር መናናቅ ይቅር ከሆነ አዎ እንላለን። ይህን በተመለከተ ሠንድ ጠቅሶ ዘርዝሮ መጻፍ ይቻላል። ስለዚህ የድርጅት መሪዎች ንቀታችሁን ተውን የምትፈልጉን ለስብሰባ ማዳመቂያ ሳይሆን የሀገራችን ችግር የሁሉ መሆኑን ልትረዱ ይገባል።



የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 045 መጋቢት 1995 ዓም ገጽ 8 "እነዚህ ከእንዲህ አይነቱ አደረጃጀት ነፃ ወጥተው መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያጠቃልል አመለካከትና አድራጎት ተቀዳጅተው በአንድነት ካልተንቀሳቀሱ በስተቀር የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ ሊያሟሉ አይችሉም" ሲሉ ከመጽሔቱ ጋር ባደረጉት የመጨረሻ ክፍል ተናግረዋል። ይህ ከፍተኛ የሕዝብ ቅስቀሳ ተደርጎ በድረስ ድረስ ቅንጅት ተመስርቶ ምርጫ 1997 ዓም ውጤት ማምጣቱ አይዘነጋም። ቅንጅት ተመስርቶ አብረው የተሰለፉት በአንድ ዓላማ ሁነው ሊሰሩ አለመፈለጋቸውን ሠነዶች ዋቢ ናቸው። መልመድና መለማመድ ያለብን ነገር ቢኖር በውይይት መተማመን ነው። በዚህ ወቅት በአቶ ልደቱ አያሌውና በእንጅነር ኃይሉ ሻውል በኩል ከሮ አለመግባባት ፈጥሮ የነበረ መሆኑን የተጻፈውን መጽሐፍት ማንበብ ይቻላል።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የነፃነት ጎህ ሲቀድ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 485 "በተለይ በልደቱና በኢንጅነር ኃይሉ መካከል ማን ምን ቦታ ላይ ይሁን በሚለው ጉዳይ በተፈጠረው ያለመስማማት ብዙ ወርቃማ ጊዜዎችን ያለ ሥራ አሳለፉ። ቅንጅቱ ለሚጠብቀው ሰላማዊ ትግል በቅጡ መዘጋጀት የነበረበትን ጊዜ በአመራር አካባቢ በተፈጠረው ክፍተትና ከአመራሩ በታች ያለነውን የድርጅት አባላት አስተባብሮ ማሰራት ባለመቻሉ ለተወሰነ ጊዜ ሽባ ሆን" ሲሉ ጽፈዋል። ዛሬ ቅንጅት የነበረውን ተሰሚነት እንዴት ሊያጣ ቻለ? ቅንጅትን በተመለከተ እንዴት ተቋቋመ እንዴት ፈረሰ ለሚለው ብዙ መጣጥፎች ወጥተዋል። ብዙ መጽሐፍትም ታትመዋል። በእርግጥ እነዚህ መጽሐፍት መታተማቸው ለወደፊቱ ስህተት እንዳይደገም ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። ቅንጅትን አስመልክቶ የተጻፉት መጽሐፍት ከእጄ የገቡት እነዚህ ናቸው።

እስክንድ ነጋ ምርጫ 97 መረጃና ትንታኔ 1997 ዓም
ልደቱ አያሌው ታህሳስ 1998 ዓም የአረም እርሻ
ማርቆስ ረታ ጥር 1998 ዓም የልደቱ ባንዳዊ ስሌት
ክፍሉ ታደሰ ግንቦት 1998 ዓም ግንቦት ሰባት
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግንቦት 1998 ዓም የነፃነት ጎህ ሲቀድ
ታምራት ታረቀኝ ጥቅምት 1999 ዓም ማንነት ሲጋለጥ ከመዐሕድ እስከ ቅንጅት
ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ ታህሳስ 2000 ዓም ቅንጅት ከየት ወዴት
ደበበ እሸቱ ታህሳስ 2000 ዓም የእምነቴ ፈተና
ታምራት ቢ ስመኝ 2000 ዓም "የዲሞክራሲ መሠረቶች በኢትዮጵያ የዓላማ አንድነት ለድል ወሳኝ ነው " ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጽሐፍት በቅንጅት ወቅት የነበረውን ደካማና ጠንካራ ጎን ገምግመው ጽፈዋል። እኔ እንደተረዳሁት እነዚህን መጽሐፍት በጥሞና ማንበብ ይጠቅማል በተለይም በሥነ መንግሥት በፖለቲካ መሪና አደራጅ የሆነ ሰው ሊማርባቸው ይችላል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መጽሐፍ ማንበብ የሚረዳው ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓም አዲስ አበባ ላይ የተፈጠረውን መድረክ እንዲጠነክር ትምርት ይሰጣል። አዲስ የተመሰረተው መድረክ ከቅንጅት መፍረክረክ ምን ሊማር ይችል ይሆን?።

## ምዕራፍ 5

## የኢትዮጵያ ምሁራን

ዲያቆን በሪሁን ወንድወሰን እስራት እንዳይፀናባችሁ አታፊዙ በተባለው የስብከት ክራቸው" አንዳንድ ሰዎች መሰልጠንን መሰይጠን አድርገው ወስደውታል። ለምሳሌ መሰ+ወደ መስ ለውጠውታል" ሲሉ አስተምረዋል። እኒህ የወንጌል ሰባኪ የኢትዮጵያንን ምሁራኖችን ጠባይ ተረድተውታል።እኔ የምመለከተው የነበረው እነዚህ የሰየጡትን ምሁራን ከፋፋይነታቸውን ለጥቅም ሲሉ መነታረካቸውን ነበር። ከመሰልጠን ወደ መሰይጠን መለወጣቸውን አልተረዳሁም ነበር። እነዚህ ምሁራን ከመሰልጠናቸው ብዛት የሀገራቸውን ማንኛውንም ታሪክ ሆነ ሃይማኖት እንደባብ ልብስ ውልቅ አድርገው ጥለውታል። እነሱ መተዋቸው ባልከፋ ሌሎች እንዲተው መጣራቸው ሆነ መሰይጠናቸው የባሰን። ዛሬ ዘመናዊ ሊቆች ሳይሆኑ ክህደትና ዘረኝነት እያስተማሩ ያሉት የሃይማኖት አባቶች ጳጳሳትና ካህናት ዲያቆናት ናቸው። በዚህ ባሳለፍነው 17 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቶያን ያለውን ድክመት ሊክድ የፈለገ ካልሆነ በቀር እውነቱ የት ላይ እንዳለ የሚጠፋው ያለ አይመስለኝም።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተዘጋጀ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያፈረሱት አባ መርቆሬዎስና ተከታዮቻቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዘው ተለዩ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 15 "ከፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አልተሾመም" የሚል ምዕራፍ ሳነብ ደንግጥኩ። ልባቸው እያወቀ አይናቸው እያየ እነዚህ ጳጳሳት ይህን መጽሐፍ አወጡ? ሰውን አይፍሩት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የቆምን ነን የሚሉ ጳጳሳት ሲሳሳቱ ማየቱ ለእኛ ለልጆቻቸው ሀፍረት ነው። ይህን መጽሐፍ በጥሞና ሳነበብ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠፋ የተፈረደባት በአባቶች መሆኑን ያመለክታል። ምክንያቱም እውነቱን የሃይማኖት አባቶች ከካዱት ሌሎች ምሁራንማ እንግዲያ ዓላማውያን ናቸው። ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ጳጳሳት አብዛኛው ዘመናዊ ተማሪዎች ሲሆኑ ሰልጥነዋል። ከላይ ዲያቆን በሪሁን ወንደሰን እንዳሉት "ሰልጥነዋል ሳይሆን ሰይጥነዋል" ሊባሉ የሚችሁ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያን አፍርታለች። የክርስትናን ታሪክ ለሚመረምረው ለቤተ ክርስቲያን ጥፋት ምዕመናኑ ሳይሆን የተማሩ አባቶች ናቸው። እምነት አለኝ ባይ አባቱን ገዳይ ይድረስ ለጳጳሳት መቼ ይሆን ይህን በልማን አፍቅሮታችሁት የምትተውት?

የሐዋርያት ሥራ ም/ 20 ቁ/28 " በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄዱሁ በኋላ ለመንጋው



የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ" ይላል። የሃይማኖት አባቶችን ለቀቅ አድርገን ወደ ዘመናዊው ምሁራን ስንመጣ ደግሞ የባሱ ናቸው።

ዶ/ር ኅጽሶ ጌ ድሌቦ ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለያዎች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 12 "አውሮፓውያን የፈጠራ ታሪካቸውን አስተማሩን የነፃ ትምህርት እድል ሰጡን። እኛም ያስተማሩንን አጠናን። ያነን ለሌሎች አስተማርን" ሲሉ ጽፈዋል። ለዚህም ነው አውሮፓውያን የሰየጡት "የሰው ልጅ ከዝንጀሮ የተወለደ ነው" ሲሉ አስተማሩ። ያንን ትምህርት ለሌሎች አደረሱት የኛም ምሁራን ተምረው ለሌሎች አደረሱ። አውሮፓውያን በተለይም ራሻ ዓለምን ያጭበረበሩበት "የራስን እድል መራስ ወሰን እስከ መገንጠል" የሚለው ከእነሱ ሳይሰራ የቀረውን ወደ አፍሪካ ወረወሩት። ሌሎች አውሮፓ እነሱ አንድ ሁነው የጋራ ገንዘብ ሲያወጡና ሕብረታቸውን ሲያጠናክሩ የአገሬ ምሁራን ይህን እየተመለከቱ መሻሻል ሲያደርጉ አይታዩም። እንዲያውም ይባስ ተብሎ ልዩነቱ በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ ነው። የሀገሩን ክብር ማስጠበቅ የሚችል ራሱ ሕዝቡ መሆኑን ቅድሚያ ምሁራን መረዳት አለባቸው።

እስፋ ጫቦ ዜጋ መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁጥር 8 ሚያዝያ 1993 ዓም ገጽ 24 "ትናንት በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና አይበገሬነት በጦር ሜዳው የበላይነታቸውን ያጡ ነጮች መልካቸውን በመቀየር እኛን መስለው በመግባት ሕዝቡን ከፋፍለው ለመበቀል ባላቸው ፍላጎት አስፈፃሚ በሆኑ መሪዎቻችን መጥተውብናል" ሲሉ ጽፈዋል። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ለስም ግብረ ሰናድ ድርጅቶች ቁጥር ብዙ ነው። ታዲያ ሕዝብ ሳይሆን የሚረዱ የሕዝቡን ባሕላዊ መተባበር ሳይቀር ለማላላት ጥረት እያደረጉ ነው። ተመራማሪ ነን ባዮች ዛሬ የትምህርት መመረቂያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ባህላዊ ቁሳቁስ ላይ የተመሰረተ ነው። በተለይ በአማራው ባህልና በተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ለምሳሌ በአማራው ባህል ከዘፈን እስክታ ጀምሮ ልቅሶና እንጉርጉሮ ምሽ የእዝን መተባበርን ሳይቀር ዝናሬው በወበራ አብሮ ማረስና አብሮ ማረም ማጨድ ሳይቀር የአንድነት ማተብ በመሆኑ ይህን ሊቆርጡ ሲነሱ ሳይገባቸው አስተርጓሚና ተባባሪ የሆኑት ምሁራን ናቸው። ምሁራኖች ሁሌም በራሳቸው ማንነት የማይኮሩ በመሆናቸው ዜና እንኳን በአውሮፓውያን ዘጋቢዮች ካልተመዘገበ እውነተኛ ዜና መስሎ አይታያቸውም።

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓም አንዱን ወዳጄ ምሁር ስልክ መታሁና ቅድሚያ "እንኳን ለብርሃን ልደቱ ለጌታችን ለመዳህኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል በሰላም አደረሰዎ" ካልኩ በኋላ ባለ በሌለ የሀገራችን ጉዳይ ስንብተከተክ ቆየን። ከዚያ እኔ ከሁመራ እስከ ጋንቤላ ለሱዳን ሊሰጥ ነው የተባለውን መሬት በተመለከተ አልሰማሁም? ስል ጠየኳቸው። ምሁሩ "በአውሮፓውያን ጋዜጠኞች ያልተደገፈ በመሆኑ" አሉኝ። እኔም አውሮፓውያን ካላወሩት አይቀበሉም ማለት ነው?ስላቸው መልሳቸው "አዎ" አሉኝ። ሌሎች

አውሮፓውያን ጋዜጠኞች ያልመዘገቧቸውን ድርጊቶች ጠቅሼ ለማሳመን ብሞክር ሊቀበሉ አልቻሉም። ካልጠበኩት ምሁር የሰማሁት በመሆኔ ደነገጥኩ። የእኛ ምሁራን ገንዘብ ስላጠራቸው እንጂ ቢኖራቸው ኑሮ እንደ ከያኒ ማይክል ጃክሰን ነጭ ለመሆን ግዜ አይፈጅባቸውም ነበር። እግዚአብሔርም አውቆ ሰማዩን አርቆ እንደሚባለው ሁኖባቸው ለዚህ የሚያውሉት ገንዘብ የላቸውም። ከላይ ልክ ሊቅ ላጽሶ እንዳሉት አውሮፓ የተማሩትን ትምህርት ለኢትዮጵያውያን እያስተማሩ ናቸው። በዘርና በሃይማኖት ሕዝቡ እንዲለያይ ያደረጉም እነዚህ ምሁራን ናቸው።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት</u> ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 143 "ኮሎኒያሊስቶች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አክብሮት ያላቸው ቢሆኑም በዚያው መጠን ጥላቻቸው ከፋ ያለ በመሆኑ ኢትዮጵያን ማዳከም ከተቻላቸውም ለመከፋፈል ወደኋላ ብለው አያውቁም። በበኩላቸው ለዚህ ስሜታቸውና ዕቅዳቸው የሚሰጡት ምክንያት ኢትዮጵያውያን እብሪተኞች አውሮፓውያንን የሚጠሉ እንደሌሎች አክብሮት አይሰጡንም። ከመጠን ያለፈ ሚዛን የጎደለው (ናሺናሊዝም) የሀገር ፍቅር ያደረባቸው ናቸው ወ.ዘተ..ለዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ባህርይና ድርጊት በግንባር ቀደም ኃላፊው አማርኛ ተናጋሪውና ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በአክራሪነት የሚያምኑ ወገን ነው የሚል እምነታቸውን ሳይደብቁ ጊዜና አጋጣሚ እየጠበቁ አማርኛ ተናጋሪውን ከሌሎች ጋር በማጋጨት በቅደም ተከተል ኢትዮጵያን ከመገዝገዝ ታቅደው አያውቁም። አዲሱ ዘዴ ብረትን በብረት በሚል ብልሃት በመጠቀም እርስ በርሳችን የማፋጀት እስተዋፅኦ አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ምሁራን የቀድሞዎቹ የሚማሩት ሕዝብን የሚያገለግሉበት ትምህርት እንጂ እነሱ ቀጭ ብለው ሕዝብን የሚበድሉበት ትምህርት ተምረው የተመለሱት በጣም ጥቂት ነበሩ።

የዛሬው ግን ቅድሚያ የናቁት ባህላቸውንና ታሪካቸውን ፊደላቸውን ነው። ምናልባት ደጋግሜ ስለ ባህልና ታሪክ ይታሰብበት እያልኩ በጽፍ ወድጄ ሳይሆን ፈርቼ ነው። ምክንያቱም ምሁራኖች ፊትኜ ስለተረዳሁ ነው። ሐምሌ 1 ቀን በ1991 ዓም ኳስ ጨዋታ አንድ የማውቃቸው ሊቀ ጠበብት ከሌሎች ምሁራን ጋር ቁመው ይጫወታሉ። ሁሉ ጉግሣ መጽሔት ሲገዙኝ ሊቀ ጠበብት "እባክህ አንተ ቄስ ነገር ስለሆንክ የቄስ ጹሑፍ ይሆናል የጻፍከው አልገዛም" አሉኝ። እኔም ጀምርኩት እንጂ አልቀሰስኩም። ዛሬስ ምነው ገጥቸበት በሆን ያሰኛል ግን ስለማልችል ቄስ አይደለሁም የቄስ ጹሑፍም አልጻፍኩም" ብዬ ማብራሪያ ሰጥቼ ገዙኝ። ከዚያ በኋላ እንደገና በሰኔ 29 ቀን 1994 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ የኳስ ጨዋ ላይ ከዘመድ ቤት ተገናኘንና ያላገኙትን እትሞች ሰብስቤ 8 መጽሔት ሰጠኋቸው።

እርሳቸው መጽሔቱን ሊወስዱት አልፈለጉም ኑሮአል። ከተቀመጡበት ወንበር ላይ ትተውት ሔዱ። እኒህ ሰው ምክትል ሚንስትር የደረሱ ናቸው። በዚሁ ቀናት ከኳስ ሜዳው ላይ ሌላም ምሁር ድክመት አስተዋልኩ። አንዱ ሊቅ ዶ/ር መጽሐፍ ገዝተው መጡና እኛ ከተቀመጥንበት ተቀመጡ። ወዲያው አንድ



ሰው መጽሐፍ ይዞ ይዞራል እኔ ስገዛ ተመለከቱ ምሁሩ "መጽሐፍ ማንበብ ትወዳለህ?" ሲሉ ጠየቁኝ እኔም እወዳለሁ አልኳቸው። ታዲያ ሊቅ ዶ/ሩ "ሰውየውን ስለማውቀው ገዛሁት አማርኛ ማንበብ አልወድም ለአንተ ይሁን" ሲሉ ሰጡኝ። እኔም አመስግኜ ተቀበልኩ። አንዴ ሊቀ ጠበብት ተሾመ ገብርኤል፣ ለዶክተር እገሌ መጽሔት ላከለት ብለው አድራሻ ሰጡኝና በተከታታ ላኩላቸው። ታዲያ አንድም ቀን ደረሰኝ ብለው ስልክ አልመቱም።

አትላንታ የኳሱ ጨዋታ ወቅት የኒህ ሊቅ ዶ/ር መጽሐፍ በገቢያ ላይ ውሎአል። እኔም ከሌሎች መጽሐፍ ከሚሸጡ ደራሲያን ጋር ምላ ለምላ እየተለዋወጥን ቆየንና ኋላ እኒሁ ምሁር መጽሐፍ ከሚሸጡበት ደረስኩ። እኔም ማንነቴን ገልጬ ከዚህ በፊት መጽሔት እልክላቸው እንደነበር ስነግራቸው ከራስ እስከ እግሬ ተመለከቱና "አንተ ነህ   አትመስልም ልጅ ሆንክብኝ" አሉኝ። በጥሞና ካስረዳኋቸው በኋላ ቀድመው እርሳቸው ፈረሙና ክፈል ብለው መጽሐፉን በጃቸው ይዘው ገንዘብ ሊቀበሉ ቋመጡ። እኔ" የራሴ መጽሐፍ አለኝ" ስላቸው ደማቸው ፈልቶ" በመጀመሪያ አንተ ክፈል ባለቤቴ ስትመጣ ተማክሬ እገዛሃለሁ። የአንተን መጽሐፍ ከዚህ ቀጭ አድርገኸው ሒድ" እንዳሳያት አሉኝ። እኔም ባለቤትዎ ሲመጡ እገዛለሁ ብያቸው ልሄድ ስል" እንዳሳያት መጽሐፉን ትተህው ሒድ" አሉኝና ትቼው ከሄድኩ በኋላ ለምን ተውኩላቸው አልኩና ከ5 ደቂቃ በኋላ ስመለስ ገልበጥበጥ እያደረጉ ሲመለከቱ ደረስኩና "ሊገዛ የሚችል መጽሐፍ ነው የአንተ መጽሐፍ $20 ሲሆን የእኔ ደግሞ $25 ነው ስለዚህ ልዩነቱን ክፈልና ውሰድ" አሉኝ ነገር ግን ባለቤታቸው አልተመለሱም ነበር።

አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች የተባለውን መጽሐፍ እንደታተመ ወዳጄ "ምሁራኑን ለመታዘብ ስለምትፈልግ እስኪ ለዶ/ርች መጽሐፍ በያድራሻቸው ላክላቸው" አሉኝና የ110 ምሁራን አድራሻ ሰጡኝ። 110 መጽሐፍ ለ110 ሊቆችና ዶክተሮች ባድራሻቸው ላኩኝ። ከነዚህ መካከል ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ሂሳቡን ልከውልኛል። ከነዚህ ከ110 መካከል አንዱ በቅርቡ መጽሐፍ ጽፈው እንድሸጥላቸው ስልክ ደውለው ጠየቁኝ። ከዚህ ያለነውን ሊበልጡ የተነሱ ምሁራን ለዚያ እርሶ አደር ወገኔ እንዴት ዋስ ጠበቃ ይሆኑታል? የሀገራችን ሰው ደግሞ መፈክሩ "የተማረ ይግደለኝ" እያለ ነው። ጥር 20 ቀን በ1996 ዓም ባህር ዳር ጠላ ቤት የሰማሁት አንዱ "የተማረ ይግደለኝ" ይላል እየደጋገመ ሌላው ይህን ቃል መስማት የሰለቸው" ዩንቨርስቲው በር ሕድና ተኛ ኢሕአዴግ ምሁራንን አባሮ ከናይጄሪያ 57 አስተማሪዎች አምጥቷልና ባልተወለደ አንጀታቸው ይረግጡሃል" ብሉ መለሰለት። የፈረንጆች ሁለት ሺህ ምሊንየም ላይ አሜሪካ ችግር ይፈጠራል ሲባል ብዙ ምሁራን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ነበሩ። ከዚያ በፊት የጠሏትን በዚህ ወቅት መጠጊያ ሊያደርጓት ተመለሱባት ታዲያ እነዚህ ምሁራን ይታመናሉ?

ሕዳር 19 ቀን 2001 ዓም ሲኤን ኤን የተባለው ኬብል ኩባንያ በዓለም ላይ በግብረ ሠናይ ተሰማርተው ለሕዝብ አገልግሎት ላደረጉ ከ4000 በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ውድድር አድርጎ ነበር። ታዲያ በዚህ ቀን አቶ ዮሐንስ ገብረ

ጊዮርጊስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሕጻናት የሚማሩበት መጽሐፍ አዘጋጅተው የሚረዱ በመሆናቸው ሲሸለሙ ተመልክቼ ከደስታዩ ብዛት አልቅሻለሁ:: መማር ማለት እንዲህ የዛሬ አበባዎችን የነገ ፍሬዎችን ሕጻናት መንከባከብ ሲገባ አብዛኛው የኢትዮጵያ ምሁራን ለግሉ ጥቅም ሲስገበገብ ይውላል:: የዛሬው ምሁራን ከአባቶቻችን የወረሰው ጥንካሬ የለም:: ሌላው ቀርቶ የሚሳቅበት አርሶ አደሩ ለማረስ በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚጠቀም ይህ ተምሬአለሁ የሚለው ሊያጠናው አልፈለገም የኢትዮጵያ አርሶ አደር ለዘመናት ሲያርሰው የነበረው መሬት በተፈጥሮ ማዳበሪያ እንጅ ከአውሮፓ በገዛው ማዳበሪያ አልነበረም:: ዛሬ የኢትዮጵያ መሬት እንደምሁራኑ የአውሮፓ ማዳበሪያ ለምዶ ያንን ካላገኘ እህል ሊያበቅል አልቻለም::

አውሮፓ ተገዝቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው ማዳበሪያ በመጀመሪያ አውሮፓውያን ምርምሩን ያደረጉበት በአውሮፓ መሬት ሲሆን ይህ ማዳበሪያ ኢትዮጵያ መጥቶ ሊሰራ አይችልም:: ምክንያቱም መሬቱ ተመሳሳይ አይደለም:: የአውሮፓ መሬት በረዶና ፀሐይ የሚፈራረቅበት የራሱ የሆነ ተፈጥሮ ያለው ሲሆን አውሮፓውያን ከብዙ ዓመታት ሙከራ በኋላ ያገኙት ነው:: አባቶቻችን መሬቱ እህል የማያበቅል መሆኑን ያውቁታል:: ስለዚህ ለአንድ ዓመት ረፍት ይሰጡታል:: ከብት እንዲከርምበት ይደረጋል:: ሌላም ሌላ መላ አላቸው:: በዚህ ዓይነት እህል አምርተው እነሱም በልተው ሌላውን አብልተው ኑረዋል:: ስለዚህ ምሁራን ያደረጋችሁት ነገር ቢኖር የአውሮፓን ባህል ለሰው እንዳስተማራችሁት ሁሉ የኢትዮጵያን መሬት የአውሮፓ ማዳበሪያ አስለምዳችሁ አርሶ አደሩ እህል ዘርቶ እንዳያበቅል አደረጋችሁት::

ደርግ አካባቢው ደን እንዲኖረው ደን ተከላ ብሎ የጀመረው እቅድ መልካም እንደ ነበር ሠፈራው ለአርሶ አደሩ መሬት ትርፍ እንዲኖረው አድርጎ የነበረ መሆኑን ወደ ኋላ መለስ ብለው ዛሬ "ደርግ ነበር መንግስት" ማለት የጀመሩ አርሶ አደሮች በ1997 ዓም ኢትዮጵያ ሕጁ የሰማሁት መሆኔን አረሳሁም:: ወያኔ የአርሶ አደሩ የነብስ አባት ነኝ ብሎ አርሶ አደሩንና የከተማውን ሕዝብ አለያይቶታል:: ለገበሬው "ይህ የከተማው ሕዝብ ባላገር ብሎ ይሰድብህ ነበር! እህል ግዛ ስትለው ሲከራከርህ ይውል ነበር! ኢሕአዴግ ከአውድማህ መጥቶ አንተ በጠራሃው ዋጋ እህልህን ይገዛሃል" እያለ ከአውድማ ጭኖ ይወስዳል:: በኔ ግም ሲል አርሶ አደሩ በርካሽ ለወያኔ ከሸጠው መልሶ በዱቤ ይገዛል:: ከተሜው ደግሞ እንደዱሮው ተከራክሮ መግዛት አይችል የወያኔን እጅ አይቶ እንዲያድር ተደርጓል:: ይህን የሚያደርጉት አንዳንድ ምሁራን ናቸው:: ስለዚህ መማር ማለት የሕዝብን ብሶት አብሮ መጋራት መሆኑ ተረስቶ ዛሬ መማር ማለት ሕዝብን ማደህየትና መናቅ ማንቋሸሽና ሆኖአል:: የኢትዮጵያ ምሁራን የአውሮፓን ሥልጣኔ ተቀብለናል ብለው ያስባሉ:: ነገር ግን ስብሰባና ግብዣ ሲጠሩ ተሎ የማይመጡ ምሁራን ናቸው:: ከአውሮፓውያን የሚወሰድ ሰዓት ማክበርን በውይይት መተማመንን የሀሳብ ፍጭትን ማስለመድ መሆን ሲገባው የኛዎቹ ደግሞ የተገላቢጦሽ አድርገውታል:: ሌላው የሚገርመው ምሁራኑ ሕብረት እንደማጣታቸው ሁሉ የቤተሰብና የወገን ፍቅር ማጣታቸው ነው::



ሊቅ ዶ/ር ጌቱ ገላይ ጭማቂ ጹሑፍ በተባለው መጣጥፋቸው
"እህያ መጣች ተጭና ጠላ
ያገራችን ሰው ወንድሙን ጠላ"
ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ሁለት ዘለላ ግጥም ዘርጋና ሰፋ አድርጋችሁ ብትመለከቱት ዛሬ በተማረው ሕዝብ ዘንድ መጠላላት ሞልቷል:: ምነው እንደመጠላላቱ ሕብረቱን ለማጠናከር ቢገፉበት? ወንድም ወንድሙን ክዷል:: እናትና አባት ልጃቸውን ክደዋል:: ልጆች ወላጆቻቸውን ክደዋል:: በተለይም ገንዘብን በተመለከተ ክህደቱ በዝቷል:: አንባቢያን አንድ ሰው በገንዘብ ከካዳችሁ ራቁት እንጂ አትቅረቡት:: ምክንያቱም በገንዘብ ከካደ በኋላ ከማፈሩ የተነሳ ሊገል ስለሚችል መራቁ ይመረጣል! ዘመኑ አስቸጋሪ ዘመን ነው:: አንድ አልረዳኝ ያለው ነገር ቢኖር ሕግን ኢትዮጵያውያን እንደፈለስፍነው መናገሩን ይተውት ይናቁት ነገር ግን ቋሚ የሆነ ሕገ መንግሥት እንኳን አልተቀረጸም:: ለምሳሌ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የነበረው ከሠንደቅ ዓላማው ላይ የዘውድ ምልክት ነበር! ብሔራዊ መዝሙርም እንዲሁ ነበር:: በደርግም ወቅት ከሠንደቅ ዓላማው ላይ አርማው ብሔራዊ መዝሙር ተለውጧል:: በወያኔ ኢሕአዴግም እንዲሁ ከሠንደቅ ዓላማው ላይ የተደረተው ምልክት አሳፋሪ ነው:: ከሠንደቅ ዓላማው ላይ ያለው ምልክት ሕብረተ ሰቡን የሚወክል ነው ቢባልም በሌሎች አገር ይህ ምልክት መጥፎ ነው:: ብሔራዊ መዝሙር እንዲሁ ቀርጿል:: ነገ ደግሞ ሌላው ቡድን መንግሥት ሲወስድ ሁሉንም መቀያየሩ አይቀርም:: ለምን ይህን እንኳን ምሁራን ሊወያዩበት አልሞከሩም?

የኢትዮጵያ ምሁራን ቁጥራቸው ብዙ ነው:: በተለይ ይህ አገር አጥፊው ትውልድ ያ ቂመኛ ትውልድ አቅዋም የለሽ ሁኖ አገሪቱንና ቤተ ክርስቲያንን በማፍረስ ላይ ይገኛል:: ከ1940 ዓም ወዲህ የተወለደው ትውልድ ሥልጣን የመያዙ ዓላማ ያልተሳካለት ትውልድ ተሰዶ ሆነ አገር ቤት የቀረው እንሆ አገርና ታሪክ አጥፊ ሆነ:: ምክትል ርዕሠ ብሔር አቶ ታምራት ላይኔ የዚያ ትውልድ አባል የነበሩ ኢሕአፓን ትተው ኢሕዴን የመሰረቱ ከዚያም ደግሞ ብአዴን የመሰረቱት በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ሰረከ ተብለው ታስረው ሲወጡ "ኢየሱስን አገኘሁት" ብለው ሁለት እጃቸውን አንስተው ማልቀስ ተግባራቸው ሆነ:: ሌሎችም እንዲሁ በተለይ በስደቱ ዓለም ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እያመሳት ያለው የዚያ ትውልድ ምሁር ነው:: መማር ማፍረስ መበተን መሆኑን የተረዳሁት በቅርቡ ዓመታት ነው:: በእርግጥ የአጥፊው ምሁር አቅም በዝቶ እንጂ አገር እንትድተላመ የሚያስብ ምሁር የሉም ማለት አይደለም አሉ::

<u>የማቴዎስ ወንጌል</u> ምዕራፍ 29 ቁጥር 9 "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶች እነሱ እንዳሰቡት ሙቶ ይቀራል ብለው ነበር:: ነገር ግን መቅደላዊት ማርያምና ሌሎች ሴቶች ከመቃብሩ ደርሰው ባጡት ግዜና ደንግጠው ሲያለቅሱ በነበረበት ወቅት "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ብሎ ተገለጸላቸው:: ታዲያ አምላክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ሠላም ለናንተ ይሁን" እንዳላቸው ሁላ ኢትዮጵያውያን ማንኛውም አማኝ "ሠላም ለኩልክሙ"ይላል:: ይህ ቃል ግዕዝ ሲሆን አማርኛው "ሰላም ለእናንተ

ይሁን"ማለት ነው:: ሰላም በአርብኛ እንዲያውም እንደምን አደራችሁ ሲሉ "ሰላማ ሊኩም" ይላሉ የማታውቀው ሰው ባጋጣሚ ቢያገኘው "ሰላም" ይለዋል:: ሰላም በሕብሩም እንደ ግዕዙ ሰላም ማለት ሲሆን ሰላም በፐሊ.ገን ቋንቋ ተጋሉ አመሰግናለሁ ማለት ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናን ይሁን ባለው መሰረት እኛም አምላካችን ለኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰጥልን ለአንድነት የሚያስብ አስተዳዳሪ እንዲሰጣት ወይም ያሉን መሪዮች ሃይማኖታዊ ምግባር ይዘው ለሕዝቡና ለአገሪቱ ሰላም እንዲሰጠን በያለንበት ሰላምን እንለምን:: ያሉት መሪዮቻችን ጠበንጃ "አምላኬ" ከሚሉ እግዚአብሔር አምላኬ ብለው ስሙን እንዲጠሩ ልዑል እግዚአብሔር ልብ ይስጣቸው:: መሪዮች ሃይማኖታዊ ምግባር ስለጎደላቸው ለአገር ሆነ ለሕዝብ ሰላም አልሰጡም:: መሪዮች ሰላም ካሰቡ ፍርድ ቤቶች መድሉ አይፈጽሙም:: ድሃ ተበደለ ሕዝብ ተቸገረ የሚል ፍርድ ቤት ካለ ሰላም ያገኛል::

የካባ ሲሳይ አምባው የጣረ ይወጣል በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 91
"ሁለት ሺህ ዓመት ሞላ በአገራችን
ብቃ በላት አምላክ ቸሩ ፈጣሪያችን
አንተን ስትማፀን አክብራ ቃልክን
ምሕረት አውርድላት አምላክ አባታችን
በእምነት ተዋሕዳ ቃልክን ተቀብላ
ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ሁንላት ከለላ
ሁለት ሺህ ዓመት ሲጀምር አንድ ብሎ
ድረስ ለኢትዮጵያ አምላክ ሆይ በተሎ::
እንፀልያለን ቀንና ሌሊት
ኢትዮጵያን ባርክላት የዓለም መድኃኒት
ልጆችዋ በሰደት ስንከራተት
ምሕረት አውርድላት የፍጥረት አባት
የሚታረስ ምድር እያለን መሬት
ወራጅ ውኃ ተርፎ እያለ በጅረት
እርሃቡ ገደለን ሰላማን ሕብረት::
ድርቅ በርትቶባት የሚበላ ጠፍቶ
ሰላም ሰላማን ዝናብ መዝነብ ቀርቶ
ችግር በሽታ ሁሌም ሲያጠቃን
እግዚአብሔር ይብቃ ብለህ ሰላሙን ስጠን
ታምርህ ይብዛላን ለእኛ ለልጆችህ
ለሕዝበ ኢትዮጵያ ይምጣልን ሰላምሕ" ሲሉ ጽፈዋል::

እኛ ኢትዮጵያውያን በስደቱ ዓለም በተለይም አሜሪካ ከመጣን ሰነባብተናል:: ታዲያ ሕዝቡን አንድ አድርጎ የያዘው ተቋም ሁለት ናቸው:: እነሱም የኢትዮጵያውያን የሰሜን አሜሪካ የእስፖርት ፌዴሬሽንና የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (አርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው:: እነዚህን ተቋም ምሁራን ለመበተን ጥረት እያደረጉ ናቸው:: አንዳንድ ሰዎች ከግል ጥቅማቸው ጋር በማያያዝ ገንዘብ ካላገኙበት ጥቅም የሰጠ መስሎ አይታያቸውም::



ለወደፊቱ ብዙ ኢትዮጵያውያንን የሚያገናኝ ከጎሳና ከሃይማኖት የፀዳ ተቋም መሆኑ ሲታወቅ ዛሬ የወያኔ ደጋፊዮች ለማጥላላት ጥረት ሲያደርጉ ይገኛሉ::ከዛሬ 26 ዓመት በፊት ቁጥራቸው አራት የእግር ኳስ አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ቡድኖች የተጀመረው የኢትዮጵያ እስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ በያመቱ ኢትዮጵያውያን እንድንገናኝ መንገድ የከፈተ ማዕከል ነው:: ይህ የተቀደሰ ማዕከል የተጀመረው በ1977 ዓም ወይም በ1984 ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ብዛት ያላቸው የአሜሪካን ከተሞች ከኒትባዎችና ታላላቅ ሆቴሎች የሚያውቁት ግዙፍ ማዕከል ነው:: ይህ ማዕከል ኢትዮጵያውያንን ማገናኘትና ባሕላቸውን እንዳይረሱ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን በያመቱ ከሰበሰበው ገንዘብ ከመቶ ሺህ ዶላር በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለድርቁ የለገሰ ነው:: በአገሪቱ አንቱ የተባሉት ታላላቅ ሰዎች የክብር እንግዳ አድርጎ ይጋብዛል:: ከዚህ አገር የተወለዱት ኢትዮጵያውያን ባሕል አለን ብለው እንዲኮሩ ከኳሱ ሜዳ ላይ በኢትዮጵያውያን የባሕል ድምጻውያን በአገር በቀል ልብስ አሸብርቀው የክብር እንግዶች እየተመለከቱ ቀኑ ዘፈን ይዋላል::

ይህ የሰውነት ማጠንከሪያው የእስፖርት ፌዴሬሽኑን ከማይወዱት መካከል ወያኔ ነው:: ሁሌም በኳሱ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ይሰባሰባሉ:: ታዲያ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን እድል ተጠቅመው የየራሳቸውን ስብሰባ ያካሂዳሉ:: በዚህ ስብሰባ ላይ ወያኔ ድክመቱ በባለሞያዎች ተብጠርጥሮ ይነገራል:: በዚህ ተቋም ሌሎች የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ወያኔ በ1990 ዓም ተጠቅሞበታል:: ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ የአይደር ተማሪዎች የደበደበበትን በስዕል ድምጽ ቪዲዮ ክር በማሳየት ኢትዮጵያውያን አብሮአቸው እንዲቆም ጥሪ ያቀረቡበት አትላንታ ላይ ነበር:: ዛሬ ወያኔ በዚህ ተቋም ላይ ዘመቻ ማድረግ ጀምሯል::ዛሬ እንደ ኳሱ ሁሉ ኢትዮጵያውያንን በዓለ ጥምቀትን ከሜዳ ላይ ታቦት አውርዶ በማሳደር ለማንነታችን ኩራት የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሉብ አንጀለስ የተጀመረው በዓል ታላቅ እየሆነ መጥቶአል:: ይህን ቅዱስ ዓላማ የጀመረችው ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሉስ አንጀለስ ስትሆን ከአደር አደር ሌሎች በአካባቢዋ ያሉት ቤተ ክርስቲያን ታቦታቸውንና ምዕመናናቸውን አስተባብረው በዓሉ በታላቅ እንዲከበር እያደረጉ ነው:: በዚህ የጥምቀት በዓል ወንጌል ይሰበካል:: ሕዝቡ ከአገሩ ቢርቅም በዓመት አንድ ጊዜ ይህን የመሰለ በዓል አክብሮ እንዲውል የተደረገው በተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና የሃይማኖት አስተማሪዎች ጥረት ነው:: በዚህ አጋጣሚ የሉብ አንጀለስን ቤተ ክርስቲያኖች ጅምራችሁ ከፍ እንዲልና እየጠነከረ እንዲመጣ ጥረታችሁን አምላክ ይባርክላቹ ለወደፊቱም በርቱ እላለሁ::

ከዚህ በላይ በተወሰኑ የኳስ አፍቃሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አክባሪዎች ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚሰጡት ጥቅም ባጭር የተጠቆመ ሲሆን በምሁራን በኩል ግን የተመሰረተ ተቋም የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያቀራርብ የለም:: በምሁራን በኩል የተመሰረተው ተቋምማ ልዩነትና ጠብ ናቸው:: ዛሬ ዶ/ር እገሌ የድርጅት መስራችና መሪ ናቸው:: ዛሬ ዶ/ር እገሌ የቤተ ክርስቲያን

መስራችና መሪ ናቸው:: ሌሎች የመሰረቱትን ተቋም መበተን እንጂ ማሳደግ የማይችሉ ምሁራን ናቸው:: የሀገራቸው ደንበር ሲደፈር አይሰማቸውም:: ቀይ ባሕር ከኢትዮጵያ መራቋ አልበቃ ብሎ ጠላቶቻችን ዛሬ ደግሞ በዓባይና በአጋዴ ላይ ተጠናክረው ኢትዮጵያን ሲያፈርሱ ሲሰበስቡ ምሁራን ዝም አሉ?

የካባ ሲሳይ አምባው <u>እግዚአብሔር አልረሳኝም የለመንኩትን አልነሳኝም</u> ያልታተመ:: "አገሬ ኢትዮጵያ ለዘላለም ኑሪ
ምኞቴ ነውና እንድትከበሪ
ሀገሬ ኢትዮጵያ ኑሪ ለዘላለም
ጥሉ አይጥልሽም ባለ መድኃኒዓለም
አምናለሁ መኖርክን ጌታ ከመንበርህ
አትርሳት አገሬን ይድረሳት ምሕረትህ
ሕዝቡ ተቸግሮ የሚበሳውና የሚጠጣው አጥቶ
ኢትዮጵያ ፀሎቷ ነውና አይቀርም ተጠምቶ
እንጀራ ሆነና የሰው ቁምነገሩ
አልቀበር ብሎአል ሰው ሁሉ ካገሩ
እናቴ ኢትዮጵያ ምን ይሆን እድልሽ
አልወጣልሽ ያለው ከልጅ ከምሁርሽ
ኢትዮጵያ አገሬ በጣም ትልቅ ነበርሽ
እጇ ጠባብ ለባሽ ብዙ ልጅ አፈራሽ" ሲሉ ጽፈዋል:: የኢትዮጵያ ምሁራን ባህላቸውን ታሪካቸውንና ሃይማኖታቸውን ጠልተዋል:: የእኛ ምሁራን የሩቅ ተመልካች የራሱን ፈንካች ከሆኑ ከርመዋል:: ለዚህም ብዙ የታሪክ ሰነድ ማገላበጥ ይቻላል:: የኛው መማር ማለት መሰልጠን፣መሰይጠን መሆኑን ካወቀ ጀምሮ በሃይማኖታቸው በታሪካቸው በፊደላቸው ላይ ንቀት አደረባቸው::

ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ <u>መልክዐ ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 236
"በቀደም አግኝቸው መሸሻን ከመንገድ
ጥያቄ ብሰጠው በታሪክ ረገድ
ሊመልስ አሰበ ልቡም ተጨንቆ
ባይኑም አስተዋለ በአንጎሉም ጠየቀ
ብዙ ወሸከተ እየዘባረቀ
እንዲያው ደከመ እንጂ ምንም አላወቀ::
ተሰማን ጠርቼ ባጨዋውተው
እንኳንስ ሊመልስ ምንም አልገባው
ወዲያው ከተፍ ሮለ ደግሞ አቶ ጣሰው
እሱም እንደነሱ እጅ እግሩ ጠፋው::
ባልሳችን ረስተው የዛሬ ልጆች
ቋንቋችን ዘንግተው ያሁን ወጣቶች
ሳይ ታች ሲሉ እያየሁ ሁላቸውንም
ጠርቼ ብጠይቅ አንዱን በቀደም
አማርኛ ለካስ ፍጹም አያውቅም" ሲሉ ጽፈዋል::



## ምዕራፍ 6

## እንደ ቀይ ባህር ዓባይንና አጋዴን እንዳናጣ?

ርዕሠ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም <u>አዲስ ዘመን ጋዜጣ</u> የካቲት 27 ቀን 1982 ዓም ገጽ 15 "እንደሚታወቀው ሀገራችን የምትገኝበት አካባቢ እንደዛሬው ሁሉ ቀድሞም በየዘመኑ የተነሱ ገናና መንግሥታትን ትኩረት የሳበ ስትራቴጂካዊ አካባቢ ነበር:: በዚህ የተነሳ ከተስፋፊዎች ቅኝ ገዥዎችና ወራሪዎች ጋር በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል:: በዚህ አንጻር በተለይ ከውጭው ዓለም ጋር መገናኛ በራችን የሆነውን የቀር ባሕርን እለኝታችንን ማስከበሩ ብዙ ጦርነቶች ውስጥ የዳረገን መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ከዚህ አካባቢ የሚቀጣጠለው እሣት በአጠቃላይ የሀገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ የጣሉባቸው ተደጋጋሚ አጋጣሚዎች እንደ ነበሩ የሚዘነጋ አይደለም:: እንደውነቱ ከሆነ የሀገራችን የረጅም ጊዜ ታሪክ አንድነታችንና ሕልውናችንን የማስከበር የጦርነት ታሪክ ነው ለማለት ይቻላል:: በአንድ ወቅት ገናና ሥልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሳ የነበረችው ሀገራችን በኋላቀርነት ታፍና መቆየት መሰረታዊው ምክንያት ይህ ነው" ሲል ከሸንገው ያነበቡትን አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 27 ቀን 1982 ዓም አውጥቶታት:: ይህ መጣጥፍ 40 ገጽ ሲሆን የዳሰሱት ብዙ ቁምነገሮችን ነው::

ሹመት ሲሻኝ <u>የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት</u> ትግል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 16" አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ሥር ባሉት በጥቁር ሕዝቦች መካከል የፖለቲካና የሞራል መነቃቂያ ምሳሌ ትሆናቸዋለች ብለው ስለሚሰጉ በክፉ ዓይን ይመለከቷታል:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ጊዜ ካገኘች እንደ ጃፓን ታይል ይሆናል የሚል ፍራቻ አላቸው:: ይህ ዓይነት አዝማሚያ ስላላቸውም ኢትዮጵያን የሚሸራርፍና ኃይሏን የሚወስን ሁኔታ ቢያዩ ደስ ይላቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ሊቀ ጠበብት ሹመት ከላይ ያነሱት ታሪክ ኢትዮጵያን ለማድከም ዋናው አንዱ መሳሪያ ይህ ነው:: ከዚህ በፊት ጦርነት ሲያማዝዙና ደም ሲያፋስሱ የነበሩ ቦታዎች የኢትዮጵያ ምሁራን አልታያቸውም:: በዓለም ላይ ብዙ ታላላቅ አገሮች ኃያል ሲሆኑ ኢትዮጵያን ለማንበክከር ያልተነሳ ማንም አልነበረም:: ኢትዮጵያን ከዓለም በፊት ለመውረር የመጣው ሕንድ በ1985 ዓመተ ዓለም በአጤ ራማ የተመራ ሲሆን በዓባይ በኩል ይምጣ በቀይ ባሕር በኩል ግልጽ የሆነ ቦታውን የሚጠቁም ሠነድ ላገኝ ባልችልም ንጉስ ራማ የሞተው ትግራይ ውስጥ መሆኑን የሞተበትም ዛሬ ድረስ ራማ ተብሎ ይጠራል::

ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ አሉ አባቶቻችን አለቁና ዛሬ ያለው ኢሕአዴግ መንግሥት ጀግኖች ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስከሰው ከወራሪ ጠብቀው ያቆዩልንን አገር ለሥልጣን ማስንበቻ ተብሎ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳ ሊሰጥ ታቅዷል:: ወደኋላ ተመልሰን ታሪክ ስንቃኝ

አባቶቻችን ኢትዮጵያን ያቆዩልን ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ጀምረው የመጡብንን ወራሪ ድል እያደረጉ ነበር። ለምሳሌ በ1985 ዓመተ ዓለም ከሕንድ የመጣው ንጉሥ ራማ ተደብድቦ ቀርቷል።

በ1600-1500 ዓመተ ዓለም መካከል ግብጽ ልትወር መጥታ ተጠቅታ ስትመለስ ኢትዮጵያውያን ተከትለው ግብጽን ለ400 ዓመታት ቅኝ ግዛት ገዝተዋል። ጥቁር ፈርዖኖች ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኢትዮጵያውያንን ከብጽን ያስወጣቸው የፋርሥ ወራሪ ሲሆን ኢትዮጵያ ከዛሬው ሱዳንና ግብጽ ደንበር ላይ ጠረፏን አስከምራ ኑራለች። ፋርሥን ከግብጽ አባሮ ያስወጣው የክሪኩ አሌክሳንዴር ሲሆን እርሱም ኢትዮጵያን ለመውረር አቅዶ ቅድሚያ ራሱ ለስለላ ገብቶ በንግሥት ሕንደኬም ሰላዮች ተደርሶበት ታስሮና ተዋርዶ ተመልሷል። የግሪኩን ወራሪ ከግብጽ ያባረረው የሮማውያኑ ወራሪ ሲሆን ግብጽን ይዞ ኢትዮጵያን ሊወር ስለመጣ ኢትዮጵያውያን ወግተው መልሰውታል የሮማውያኑን ወራሪ ከግብጽ ያባረረው ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተነሳው የእስልምና ሃይማኖት ኃይል በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ላይ ቀጥተኛ ጦርነት አልገጠመም ነበር። ነገር ግን የእስልምና ሃይማኖት ኃይል ተስፋፊዎች ኢትዮጵያ ከባህር ማዶ የነበራትን ግዛት እንድታጣ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የባሕር ኃይልና የበላይነት እንዲመታ ሆኑ። ትልቁ ውድቀት ከዚህ ቢጀምር ከባህር ወዲህ ያለውን ግዛቷን ከሌሎች ወራሪዎች ጋር አንዴ በሃይማኖት በሌላ ጊዜ በንግድና በጉልበት ለመያዝ ቱርኮች በመምጣታቸው አባቶቻችን አሳፍረው መለሱአቸው።

የቀድሞ የባሕር ኃይል መለዮ መለዮ ለባሾችና ሲቪልሠራተኞችየኅብረት ሥራና መረዳጃ ማህበር ነው ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍና ባሕር ኃይል በተባለው መጽሐፍ ገጽ 44 “አዲሱ የአረቦች የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኃይሉን አጠናክሮ የአክሱማውያንን የባሕር ማዶ ግዛትና ኃይል በመደምሰስና በመቆጣጠር ብቻ ሳይወሰን በዘመኑ የታወቁትን ሁለቱን ኃያላን የሮማውያንንና የፋርሳውያን ኃይሎች ጭምር በመደምሰስና በአክሱም መንግሥታትም ላይ የገለልተኝነትና ውድቀት ተፅዕኖ በማሳደር ለዓባይ ሸለቆ ለቀይ ባሕርና ለኤደን የባሕር ሰላጤ የንግድ እንቅስቃሴ ሰላም ፀጥታና ዋስትና ለመስጠት በብቃት ተደራጅቶ የነበረው የየብስና የባሕር ኃይላችን ቀስ በቀስ እንዲደክምና በቀላሉ ለማንሰራራት በማይችሉበት ሁኔታ እንዲወቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል” ሲሉ ጽፈዋል።

የአውሮፓ ወራሪ ዜጎችን ለማስፈታት ብሎ የእንግሊዝ ጦር ቢገባ ብዙ ሳይቆይ ወጥቶ ሲሄድ ግብጽ ኢትዮጵያን ልትወር ስትመጣ ተደብድባ ተመልሳለች። ወዲያው ጣልያን በምጽዋ በመምጣቷ ዶጋሊ ላይ ድል ሆነች። ድርቡሽ ሕዝብንና ቤተ ክርስቲያንን አቃጥሎ ሲመለስ የኢትዮጵያ ልጆች መተማ ላይ ብድራቸውን መልሰዋል። ኢጣልያን አድዋ ላይ ድል ሁኗ ተመልሳ ነበር። ከዚያም እንደገና አየርና መርዝ ይዛ ኢትዮጵያን ወረረች። ለተወሰኑ ዓመታት የኢትዮጵያን ዋና ከተማ ተቆጣጥራ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጋዝ መርዝ ብትፈጅም አባቶቻችን በጀግንነታቸው ጣልያንን አባረው ክብራችን



አስከብረው ኢትዮጵያን አቆዩን። ሱማሌም ልትወር መጥታ ተደብድባ ተመለሰች። የትናንቷ ኤርትራም ወረራ ጀምራ እንደ ክርስትና አባቷ ጣልያን ተደብድባ ተመልሳለች።

የቸገረን የውጭ ወራሪ አንለው የአገር አስተዳዳሪ የኢትዮጵያውያንን ክብር አስደፋሪ የሆነው የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ጉንብስ ቀና እያለ ነው። ላሚቱ ጃርት ወልዳ እንዳትልሰው ወጋት እንዳትተዎው ልጅ ሆነባት የተባለው ተረት በኛ ደርሶ የውጭ ወራሪ አንለው ጥቁር ነው! የአገር አስተዳዳሪ አንለው አገር ገንጣይና አስገንጣው ሕዝብን በሃይማኖትና በዘር ከፋፋይ ነው? ይህን ሰው ማን እንበለው? ሰው ወይስ ሰይጣን? ፍጥረቱ ከሰው ሲሆን ተግባሩና ሥራው ደግሞ ሠይጣን ነው። አንባቢያን ልብ ወለድ እንዳይመስላችሁ ከዚህ በላይ በጻፍኩት ሰድ ንባል ላይ መሰረት ለማስያዝ የታሪክ መጽሐፍት መጥቀሱ ለአንባቢያን ይጠቅማል።

1ኛ ሕንድ ኢትዮጵያ መውረሯን አስመልክቶ አለቃ ታዮ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ገጽ 18-19 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ኑቢያ አክሱም ዛጉዬ ገጽ 35 የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል የ1660 ዓመት ታሪክና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና እቅድ መስከረም 1983 ዓም ገጽ 32

2ኛ ግብጽ ኢትዮጵያን ለመውረር መጥታ ተጠቅታ ኢትዮጵያውያን አባረው ግብጽን ብቅኝ ግዛት የያዙ መሆናቸውን አስመልክቶ አባ ተሥፋ ሥላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትጵያዊ ነው የተዋሕዶ እንበሳም መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በተባለው መጽሐፉ ገጽ 101 ከላይ የተጠቀሰው የአቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ገጽ 17-117-118-119 የተጠቀሰ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ግብጽን የገዙት ስማቸው ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገጽ 118-119 “ሰበቆን÷ሻባካ÷ሰበኩስ÷ሻባታቃ÷ ወይም ታራቆስ÷ታርሐቃ÷ ሻባካ÷ ባታካ÷ታርሐቃ÷ታኑታመሙን÷ፔያንኪ÷ሻበሻ÷ሻ÷ባታቃ÷ታርሐቃ÷ታኑሙን” ሲሉ ዘርዝረው ጽፈዋል። ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 819 “የኢትዮጵያ ንጉሦች ግብጽን እየቀላቀሉ ይገዙ ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

3ኛ ፋርስን አስመልክቶ መራረስ አማን በላይ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 113 እንዲሁም የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 139-141-142 ሌሎችንም መመልከት ይቻላል።

4ኛ የግሪኩን ወራሪ አስመልክቶ ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 7“መለስ ብለን ከታሪካችን ውስጥ በመጠኑ ብንመለከት የሚያኮራንና የሚያስመካን ታሪክ ማግኘት እንችላለን። ከክርስቶስ ልደት በፊት በግሪክ ላይ ነግሦ የነበረው ታላቁ አልክሳንደር ግዛቱን

እያሰፋ ከመቆዶንያ ግብጽ ድረስ ተሻገረ። ብዙ አገሮችም በጦር ሳይሆን ገና በዝናው እየፈሩ ገበሩለት። ኩዊንተስ ኩርቲውስ የተባለው የዘመኑ ታሪክ ፀሐፊ የአሌክሳንደርን ግዛት ማስፋፋትና ለጦርነት መነሳት ሲገልጽ ወጣቱ ለጦርነት ሲነሳ የምወረው ግብጽን ብቻ አይደለም ኢትዮጵያን ጭምርት ነው ማለቱን ጽፏል። አሌክሳንደር ዝቶ እንደተነሳው ከግብጽ ጀምሮ ሕንድ ድረስ አስገበረ። በመሐል ግን ኢትዮጵያ ከገባሪዎች ተነጥላ ቀረች።"

"አሌክሳንደር ስለ ኢትዮጵያ ጀግንነት ሰምቶ ነበርና ከኢትዮጵያውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም ፈራ። ስለ ኢትዮጵያውያን የሚነገረው ጀግንነት እውነት ስላልመሰለው ራሱ አለክሳንደር ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰለል ተነሳ። ክሮኒክልስ ኦፍ ጆን ቢሾም ኦፍ ኒኩ በሚባለው መጽሐፉ ላይ እንደሚተርከው አሌክሳንደር ከምርጥ የጦር አለቆች ጋር ሆኖ ሁሉም ተራ ሰው መስለው ለመሰለል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬም አለክሳንደር ተራ ሰው መስሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመሰለል መግባቱን ሰማች። ንግሥቲቱ እነዚህን እንግዳ ተራ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቷ አስጠርታ እንዲህ አለች። ዓለምን አንቀጥቅጠህ የገዛህ ታላቁ እስክንድ ዛሬ በሴት እጅ ተይዘሃል" አለችው ሲሉ ጽፈዋል። ሌላው ከላይ የተጠቀሰው የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ገጽ 176 እንዲሁም የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 113 ተብራርቷል።

5ኛ የሮማውያንን ኃይል ኢትዮጵያ ወግታ የመለሰች መሆንዋን ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ገጽ 267 እና መራሪስ አማን በላይ መጽሐፍ ከላይ የተጠቀሰውና ሌሎችም ብዙ መጽሐፍት ዘግበዋል። ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተደረጉት ጦርነቶችን በ14ኛው ክፍለ ዘመንና ኋላም በ18ኛው ብሎም በ19ኛው ክፍለ ዘመን በ15ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ለማንነቷ ተዋግታለች።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘናት ትግልና</u> የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 262 "1973 ዓም የዓረብ ማኅበር አባል አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሊቢያ ላይ ባደረጉት ስብሰባ ኢትዮጵያ እስራኤል ቀይ ባሕርን እንድትቆጣጠር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ስለሆነች የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት በማውገዝ የኦጋዴን ወንበዴዎችን መርዳትና ኤርትራን ሙሉ ነፃነትን እስከታገኝ ወንበዴዎችን መደገፍና ማበረታታት ያስፈልጋል የሚል ውሳኔ አሳልፈው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከላይ ጥቅስ የተወሰደው መጽሐፍ ዓመቱ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሲሆን በኢትዮጵያ 1965 ዓም መሆኑ ነው። አረቦች ትግላቸው ግቡን መቷል። ገንዘባቸው አልጠፋም ሰርቷል። ያ ማለት ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ለማራቅ ያደረጉት ሴራ ተሳክቷል።

ሜጀር ጀኔራል ሁሴን አህመድ <u>መስዋዕትነት እና ዕናት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 92" ቀደም ብሎ በተገለጸው መሠረት የኢትዮጵያ ጆኦ ፖለቲካዊ ሁኔታ በአፍሪቃ ቀንድ በቀይ ባሕር፣በሕንድ ውቅያኖስ፣ እንዲሁም በዓባይ ምንጭ የፖለቲካ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ያለው በመሆኑ ከ18ኛው ክፍለ



ዘመን ቀደም በ16ኛው ክፍለ ዘመን በውጭ ወራሪዎች የአገራችን ሀልውና ለበርካታ ዓመታት የተፈተነበት ጊዜ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ <u>ክህደት በመደም መሬት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 43" ኢትዮጵያ የግብፅንና የሱዳንን የውሃ ፍላጎት ሰማንያ በመቶ የሶማሊያን ፍላጎት መቶ በመቶ የምታሟላ ሀገር ነች። የሶማሊያ ሕዝብ በአብዛኛው ዘላን እንደመሆኑ መጠን ችግሩ ውሃና ግጦሽ ነው። ውሃውም ግጦሹም ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ወንዞች ማለትም ዋቢ ሸበሌ፣3 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ገናሌና ዋዳ 4 ቢልዮን ሜትር ኩብ፣ በጠቅላላው 7 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ሶማሊያ ይፈሳሉ። ከሰሜንና ስሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከዓባይ 50 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ከባሮ 14 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ ከባርካ 0.6 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ ከዳንድር ረሀድ 4 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በጠቅላላው 80 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ሱዳንና ግብጽ ይፈሳል። በኢትዮጵያና በኬንያ ድንበር ላይ ባለው የሩዶልፍ ሐይቅ ውስጥ በኦሞ ወንዝ አማካኝነት የሚጨመረው አማካይ ውሃ መጠን በማለት 15 ሚኒሊዮን ሜትር ኩብ ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ 100 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በነፃ ለጎረቤት ሀገሮች በየዓመቱ ትሰጣለች።"

"በዚህም ምክንያት የሱዳን፣ የግብጽና የሶማሊያ ሕልውና ከኢትዮጵያ ውሃዎች ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም መጠን የመከላከያና የውጭ ፖሊሲያቸውም በዚሁ ጥቅማቸው ላይ የተመሰረተ ነው። ሊወገድ የማይችል የተፈጥሮ ቁራኛነት ነው።" ይሉና ገጽ 44-45" የቀይ ባሕር አዋሳኝ ሀገሮች በጠቅላላው የዓረብ ሀገሮች እንደሆኑ ከባድ ጥረት እንዳለ ይታወቃል። የዓረብ ሀገሮች የኤርትራን ነፃነት ሙሉ ሙሉ ያደረጉትና ለትግሉ ብዙ ገንዘብ ያፈሰሱት ይህንን ዓላማ እውን ለማድረግ ነው። የቀይ ባሕር ፍፁም አረባዊ መሆን ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን የኃይል ሚዛን በማዛባት እስራኤልን ለተጨማሪ አደጋ ሊያጋልጣት ይችላል። ስለዚህም ኤርትራ የዓረብ ሊግ አባል እንድትሆንና በሌላ በኩል ደግሞ ወገናዊነቷን ጠብቃ ከአሜሪካና ከእስራኤል ጋር እንድትሆን ያልተቋረጠ የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ላይ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

መሰረታዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ከዓለም ገጸ ምድር (ካርታ) ለማጥፋት ከተነሱ ውለው አድረዋል! በነገራችን ላይ ሳናውቀው እኛው ኢትዮጵያውያን ተባባሪ ሆነናል። ከላይ እንደጠቀስኩት በሃይማኖት አሳበው ወንድሞቻችን መጥፎ ትምህርት አስተምረው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማፋጀት ታጥቀው ተነስተዋል። አንዳንድ ሰነዶች የሚያቀርቡት ታሪክ ቢኖር በኢትዮጵያ ውስጥ ሠላም እንዳይኖር የኢትዮጵያን እስላም በተለይ በቅርቡ የተፋፋመው ያጥፍቶ መጥፋት ቡድን በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ የፈጸመው አስነዋሪ ተግባር ከአረቦች የፈለቀ መሆኑ አይዘነጋም። አረቦች ከምንግዜውም በላይ ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተነስተዋል። አረቦች በህጋዊ መንገድ ኢትዮጵያውያንን እንደ ባርነት ቆጥረው ገዝተው እየወሰዱ ናቸው።

ለምሳሌ ከሚሄዱት ኢትዮጵያውያን የእስላም ስም ካልተሰጣቸው በቀር የመግቢያ ፈቃድ ቪዛ ሊያገኙ አይችሉም:: ይህ የአንድን አገር ማንነት መድፈርና ማስደፈር ነው:: ዜጎች የሚበሉት ሲያጡ ሊሰደዱ ይችላሉ:: ይህ በዓለም ላይ ያለ ሲሆን ኢትዮጵያውያንን ግን የወያኔ መንግሥት በህጋዊ ሰነድ አዘጋጅቶ በመሸጥ ላይ ነው:: አረቦችም በመግዛት ላይ ናቸው:: አረቦች ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ማራቃቸው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሰላም አጥታ ልማት በዓባይ እንድታተኩር አይፈልጉም:: እነሱ ከግብጽ ገዝተው ለመውሰድ ስለሚፈልጉ የኢትዮጵያን ብልጽግና አይፈልጉም::

እስልምና ሃይማኖት መስራች ነቢዩ ሙሐመድ "ኢትዮጵያውያንን ካልወጓችሁ አትውጓቸው" ብለው ትዕዛዝ መስጠታቸው አይካድም:: ነገር ግን ይህን ትምህርት አረቦች ሊቀበሉት ቀርቶ ሊሰሙት አይፈልጉም:: ለዚህም ነው ፀረ ኢትዮጵያ አቅዋም በመያዝ ከ8ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ እስከ ዛሬ እኛን ሊያጠፉ በመጣር ያሉት:: የዓባይ ውሓ ከአጻራሹ ከጣና ወጥቶ ለሱዳንና ለግብጽ መሬት ሕይወት የሚዘራበት የሆነው ሲጀመር ጀምሮ ነው:: ዓባይ ብቻውን አይደለም የሚሰደደው ሌላውን የኢትዮጵያን መሬት ሸርሽሮ በጥብጦ ይዞ ይጓዛል:: የዓባይ ወንዝ ከሀገሪቱ መልክአ ምድር አንድ አስረኛውን ክልል ቢሸፍንም ከዓለም አቀፍ ሕግጋት አንጻር በውሃ ሀብት የመጠቀም መብት የሁሉም ሃገሮች መሆን ሲገባው ግብጾች ግን ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ ልማት እንድታለማ አትፈልግም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስማምቶ በአንድነቱ እንዲኖር ዓረቦችና ግብጾች አይፈልጉም:: ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ገንዘብ ገዝታ የምታመጣው ጳጳስ ግብጽ ነበር:: እነዚህ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰርቶ እንዳይበላ የበዓላት ብዛት ደርበው ደራርበው ለኛዎቹ የበስማም ቄሶች ይነግሯቸዋል:: የእኛዎቹ የበስማም ቄሶች ደግሞ "ይህ የጳጳሱ ቃል ነው" ብለው እያወገዙ በሚሰራበት ቀን ሕዝቡ ቁጭ ብሎ እንዲውል ያደርጉታል:: መጽሐፍ ቅዱስ ጠንቅቆ ሕዝብ እንዲያውቅ አይፈልጉም:: መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው አውቀው ዶግማና ቀኖና ለይተው የሚያስተምሩትን "ፀረ ማርያም ናቸው" አስብለው ያስገድሏቸዋል:: ሕዝቡ በጥረቱ የሚያለማውን ልማት አውግዘው ያጠፉታል:: ለምሳሌ ወይን በአገራችን ይመረት ነበር:: የግብጾች ጳጳሳት ወይን እንዳይመረት አስከለከሉ:: ምክንያቱ ምንድነው ሲባሉ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሚፈተትበትን የባላገር መጫወቻ ሆነ" ብለው እንዲከለከል አስደረጉ:: ወይን የሚመረትበት ቦታ ደጋ ቀመስ ሲሆን ዛሬ ይህ አካባቢ "ወይና ደጋ" ይባላል:: ይህ ስም ቀደም ብሎ ወይን የሚመረትበት ቦታ መሆኑን ነው ታሪክ የሚዘክረው:: ወይን ዛፍ ተመንጥሮ ከጠፋ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ተቀድሶ የሚቆረብበት ዘቢብ እስከ መታጣት ደርሶ ሳለ መልሰው ራሳቸው የግብጽ ተወላጆች በንግድ ከውጭ አገር ዘቢብ እንዲገባ አደረጉ:: የዘቢብ ችግር ዛሬ ድረስ አለ:: ኢትዮጵያ ያሉ ቄስ ቤተሰብ ያላችሁ "ምን ልላክላችሁ" ብትሏቸው መልሳቸው "ዘቢብ" ነው::



ዛሬ ጠላቶቻችን ገዝግዘው ገዝግዘው ቀይ ባሕርን ከወሰዱ በኋላ ፊታቸውን ያዞሩት በዓባይ በኩል ነው:: ለምሳሌ በዘመነ ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን ጎጃም ውስጥ ብር ሸለቆ ከተባለው ለም መሬት ላይ የተጀመረው ልማት እንዴት እንደከሰረ ማሰብ ይገባናል:: በዚያ ልማት ወቅት ጣሊያኖችን ማርኮ ልማቱን ያስቀረ ኢሕአፓ ነው:: በዚህ ምክንያት አካባቢው ከልማት ይልቅ ወደ በርሃነት እንዲለወጥ ሁኗአል:: በዚህ ልማት መቋረጥ የተጠቀመችው ግብጽ ናት:: ለምሳሌ ይህ ልማት ኑሮ ቢሆን ኑሮ ከብር ሸለቆ አልፎ በሌሎች አውራጃዎች በተለይም በነቆምጨ አምባው ታታሪ አስተዳዳሪ አይነት ቢያገኘው በአባይ ላይ ከፍተኛ የሆነ ልማት ይካሄዳል:: ይህ ከሆነ ደግሞ የዓባይ ውሃ በልማት ላይ ይውላል ማለት ነው:: የዓባይ ውሃ በልማት ከዋለ ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚፈሰው መጠኑ ሊቀንስ ነው:: ስለዚህ በግብጽ ታቅዶ በሱዳን መንግሥት ጠቋሚነት ይህን ልማት እንዳይለማ ኢሕአፓ እንዲያዘጋው ታዘዙ:: ሲጀመር ጀምሮ በአረብ አገሮች ሰልጥኖ ወደ ሻዕቢያ ነፃ መሬት የገባው ኢሕአፓ ትዕዛዙን ፈጸመ:: ዛሬም ጠላቶቻችን መተማን ከወሰዱ ከመተማ ጣና ያለውን ርቀት ተመልከቱ:: ዓባይን በራሱ ገብተው ሊቆጣጠሩ ማሰባቸውን ምሁራን ማሰብ ተሳናቸው?

አያናዝጊ አ!ወልቃይት ያልታተመ::
"ዓባይ ነኝ ምን ነካው ይህ ሕዝብ ምን ሁንዋል
ከጥንት ጀምሮ ሲወቅሰኝ ይኖራል
እኔ ምን አጠፋሁ እኔ ምን በደልኩኝ
ቀርቶ ማደርያ ማረፊያ እንኳን የለኝ?::

ስፈጠር ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ
ትዕዛዜን ጠብቄ ቁልቁል በበርሃው ተምዘግዝጌ ስፈስ
አንድ እንኳ ያላሰበ በመስኖ ለማረስ
ዓባይ ቢጠሩህ አትሰማ
ምን አስቀምጠሃል ከግብፆች ከተማ
ይሉኛል አፍ ሞልተው
በሕብረት ሳይሰሩ እነሱ አንድ ሁነው
እኔ ከዛ ቦታ ከግብጾች ከተማ ደግሞስ ምንስ ኑሮኝ
ማንስ ነውከጥንት ጀምሮ ቁልቁል ሲነጉድ ይዞኝ::

እነሱው ተጠቅመው አፈሩን ቆልለው
እናንተን እርስ በርስ አጋጭተው አጣልተው
መሆኑ መቹ ጠፍቶኝ
እናንተ አንድ ሳትሆኑ እኔን የምትወቅሱኝ
ይቅር መገደቡ ቁጭ ብሎ ባንድነት የተመካከረ
ተናግሮ አናጋሪ ማን አለ እስኪ እኔን ለማስቀረት ማነው የጣረ
ዓባይ በጣናላይ ሄደ ተንኅባሎ
እኔው ውሃ እርሱም ውሃ ብሎ
እርስ በርሳችሁ ደምን ከማፋሰስ

ዓባይን ገድቦ ነበር ማረስ ማንደፋረስ ማረስ" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>ከሕደት በደም መሬት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 53 "1928 ዓም ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ ቢቆይም አስተዳደሩ የራስ-ገዝ ጠባይ የነበረውና ሕዝቡም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ዘመን ነበር። ከዚያም ተካታትሎ በኢጣሊያንና በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር የቆየበት ዘመን በድምር 19 ዓመት ሲሆን እነኘሀም ዓመታት የኦጋዴን ሕዝብ አስተዳደሩን ለማማረር ያበቁት የግፍና የጭቆና ዘመናት ነበሩ"።

ይሉና ገጽ 65 "ዛሬ ሶማሊያ ተዳከማለች። ዚያድ ባሬ ለአገዛዙ እንዲያመቸው ብሎ በፈጠረው የዘር (ጎሳን) ልዩነት ውጥረቱ እንዳለ ነው። ሶማሊያ ከባድ የሆነ እልቂትና የፖለቲካ ትርምስ ውስጥ ከገባች ዓመታት ተቆጥረዋል። ሕዝቦቿ በመጀመሪያ የፈለሱት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያም እጆችዋን ዘርግታ ተቀብላቸዋለች። ያለፓስፖርትና ያለቪዛ ጥያቄ እንደልብ ገብተው በሰላም የሚኖሩብት፣ የሚሰሩባት አንዳንዶቹም የከበሩብት ሀገር በመሆኗ ብዙ ሶማሌዎች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን አስተያየት እንዲለውጡ አስገድዷቸዋል። ምንም እንኳን ሱማሊያ የጠነከረ ማዕከላዊ መንግሥት ባይኖራትም የተለያዩ መሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች በግል እንደሚናገሩት ዛሬም የታላቋ ሲማሊያ ሀሳባቸውን አልለወጡም። ምንም ዓይነት መንግሥት በሱማሊያ ቢፈጠር ይህ ፖሊሲ የሚለወጥበት ጊዜ አልተቃረበም። የሶማሊያ ፖሊሲ ከአረባዊነትና ከአክራሪ የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ያለና የሚኖር የኢትዮጵያ ሥጋት ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ዛሬ በወያኔዎች ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኦጋዴን ጉዳይ የዘነጋ ይመስላል። ከላይ አባይ የሚያመጣውን ችግር እንደዘረዘርኩት ሁላ የቅርቡ ጠላት ሳቢው ኦጋዴ ነው። ኦጋዴን በተመለከተ ከዚህ በፊት ብዙ ደም ፈሶበታል። ይህን መሬት በነዳጅ የተትረፈረፉ አገሮች በሃይማኖት እያመካኙ ሰላም እየነሱ ነው።

ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም <u>የጦር ሜዳ ውሎ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 19 " እንግሊዞች ከሰሜን ሶማሊላንድን ጥላ ስትወጣ በአረብ አገሮች መሀከል ወደፊት ሠላም ሰፍኖ ተፈቃቅረው የሚኖሩባትን ሁኔታ አመቻችታ ሳይሆን የሶማሌ ዩዝ ሊግ፣የሶማሊያ ሊግ እና ግሬተር ሶማሌላንድ የተባሉ ፓርቲዎች አቋቁማና ታላቃዋን ሶማሌ መንግሥት የሚል ጠንቀኛ መሪሃ ግብር አስታጥቃ ነው የወጣችው። የሁሉም ፓርቲዎች ዓላማቸው የሶማሌ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች በሙሉ በአንድ መንግሥት ሥር መተዳደር አለባቸው፥ የሱማሌ ጎሳ የሆነ በሙሉ በአንድ መንግሥት መጠቃለል አለበት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሶማሌዎች በሙሉ በአንድ መንግሥት ሥር መጠቃለል አለባቸው የሚሉ ነበሩ። የታላቅዋ ሶማሌ ተቀዳሚ ዓላማ የእንግሊዝ መንግሥት ቀብሮት የሄደውን ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳውን ፈንጅ ማፈንዳት ነበር። በተግባር መተርጎም የሚቻለው እንዴት ነው? ሲባል ከኢትዮጵያ ከኬንያ መሬት ቆርሶ በመውሰድና ጅቡቲን በሙሉ ወደ ሱማሊያ ጠቅልሎ በማስገባት ታላቅዋን ሲማሌ መመሥረት ነው" ሲሉ ጽፈዋል።



## ምዕራፍ 7

## የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይረፍ?

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አምበሣ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 238 "አጤ ዮሐንስ ደብረ ታቦር በመጡበት ዘመን ራስ መንገሻ የአባታቸው የአጤ ቴዎድሮስ አፅም ከመቅደላ ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲሄድና በማኅበረ ሥላሴ ገዳም እንዲያርፍ ሲሉ በማሳሰባቸው በ1871 ዓም በመጋቢት ወር ከመቅደላ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ከአረፈበት ከርሠ መቃብር ወጥቶ ወደ ቤገምድር ተጓዘ። በጉዞውም ላይ እንዲያ ይጠላቸው የነበረው የወሎ ሕዝብ ከልጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር በመተባበር እያጀበና እየከበከበ በሚያርፍበት ቦታ ሁሉ እየደገሰ ቤገምድር ደንበር ድረስ በክብር ሸኘቷል" ይሉና "ይሁን እንጂ የንጉሠ ነገሥቱ ፍኖተ አፅም እንደተለመደው ክብር ሳይጓደልበት በየአረፈበት ጸሎተ ፍትሐት ሳይለየው ወዳጅ ዘመዳቸው እያለቀሰ ከመቅደላ ፊልሶ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም አረፈ" ሲሉ ጽፈዋል። ኢትዮጵያውያን አንድ ሁኖ እንዳይነሳ የወያኔ መንግሥት ቅስሙን ሰብሮ አንገት አስደፍቶ የምንኮራበት የጀግና ስም እንዳንጠራ ሊያደርገን ሲያቅድ ምን ይሁን ትላላችሁ?

አንዳንድ ወገኖቼ የሚሉኝ "4ኛው አጤ ዮሐንስ የሞቱበትን መተማን ወያኔ ለሱዳን ይሰጣል ማለት ዘበት ነው። ታሪካቸው መሆኑን ያውቃሉ" እያሉ ያዘናጉኛል። በመሰረቱ ወገኖቼ አልገባቸው ብሎ እንጅ ወያኔ ለታሪክ የሚሰሳ አይደለም። ለታሪክ የሚሰሳድማ ቢሆን ኑሮ 4ኛው አጤ ዮሐንስ ግብጽን ተዋግተው ድል ያደረጉበትን ጉራይንና ሌሎችንም ወረዳዎች ለኤርትራ አይሰጥም ነበር። ሌላው ቀርቶ በ1992 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባድሜንና ሌሎችንም ወረዳዎች በደሙ ያስመለሳቸውን መሬት እያወቀ ለሻዕቢያ አይሰጥም ነበር። ይህን ያደረገ መንግሥት አጤ ዮሐንስ የሞቱበትን መተማን ሊከላከል አይችልም። ስለዚህ የዋሕ ባትሆኑ መልካም ነው። ወያኔ ማህበረ ሥላሴ ገዳሙን አሳልፎ ሊሰጥ መሆኑን ከላይ ሰነድ እየተጠቀሰ ተጽፏል። ስለዚህ ወያኔ ለታሪክና ለአገር አንድነት ይቆማል እያሉ አንዳንድ ሰዎች ቤት ልማት ኢትዮጵያ ውስጥ የተቀበሉ ግለሰቦች የሚሉት እንጂ ተግባሩ የሚያረጋግጠው አገር አሳልፎ መስጠት ነው። ስለዚህ እኔ የምጠይቀው የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢትዮጵያ አንድ ትሁን ካልን ለአገር የተዋደቁት ጀግኖች አጽም መጠበቅ ይኖርበታል።

ተተኪው ትውልድ በእኛ ላይ የወቀሳ ናዳ እንዳያወርድብን የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያረፈበት ቦታ ማስቀረት ካልቻልን አጽማቸውን አውጥተን ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም ደማቸው ከፈሰሰበት ለ10 ዓመት ከተቀመጠበት መቅደላ መዳንኒዓለም ይመለስ ብሎ መነሳት ያስፈልጋል። አልያም ደግሞ ተደራጅቶ

በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት መሬቱ መስጠት የለበትም ወታደር ጠረፉን ይጠብቅ የአካባቢው ደህንነት ይጠናከር ብሎ መነሳት አመጽ መቀስቀስ አይደለም። የአካባቢው ሕዝብ በመነሳቱና በውጭ አገር ያሉት ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ምሑራን በማጋለጣቸው አሁን ለጊዜው ረገብ ያለ ቢመስልም "ያዴቆን ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም" እንደሚባለው ወያኔ አቅዷልና ሊተኛላት ስለማይችል ለኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግልና ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አንስቶ ደንበርን ማስጠበቅ የማንኛውም ግለሰብ መብት ነው። ይህን ጥያቄ በማንሳቴ የድርጅቴ ፈቃድ ይሰረዝብኛል! ቤቴን እቀማለሁ፤ዘመዶቼ ከስራ ይባረራሉ እኔም እንዳልገባ የመግቢያ ፈቃድ እከለከላለሁ በሚል ሆዳምነት ዝም ማለት ከአጥፊው ጋር አንድ ሁኖ መቆጠር መሆኑን መረዳት አለብን።

የታሪክ ምሑራን ለአገራችን አንድነት የታገሉ ግለሰቦች አጽምና ታሪክ ቦታ እንዲኖራቸው ከፍተኛ የሆነ ሐላፊነት አለባቸው። ስለዚህ የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ነገር ሲነሳ በዚህ በ3ኛው ሺህ መግቢያ ያለው ሁሳ ተወቃሽ ነው። የሕዝብ ሜድያዎች ሌላውን ወሬ ከማናፈስ ይልቅ አጽማቸው ያረፈበት ቦታ በሥርዓት ይጠበቅ አልያም ደግሞ ደማቸው ከፈሰሰበት መቅደላ መሄድ አለበት ብሎ መቀስቀስ ብተና አይደለም። ያጤ ቴዎድሮስን አጽም ከመቅደላ ማሕበረ ሥላሴ ልጃቸው ራስ መሺሻ ቴዎድሮስ በ1870 ዓም የወሰዱበት ምክንያት አንደኛ ማሕበረ ሥላሴ የኢትዮጵያ ማህል አገር በመሆኑን ስላወቁና ሌላው ደግሞ ለወደፊቱ የዓረቦች መስፋፋት አሳስቦአቸው ትውልዱ አጽማቸው ያረፈበት ቦታ በመሆኑ ይጠበቅ ብሎ ይነሳል ብለው አስበውም ይሆናል። ሌላው የራስ መሺሻ ዓላማ አባታቸው አጤ ቴዎድሮስ የተከፋፈለች ኢትዮጵያ አንድ ለማድረግ ቅድሚያ ጭንቅላታቸው በእውቀት የታነጸበት የታሪክ ትምህርት የተማሩበት ማህበረ ሥላሴ ገዳም መሆኑን አምነው ይሆናል። እነዚህን መሰረተ ጉዳዮች የዛሬው ትውልድ አመዛዝኖ ተገቢውን ቦታ እንዲሰጣቸው ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁሳ አደራዬ የጠበቀ ነው።

ኢትዮጵያውያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሆነ በደርግ ዘመነ መንግሥት ውጭ ወጥቶ መኑቶ መቅረት ተለምዷል። በሀገራቸው የመኖር እድል ስላላገኙ ከቤተዘመድ ተለይቶ ብቻን ሲንከራተት ኑሮ ወደ ማይቀረው ዓለም መሄድ ተለመደ። ታላላቅ በሀገር አስተዳደርና በወታደራዊ መሪ ሁነው የሠሩ ኢትዮጵያውያን አገራቸው ላይ መኖር አቅም አቅቶአቸው ተሰደው እየሞቱ ነው። ወደድነም ጠላን አገሪቱን በርዕሠ ብሔርነት የመሩት ሳይቀሩ በሥርዓት አልተቀበሩም። ምንም እንኳን ለሰባት ቀን አገር የመሩ ርዕሠ ብሔር ጄኔራል ተሥፋዬ ገብረ ኪዳን በሥርዓት አልተቀበሩም። ወደድነም ጠላን ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገር መርተው ብዙ ጥፋት ያደረሱ መሆናቸው ባይካድም በአንጻሩ ደግሞ ብዙ ልማት የሰሩ መሆናቸው ግልጽ ነው። ታዲያ እርሳቸው ሲሞቱ የት ይቀበሩ?

የትኛው የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር ነው ታሪኩ ሳይሸራረፍ ለተተኪው ትውልድ የተላለፈው? ሌላው የእኔ ቢጤው ሕዝብ ቀርቶ የታሪክ ጠበብቶች ናቸው የሚባሉ ሳይቀሩ የዕርሠ ብሔሮችን ስም በተርታ አይጠሩም። ለወደፊቱ



አስተውሉ ሲናገሩና ሲጽፉ "አጤ ቴዎድሮስ፤አጤ ዮሐንስ፤አጤ ምኒልክ፤አጤ ኃይለ ሥላሴ፤መንግሥቱ ኃይለ ማርያም"ብለው ሲጠሩ ከመሀል ብዙ መሪዎች ተረሱ። ለምሳሌ መባል ያለበት "አጤ ቴዎድሮስ፤አጤ ተክለ ጊዮርጊስ፤አጤ ዮሐንስና አጤ ምኒልክ፤ልጅ እያሱ፤ንግሥት ንግሥታት ዘውዲቱና አጤ ኃይለ ሥላሴ፤ርዕሠ ብሔር አማናዶምና ርዕሠ ብሔር ተፈሪ ባንቲ፤ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና ርዕሠ ብሔር ተሥፋዬ ገብረ ኪዳን ርዕሠ ብሔር ታምራት ሳይኔና ርዕሠ ብሔር መለስ ዜናዊ"ብሎ መጥራት አይፈልጉም። ይህ እንዲለወጥ የአንድነት አቢዮት መጀመር አለበት። ከላይ እንዳልኩት በሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ መርጦ ያነገሣቸው ባለመሆናቸው ከሥልጣን ሲወርዱም ተገለው አልያም በቅርቡ ደግሞ አገር ጥለው መጥፋት ተጀመረ።

መቼ ይሆን የአገሪቱን መሪዎች በሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ አልቅሶ የሚቀብራቸው? ልቅሶም ይናፍቃል? አጤ ቴዎድሮስ የተበታተነች አገር አንድ ለማድረግ ቆርጠው ሲነሱ የገጠማቸው ችግር ከውጭ ወራሪ ጋር ተባብሮ እርሳቸውን ማስገደሉ ነው። ሌሎችም መሪዎች መቃብራቸው አይታወቅም። ዜና መዋዕላቸው በሥርዓት አይጻፍም። ይህ እንዲሆን የአንድነት አቢዮት መስተጋባት አለበት። ከዚህ በፊት በአንድ መጣጥፌ አልፎ አልፎ የምጠቅሰው ነገር ቢኖር ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስደተኛ ናቸው። ሰው ናቸው ሲሞቱ የት ይቀበሩ? አስከሬናቸው እንዴት ይገባል? ማን ነግ ለኔ ብሎ በሥርዓት አክብሮ ይቀበላል። ስለ አገራቸው የሚንገበገቡ ኢትዮጵያውያን እየናፈቁ እድሜያቸውን በስደት አሳልፈው ሲሞቱ ሬሳቸው የሚመለሱ ብዙ ናቸው። ከመሞታቸው በፊት ለምን አገራቸው አይገቡም?ኀበዝ ብዙ ችግሮች እየመጡብን ነው።

ከላይ እንዳልኩት የአገሪቱን መሪዎች ታሪክ በተመለከተ ሁሉንም ላንወዳቸው እንችል ይሆናል።ነገር ግን እውነቱን ልንደብቅ አይገባም። በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተመለከትኩት ጉዳይ አንዱን የአገር መሪ በራሱ መነጠር አይቶ መጥላት ሲገባው ሌሎች በነገሡት ላይ ተነስቶ መጥላት አግባብ አይደለም። መሪዎች ሰዎች ናቸው። ስዕተት አለባቸው። መጥፎ የሰሩትን መጥፎ ብሎ መጥቀስና ጥሩ የሰሩትን ጥሩ ብሎ መጻፍ በእኛ ዘንድ አልተጀመረም ለምን? ካንድ ወዳጄ ጋር የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያለው ማህበረ ሥላሴ ሲሆን ወደ ሱዳን ሊከለል ነው ይህን በተመለከተ ምን ታስባለህ? ስላቸው የመለሱልኝ መልስ አስደነገጠኝ" ይህ የማህል አገር አማራ ትቢት ሊመታ የሚችለው የነዚህ ዓይነት ጀብደኞች ታሪክ ሲጠፋ ነው። ምነው በተሉ ማህበረ ሥላሴ ወደ ሱዳን ተከልሎ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ባንሰማ ደስ ባለኝ?" ሲሉኝ ስለ ወዳጄ አፈርኩ። በትክክል ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚያስቡትን ሰዎች አደራ ለማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይረፍ? ይህን አይነት አላፊነት የሚሸከም ትውልድ ይኖር ይሆን?።

ቴዎድሮስ ለፋ ጣረ ኢትዮጵያ እንድትኮራ
ሕይወቱን ሰዋላት ትውልዱ እንዲኮራ
አንተ አዲሱ ትውልድ በእንተነትህ ኩራ
ቴዎድሮስ ተጥሉብሃል የታሪክ አደራ።

## ምዕራፍ 8

## ጠቅላላ ሠነድ ከሃይማኖትና ከታሪክ መጽሐፍት


1 መጽሐፍ ቅዱስ
2 ቅዱስ ቁርዓን
3 በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ
4 አንበር መስቀልየ በዲባ መስቀል መስቀሌን በመስቀለኛ ላይ አኑር
5 ድርሳነ ኡራኤል
6 ሰኔ ጎለጎታ
7 አባ ቀውስጠስ የስሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ይግባኝ ለክርስቶስ
8 ይድነቃቸው ተሰማ ሰምና ወርቅ ተሰማ እሸቴ
9 መምሕር ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ማደስ ወይስ ማፍረስ
10 አስቻለው ከበደ ክርክቤዴል ሳዶፍ ኢትዮጵያና የሰማይ ኃያላት
11 አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ
12 ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የኢጣሊያን ጦርነት
13 ሀዲስ አለማየሁ ትዝታ
14 ማርሴል ግሪዮል ተርጓሚ ላቀች እክሊሉ የንጉሥ ነገሥቱ ትውስታ በ1929 ዓም
15 ግደይ ባሕር ሹም አሞራ
16 ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ሞት የተፈረደባቸው 15 ሺህ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይ ምጽዋ
17 ሻለቃ ስለሽ ፍስሃ አንድነት ለአንድነት
18 የህወሓት ኮሚኒስት ሃይል የ10 ዓመት ግምገማ ሐምሌ 1977 ዓም
19 ቀደሰ አለማየሁ ሞገስ ደርሶ ሁሉም ሉሁን ይወቅ
20 ዶ/ር ኃይሌ ወልደ ሚካኤል አብሮነት በኢትዮጵያ
21 መምህር ስፍሀ ጽዮን ካሣ መርኖ አጻም ወግዕዝ አጻምና ግዕዝ
22 ያሬድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር
23 ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ
24 ሒራ አሳታሚና አከፋፋይ የግል ማህበር የሐበሻው ሂጅራና ሙሃጂሮች
25 ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መዛሪያዎች
26 አህመድ ሙነወር ሰይድ ኢብራሂም የእስልምና ድንጋጌ የአመጣጥ ታሪክ
27 ዲያቆን ቢጋሻው ደሳለኝ የመስቀሉ ሥር ቁማርተኞች
28 ዶ/ር እያሌው ሲሳይ የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ታሪክ
29 አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ
30 ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች
31 በላይ ግደይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ
32 ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ
33 ዶ/ር ሔነሪ ብላንክ ዳኛው ወልደ ስላሴ እንደተረጎመው የእስራት ዘመን በአበሻ አገር
34 ብርሃኑ ጣሰው የፍቅር መቅረስ
35 ነጋ ወልደ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ
36 ዘውዴ ገብረ ሕይወት የሕይወት ውጣ ውረድ
37 አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ





38 አስናቀ እንግዳ አረባዊ አጤነት የአፍሪካ ቀንድ ፍዳ
39 መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ
40 ኅበዜ ጣፈጠ አባ ጤና ኢያሱ
41 ዘውዴ ረታ ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ
42 ከበደ ተሰማ የታሪክ ማስታወሻ
43 ጀኔራል ነጋ ተገኝ የኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974
44 ሕይወቴ ሕዳሩ ያቺ ቀን ተረሳች
45 ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም 1900-1966
46 ዳኛው ወልደ ሥላሴ ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት
47 ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ
48 ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን የትግል ፍጻሜ
49 ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሽክም የማይከብደው ሕዝብ
50 ሻለቃ ጌታቸው የሮም ስም ከመቃብር በላይ
51 ብላቴ ጌታ ማኅተመ ስላሴ ዝክረ ነገር
52 ፊንታዬ ወ/ሊባኖስ የአባ ጠቅል አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት
53 ልጅ አግባው ውብነህ ራስ አሞራው ውብነህ
54 የስዩም ጣሰው ማስታወሻ የንጉሡ ገመና
55 ሊቀ ካህናት ስሎሞን ገብረ ሥላሴ በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም
56 ኮሞዶር ጣሰው ደስታ የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል
57 ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ቅጽ ሁለት
58 ገብረ መድህን እርአያ እና አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅ ሤራ
59 ባብሌ ቶላ አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ
60 ገብረ መድህን እርያ አብርሃም ያየህ የወያኔ ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ
61 አማረ አፈለ ብሻው አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች
62 አማረ አፈለ ብሻው የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ
63 ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ ቢጋሻው
64 እያናዚጊ አ!ወልቃይት ያልታተመ
65 መጽሐፈ ሕግጋት
66 ታጋይ ገሠሠ ረታ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያ ደብተራ
67 ተወልደ ገ/ተንሳይ ኮ/ል ባድመ እንደምክንያት
68 መዳኅኔ ታደሰ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት
69 Kshsay Berhe Ethiopia:Demcratization and Unity
70 70 0ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የነፃነት ጎህ ሲቀድ
71 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ
72 የካባ ሲሳይ አምባው የጣረ ይወጣል
73 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ኑቢያ አክሱም ዛጉዬ
74 አባ ተሥፋ ስላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የተዋሕዶ አንበሳ
75 መራሪስ እማን በላይ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ
76 ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ
77 ቀ/ ኃ/ሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሕይዎቴና የኢትዮጵያ ርምጃ ቅጽ 2
78 ሜጀር ጄኔራል ሁሴን አሕመድ መስዋዕትነት እና ጽናት

79 የቀድሞ የባሕር ኃይል መለዮ ለባሾችና..የኢትዮጵያ የባሕር ጠፈና ባሕር ኃይሏ
80 ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ ክህደት በደም መሬት
81 አስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል ጋሀዲ
82 ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም የጦር ሜዳ ውሎ
83 የካባ ሲሳይ አምባው እግዚአብሔር አልረሳኝም የለመንኩትን አልነሳኝም
84 ገሪማ ታፈረ አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ
85 ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ መልክሀ ኢትዮጵያ

ከመጽሔትና

86 ዶ/ር ሒሩት ወልደ ማርያም ሐመር መጽሔት 15ኛ ዓት /ቁ 16 የካቲት 2 ሺህ ዓም
87 አበራ ለማ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 13 ሰኔ 1992 ዓም
88 ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ ሓንቲ አንድ ዋን ኢትዮጵያ
89 ጌታቸው ረዳ ዜጋ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 8 ሰኔ 1994 ዓም
90 መራራስ አማን በላይ ጉግሣ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁ 1 ሐምሌ 1993 ዓም
91 በቡድን ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 057 ሚያዝያ 1996 ዓም
92 ሙዳይ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም
93 ቀኛዝማ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ሐ
94 መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም
95 ጌታቸው አማረ ኢትዮጵያ ርቪው መጽሔት ሚያዝያ 1985 ዓም ወይም 1993
96 ደመዘቅ መንግሥቱ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 72 ሐምሌ 1997 ዓም
97 ልጅ ሚካኤል እምሩ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 074 ታህሳስ/ጥር 1996 ዓም
98 ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ዜጋ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁ 2 ጥቅምት 1996 ዓም
99 አቶ ታምራት ላይኔ ዜጋ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 7 መጋቢት ሚያዝያ 1994 ዓም
100 ደርብ ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1986 ዓም
101 ዞብል አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም
102 አደራ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 1985 ዓም ሐ
103 የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ታህሳስ 1986 ዓም
104 ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 10 ቁጥር 11/1995 ዓም ሐ
105 ዶ/ር ፒተር ኒዮተቦክ መስታውት መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 ዓም
106 ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፍወርቅ እሰር መጽሔት 1990 ዓም ሐ
107 ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 6/1992 ዓም
108 ገ/ፃድቅ አበራ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 3 ነሐሴ 1991 ዓም
109 ውዱ ገበየሁ ዜጋ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 5 የካቲት/መጋቢት 1992 ዓም
110 ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም
111 ሞረሽ መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 2/1987 ዓም
112 አማረ አፈለ ብሻው ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም
113 አርበኛው መጽሔት ነሐሴ 1991 ዓም
114 ጌታቸው ወልዴ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሐምሌ 1985 ዓም
115 ሻለቃ መላኩ ተፈራ ኢትአጵ መጽሔት ታህሳስ 1992 ዓም
116 ወልዱ ሃይሌ ሩሕ መጽሔት 1ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥቅምት 1993 ዓም
117 ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ነሐሴ 1996 ዓም
118 አምባሳደር አህዱ ሳብሬ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅ 1 ቁ 6 ጥር 1996 ዓም
119 ረዳት ፕሮፌሰር መድኃኔ ታደሰ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ግንቦት 1997 ዓም



120 ገብረ መድኅህ አርአያ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሕዳር 1986 ዓም
121 ግደይ እቁባይ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅ 2 ቁ 11 ሰኔ 1997 ዓም
122 ብሥራት አማረ ኢትዮአጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 044 የካቲት 1995 ዓም
123 ሚካኤል እምሩ ኢትዮአጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 045 መጋቢት 1995 ዓም
124 አሰፋ ጫቦ ዜጋ መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁ 8 ሚያዝያ 1993 ዓም

መጣጥፍ

125 ሜጋ ማከፋፍያ ኃ/ተ/ የግል ማህበር
126 ሹመት ሲሻኝ የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት ትግል
127 ዲያቆን ናትናኤል ታምራት እግዚአብሔር ለምን ዝም አለ?
128 ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው
129 ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ ሰስቱ ምንትዋቦች
130 ክቡር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም
131 ያሬድ ጥበቡ የአመጹን አዙሪት ለመስበር
132 የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ረቂቅ ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም
133 ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ ቋሚ ጽ/ቤት ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት
134 አሸብር ተቆርቋሪ የለለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ
135 ዶ/ር ጌቱ ገላይ ጭማቂ ጹሑፍ
136 ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለሸንጎ የቀረበ 1982 ዓም

ጋዜጣ

137 አበባው ይግዛው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 1965 ዓም
138 አቶ ሰዩ አብርሃ አዲስ ነገር ጋዜጣ ቅ 1 ቁ 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም
139 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 7 ቁጥር 8 መጋቢት 1993 ዓም
140 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 6 1993 ዓም
141 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 7 1995 ዓም
142 ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 3 1995 ዓም
143 ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 4 1995 ዓም
144 መጽሐፈ ሲራክ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 5 ቁጥር 7 1992 ዓም
145 መይሳው ጋዜጣ ጥር 15 ቀን 1992 ዓም
146 ፊያሜታ ጋዜጣ ታህሳስ 1990 ዓም

ዘማሪያንና ድምጻውያን

147 ዘማሪት ፀዳለ ጎበዜ እቤቱ የሆንብኑን አስብ የሥዕል ድምጽ ክር
148 መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምሩ
149 ዲያቆን በሪሁን ወንድወሰን እስራት እንዳይፀናባችሁ አታፈዙ
150 ኪሮስ አለማየሁ ዘፈን "አይበልናዶ" አላልናችሁም!
151 ሻምበል በላይነህ ዘፈን "ታሪክ ይመስክር"
152 ይርጋ ዱባለ ዘፈን "ወልቃይት ጠገዴ"

153 ፋሲል ደምወዝ ዘፈን "አለ ነገር ዘንድሮ አለ ነገር"

በራሪ ወረቀት

154 ከኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም
155 ግንቦር 7 ድምጽ ሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓም
156 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
157 የጎንደር ክፍለ ሀገር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ተራዝ መስከረም 1984 ዓም
158 ታጋይ ብርሃኔ ገ/ ጻድቅ የኢትዮጵያ ራዲዮ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም
159 የጎንደር ክፍለ ሀገር አውራካዎችና ወረዳዎች ምክትል ወረዳዎች
160 ከሰሜን አሚሪካ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን
161 አውደ ኢትዮጵያ ልዩ እትም 1/2000 ዓም

በቴሌቭዥን የቀረበና ጥያቄና መልስ በውይት የተነገሩ

162 የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚሽን የሲዲ ክር
163 ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ለወጣቶች ንግግር ሲያደርጉ
164 አቶ ማሞ ስበር፤ ጥያቄና መልስ
165 አቶ ፀጋ በላይ፤ ጥያቄና መልስ ብሉም ደብዳቤያቸው
166 አቶ ወልደ ገብርኤል አስጌ፤ ጥያቄና መልስ
167 አቶ ሊቀ እጅጉ፤ ጥያቄና መልስ
168 ስሜ እንዳይነገር ያሉኝ፤ ጥያቄና መልስ
169 ሻለቃ ጌታቸው የሮም፤ ጥያቄና መልስ
170 አቶ ዘውገ ፈንታ፤ጥያቄና መልስ
171 ክቡር አቶ ፈንታዬ ወ/ሊባኖስ፤ ጥያቄና መልስ
172 ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዲቅ፤ ጥያቄና መልስ
173 የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ ገለፃ
174 አምሳለቃ )ደጀዝማች) አፈራ አዳነ ጥያቄና መልስ
175 አቶ ጫቅሌ ኩምነገሬ ጥያቄና መልስ
176 አባ ታጠቅ ቡድን የተመለከቱትንና የሆነውን የገለፁልኝ
177 አቶ ታመነ ወይም ሊንጎ የኢዲዩ ወሳኝ ሰው በጨዋታ።
178 የጭልጋው አራሽ አንደፋራሽ ንብረታቸውን ሱዳን የወረሰባቸው።

በነገራችን ላይ ይህን መጽሐፍ ማንም እንዲመለከትልኝ ምክር አልጠየኩም። በእኔ ብቻ ታርሞ ለንባብ የቀረበ በመሆኑ ድክመት ቢታይበት ተጠያቄው ራሴ ነኝ። ስለዚህ በምታዩት ድክመት አንባቢያንን ምክራችሁን እሻለሁ።

አሳስቦ ሳስጀመረኝ አስጀምሮ ሳስፈጸመኝ
ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን!

መልዕክት ከአያናዚጊ ለዚህ መጽሐፍ አንባቢያን የአደራ ጥሪ <u>አ!ወልቃይት</u> እያልኩ በተደጋጋሚ በሐዋርያ ጋዜጣ እጽፈው የነበረውን መጣጥፍ ያነቡ ነበር? እንግዲያውስ ያንን መጣጥፍ መጽሐፍ አድርጌ ለማውጣት ጀምሬአለሁና አንባቢያንን ትብብራችሁን እጠይቃለሁ።

1ኛ ስለ ወልቃይት የምታውቁትን ታሪክ ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ላኩልኝ። P.O.BOX 492 Seattle WA 98111 U.S.A አማካይነት ቢልኩልኝ ሊደርሰኝ ይችላል።

2ኛ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት በወልቃይት ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ግፍና ሰቆቃ በሚመለከት የታሰሩና ጠፍተው የቀሩ ሰዎችን ስሞች ቢቻል ከፎቶ ግራፋቸው ጋር!

3ኛ ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ችግር በሚመለከት የሚያውቁትን ስሞች ቢቻል ከፎቷቸው ጋር!

4ኛ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ቤተሰቦቻችሁን በግፍ አስሮና አሰቃይቶ የገደላቸውን ሰማትታት ቢቻል ከፎቶግራፍ ጋር ታሪካቸውን!።

5ኛ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ላይ የምታውቁትን ታሪክ! ለወደፊቱ ለትውልድ ይድረስ የምትሉትን!

ኢትዮጵያውያን እንዲያውቁት ለማድረግ የምታውቁትን ታሪክ ላኩልኝ። የምትልኩትን ደብዳቤ ከፖስታው ላይ ለአያናዝጊ እያላችሁ ጻፉበት! ስለ ትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ።

<u>አ!ወልቃይት</u>
በቅርብ ቀን ለንባብ ይቀርባል

ከማክበረ ሠላምታ ጋር
አያናዝጊ ኮሎምቦስ ኦሃዮ!